አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


# የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች ጥናት

በ


ሙሉዓለም አሰፋ


ለአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ፅሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት
የቀረበ ጥናት

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች ጥናት

በ

ሙሉዓለም አሰፋ

ለአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ፅሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት
የቀረበ ጥናት

አማካሪ

የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች ጥናት

በ

ሙሉዓለም አሰፋ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| ............................................................ | ........................... |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ............................................................ | ........................... |
| የውስጥፈታኝ | ፊርማ |
| ............................................................ | ........................... |
| የውጭፈታኝ | ፊርማ |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት " የነገዴ ማህበረሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች ጥናት " በሚል ርዕስ የተከናወነ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ የነገዴ ማህበረሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች አሰራርና አገልግሎት ማሳየት ነው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የቤተ መፅሃፍት ንባብ እንዲሁም ጥናቱ በሚከናወንበት ቦታ ላይ በአካል በመገኘት በምልከታ ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል። መረጃዎቹም እንደ አስፈላጊነቱ በቪዲዮና በፍቶ ግራፍ እንዲሁም በመቅረፀ ድምፅ ተሰንደዋል። የመተንተኛ ዘዴው ተግባራዊ የሚደረግበትን አቅጣጫ የሚመራ የክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብን/performance theory/ ጥናቱ ተጠቅሟል። በስፌት እና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት ምን ይመስላል? ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? የእጅ ስራዎቹ ላይ የሚታዩ ያታዊ ተሳትፎዎች ምን ይመስላሉ? የሚሉ ጉዳዮችን ተመልክቼ የሚከተለው መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ። ጥናቱ በተወሰነባቸው 03 እና 16 የባህር ዳር ቀበሌዎች ላይ በነገዴ ኅብረተሰብ ለስፌት ስራ የሚሆነው ጥሬ ቁስ ደንገል ከኅብረተሰቡ ጥንት አመጣጥ እና የኑሮ ዘይቤ ጋር የተያያዘ መሆኑን በጥናቱ ታውቋል። የስፌት ቁሶቹን በሰርግ ፣ በለቅሶና መሰል የማህበራዊ ህይወት ላይ ኅብረተሰቡ እንደሚጠቀምባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የስፌት ቁሶች በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውና ለስፌት ስራ የሚውለውን ደንገል መቁረጥ ፣ ማድረቅ ፣ መሰፋትና ማስጌጥ ሴቶች ቤት ውስጥ ከሚሰሯቸው ስራዎች ጋር ተመሳሳይ ስለሆኑ እንዲሁም ስፌት ለመስራት ከፍተኛ ጉልበትን ስለማይጠይቅ የስፌት ስራ በሴቶች እንደሚሰራ ጥናቱ አረጋግጧል። ከኅብረተሰቡ ውጪ ያሉ ሰዎች ከነገዴዎች ላይ የስፌት ውጤቶችን በመግዛት በቁሶች ላይ የተለያዩ ጌጦችን በመጨመር እንደሚያስጌጧቸው ለማወቅ ተችሏል። የስፌት ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና የተጠቃሚው ኅብረተሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሶቹ ድሮ ከሚሰሩበት መልክ እና ጥሬ ቁስ በአሁኑ ወቅት እየተቀየሩ እንደሆነ ጥናቱ አረጋግጧል። የድንጋይ ወፍጮ እና የታንኳ ስራ በወንዶች የሚከናወነው ስራው ጠንከር ያለ ጉልበትን የሚጠይቅ በመሆኑ እንዲሁም በቤት ውስጥ ባለመሰራቱ ምክንያት እንደሆነ ተረጋግጧል። ሙያውንም ከአባቶቻቸው እንደለመዱት ከመረጃ አቀባዮች የተገኘው መረጃ አመላክቷል። የኅብረተሰቡ የእጅ ስራዎች ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የእለት ተእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የኅብረተሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ ፍልስፍና ፣ ማንነት ፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማስተዋወቅ በኩል አስተዋፅኦ እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የጥናቱን ግኝት መነሻ በማድረግ የሃይማኖት አባቶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ፣ የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንደስትሪ እንዱሁም ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሙያው ለቀጣይ ትልድ የሚተላለፍበትን ሁኔታ ቢመቻቹ መልካም ነው ።

# ምስጋና

ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ አቅጣጫን በማሳየትና ስህተቶቼን በማቃናት እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር የኔዓለም አረዶ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በጥናት ስራዬ ውስጥ ከእኔ ጎን በመሆን አብረውኝ ለደከሙት ሁሉ ለቤተሰቦቼ እና ለጓደኞቼ እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ አሻራቸውን ላሳረፉ ሁሉ ጥልቅና የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ሙዳዬ ቃላት

ከዚህ በታች ያሰፈርኳቸው ቃላት በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱና ለአንባቢ እንግዳ ይሆናሉ ብዬ ያሰብኳቸው ናቸው፡፡ ለቃላቱ ፍቺ የሰጠሁትም በተጠኚው ኅብረተሰብ ትርጓሜ እና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ባለው ፍቺ መሰረት ነው፡፡

**ሌማት** ፡- ከአክርማ ወይም ከስንደዶ የሚሰራና ለእንጀራ ማስቀመጫነት የሚያገለግል መሶብ፡፡ (32)

**መሶብ** ፡- ከአክርማና ከስንደዶ የተሰፋ ለእንጀራ ማስቀመጫ ወይም ለመብያ የሚሆን የቤት ዕቃ፡፡ (51)

**መሶብ ወርቅ** ፡- ልዩ ልዩ ቀለማት ባላቸው አለላዎች ተጊጦ የተሰፋና ረዘም ያለ እግር ያለው መሶብ፡፡ (51)

**ሙዳይ** ፡- ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለጌጣጌጥ ፣ ለብርጉድ ማስቀመጫነት የሚገለገሉበት ፣ በአገልግል ቅርፅ የምትሰራ አነስተኛ የስፌት ዕቃ፡፡ (68)

**መዶሻ** ፡- ከባድ የብረት ጭንቅላትና የብረት ወይም የእንጨት እጀታ ያለውና ምስማር ለመምታት ፣ ድንጋይ ለመፈርከስ ፣ የጎበጠ ብረት ለማቃናት ፣ የሚያገለግል የተለያየ መጠን ያለው መሳሪያ፡፡ (64)

**መጅ** ፡- በወፍጮ ላይ ወደፊትና ወደኋላ በማመላለስ እህልን ለመከካት ወይም ለመፍጨት የሚያገለግል ትንሽ የወፍጮ ድንጋይ፡፡ (64)

**ሰበጢራ (ሰበጠራ)** ፡- ከቀርከሃ ፣ ከማሽላ አገዳ ፣ ከሽምበቆና ከመሳሰሉት የሚሰራ የእንጀራ ቅርጫት ወይም ሰፌድ፡፡ (117)

**ሰበዝ** ፡- የተሰነጠቀ ስንደዶና አክርማ በላዩ ላይ እየተጠመጠመበት የሚሰፋና የሚያያዝ ያልተሰነጠቀ ስንደዶ ፣ የስፌት ሳር ፣ ሳሩም ሰበዝ ይባላል፡፡ (116)

**ሰፌድ** ፡- ከአክርማ ፣ ከስንደዶና ከግራምጣ የሚሰራና ለእህል ማበጠሪያና ማንፈሻ እንዲሁም ከምጣድ ላይ ለእንጀራ ማውጫ የሚያገለግል ስፌት፡፡ (128)

**ታንኳ** ፦ ከቀርከሃ ወይም ከሸንበቆ ወይም ከደንገል ፣ የሚሰራ የውሃ ላይ መጓጓዣ፡፡ (266)

**አለላ** ፦ ቀለም የተነከረ ስንደዶ ወይም አክርማ፡፡ (301)

**አለላ ሙዳይ** ፦ ከአለላ የተሰራ ትንሽ ሙዳይ፡፡ (301)

**አገልግል** ፦ በውስጡ ምግብ ወይም የተለያየ ዕቃ ለመያዝ የሚያገለግል ባለመክደኛ የስፌት ዕቃ፡፡ (340)

**እፊያ** ፦ የመሶብ ፣ የድስት መክደኛ፡፡ (368)

**ኩታራ** ፦ ጉብል ፣ብላቴና፡፡ (384)

**ወራንታ** ፦ ከግራምጣ ወይም ከአክርማ ፣ የሚሰፋና ከቁና ከፍ የሚል የእህል መስፈሪያ፡፡(405)

**ወንፊት** ፦ እህልን ወይም ዱቄትን ለመንፋትና ተፈላጊውን ከማይፈለገው ለመለየት የሚያገለግል ከአክርማ ፣ ከስንደዶ ፣ ከግራምጣ ወይም ከሽቦ ተታቶ የሚሰራ ዕቃ፡፡ (413)

**ወፍጮ** ፦ በሰው ጉልበት ወይም በሞተር ሃይል ሊሰራ የሚችልና እህልን ወይም ሌላ ነገርን ለመፍጨት ፣ ለማድቀቅ የሚያገለግል ዕቃ ፣ መሳሪያ ወይም የተወቀረ ድንጋይ፡፡ (422)

**ዶማ** ፦ እጀታ ያለው መቆፈሪያ፡፡ (485)

**ግራምጣ** ፦ በቆላና በወይናደጋ በረግረግ ውስጥ የሚበቅልና ለስፌት ስራ የሚያገለግል ፣ ግንዱ አራት ማእዘንነት ያለውና እንደቄጠማ ወፍራም የሆነ የሳር አይነት፡፡ (519)

**ግርድ** ፦ አውድማ ላይ ምርቱ (ፍሬው) ከገለባ በሚለይበት ጊዜ ከዋናው ምርት ውስጥ እየተንገዋለለ የሚወገድ የእህል ፍሬ ስብርባሪ ፣ በደንብ ፍሬ ያልያዘና በእንቡጥነት የቀረ እንጨት ፣ ብጣሪ ፣ ንፋሽ ያለበትና ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ የምርት ክፍል፡፡ (521)

**ማውጫ** **ገፅ**


አጠቃሎ ....................................................................................................i

ምስጋና .....................................................................................................ii

ሙዳዬ ቃላት .............................................................................................iii

1. ምዕራፍ አንድ መግቢያ ...............................................................................1

1.1.የጥናቱ ዳራ ............................................................................................1

1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..........................................................................2

1.3.የጥናቱ ዓላማ ........................................................................................2

1.4.የምርምር ጥያቄዎች ..................................................................................3

1.5.የጥናቱ አስፈላጊነት ..................................................................................3

1.6.የጥናቱ ወሰን ..........................................................................................4

1.7.የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ...............................................................................4

1.7.1.የናሙና አመራረጥ ስልት ........................................................................4

1.7.2.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ............................................................................5

1.7.2.1.ምልከታ ...........................................................................................5

1.7.2.2.ቃለመጠይቅ ......................................................................................6

1.7.2.3.ተተኳሪ የቡድን ውይይት .......................................................................7

1.7.3.የመረጃ አተናተን ዘዴ ............................................................................7

1.7.4.ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ..........................................8

1.8.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ................................10

1.8.1.ያጋጠሙ ችግሮች ችግሮች ....................................................................10

1.8.2.የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................................................11

1.9.የጥናቱ አደረጃጀት ...................................................................................11

2. ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት

2.1.ፅንሰ ሐሳባዊ ቅኝት .................................................................................12

2.1.1.ቁሳዊ ባህል .........................................................................................13

2.1.2.የቁሳዊ ባህል ባህሪያት ........................................................................15
2.1.2.1.ተጨባጭነት ........................................................................15
2.1.2.2.ተፈጥሯዊነት ........................................................................15
2.1.2.3.ዘመን ተሻጋሪነት ........................................................................16
2.1.3.የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ........................................................................16
2.1.3.1.ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ........................................................................16
2.1.4.የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት ........................................................................18
2.1.5.የቁሳዊ ባህል ምደባ ........................................................................19
2.1.6.የቁሳዊ ባህል አገልግሎት ........................................................................21
2.2.ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት ........................................................................21
2.3.የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................................................................23
2.3.1.በነገዴ ወይጦ ኅብረተሰብ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ........................................................................24
2.3.2.ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች ........................................................................26

3. ምዕራፍ ሶስት
3.1.የባህር ዳር ከተማ አካባቢያዊ ዳራ ........................................................................31
3.2.የነገዴ ኅብረተሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........................................................................34
3.2.1.የነገዴ ወይጦ ጥንት አመጣጥ ........................................................................34
3.2.2.ስያሜ ........................................................................35
3.2.3.ቋንቋ ........................................................................36
3.2.4.ሃይማኖትና ባዕድ አምልኮ ........................................................................37
3.2.5.ኅብረተሰብ ግንኙነት ........................................................................38
3.2.6.አስተዳደራዊ ሁኔታ ........................................................................40
3.2.7.ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ........................................................................41
3.2.8.የጋብቻ ሁኔታ ........................................................................42

4. ምዕራፍ አራት
በነገዴ ኅብረተሰብ የእጅ ስራዎች መረጃ እና ትንተና ........................................................................43
4.1.የስፌት ስራ ........................................................................43

4.1.1.የስፌት ውጤቶችን መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ........................43
4.1.2.የስፌት ውጤቶችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መገኛ ቦታ ...........49
4.1.3.የስፌት ስራ አሰራር ሂደት እና ደረጃዎች .............................................50
4.1.3.1.የመቁረጥ ተግባር .....................................................................51
4.1.3.2.የማድረቅ ተግባር .....................................................................52
4.1.3.3.የመስራት ተግባር ....................................................................52
4.1.3.4.የማስጌጥ ተግባር .....................................................................53
4.1.4.የስፌት ስራ ውጤቶች ዓይነት የአሰራር ሂደትና አገልግሎት ..................54
4.1.4.1.ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች ..................................55
4.1.4.2.ለእርሻ ስራ የሚያገለግሉ የስፌት ቁሶች .....................................62
4.1.4.3.ለማህበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት የሚውሉ የስፌት ......................66
4.1.4.4.ለመጓጓዣነት አገልግሎት የሚውሉ የስፌት ቁሶች ......................73
4.1.5.የስፌት ቁሶች ጠቀሜታ ......................................................................76
4.1.6.በስፌት ስራ ላይ የባለሙያዎች ፆታዊ ተሳትፎ .....................................78
4.2.የድንጋይ ወፍጮ ስራ ........................................................................................80
4.2.1. የድንጋይ ወፍጮ መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ..........................80
4.2.2. የድንጋይ ወፍጮ ስራ አሰራር እና ደረጃዎች .........................................82
4.2.3.የድንጋይ ወፍጮ የአሰራር ሂደትና አገልግሎት .......................................84
4.2.4.የድንጋይ ወፍጮ ቁስ ጠቀሜታ ...........................................................87
4.2.5.የድንጋይ ወፍጮ ስራ ወቅታዊ ሁኔታ .....................................................88
4.2.6.በድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ የባለሙያዎች ፆታዊ ተሳትፎ ........................89
4.3.ባህላዊ የስፌት እና የድንጋይ ወፍጮ ሙያ ለመዳ ..........................................90
4.4.በቁሶቹና በሰው ልጅ መካከል ያለ ቁርኝነት .......................................................91
4.5.የባለሙያዎች የዕርስ በዕርስ ግንኙነት ...........................................................92
4.6.ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሙያው ባለቤቶች ያላቸው አመለካከት .....93
4.6.1.አወንታዊ አመለካከት ......................................................................94
4.6.2.አሉታዊ አመለካከት ..........................................................................94
4.7.በእጅ ስራዎችና በባለሙያዎቹ ላይ የሚታዩ ችግሮች .......................................95
4.7.1.የመስሪያ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ ..........................................................95

4.7.2.የባለሙያዎች መቀነስ ....................................................................96
4.7.3.የፋብሪካ ምርቶች መስፋፋት ..........................................................96
4.7.4.የመንግስት ድጋፍ አለመኖር ..........................................................97

5. ምዕራፍ አምስት
5.1.ማጠቃለያ .........................................................................................98
5.2.የይሁንታ ሃሳቦች .............................................................................100
ዋቢ ጽሁፎች ......................................................................................101
አባሪዎች
አባሪ 1 ለስፌት ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 2 ለድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 3 ለሀገር ሽማግሌዎችና ታሪክ አዋቂዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 4 ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች
አባሪ 5 ምልከታ የተደረገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች
አባሪ 6 የእጅ ስራ ቁሶቹ አገልግሎት በሰንጠረዥ
አባሪ 7 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር በሰንጠረዥ
አባሪ 8 የፎቶ ንባብ

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

አንድ ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ ማንነት ፣ ታሪክና ቋንቋ አለው። በነዚህ ዕሴቶቹ አማካኝነት የራሱን ህልውና ያስጠብቅበታል ፣ ማንነቱን ይገልፅበታል ፣ አመለካከቱን ያንፀባርቅበታል። ይህም በመሆኑ በየዘርፉ ያሉ ምሁራን የየኅብረተሰቡን አመለካከት ፣ እምነትና ማንነት ለማወቅ የጥናት ትኩረታቸው በየኅብረተሰቡ ባህል ፣ ታሪክና ቋንቋ ላይ ይሆናል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ኅብረተሰቦች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ኅብረተሰቦች የተለያየ ቋንቋ ፣ ባህል ፣ ማንነት እንዲሁም እምነት አላቸው። የኅብረተሰቦችን ባህላዊ ጉዳዮች የዘርፉ ምሁራን በተለያየ መንገድ አጥንተዋል። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች እና ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም የህትመት ሚዲያዎች የየኅብረተሰቡን ባህል በተለያየ መንገድ ለማሳየት ጥረት አድርገዋል።

የነገዴ[1] ኅብረተሰብ ልክ እንደማንኛውም ኅብረተሰብ የራሱ የሆኑ ባህላዊ እሴቶች አሉት። እነዚህ ባህላዊ ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ይገኛሉ። የተለያዩ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ተመራማሪዎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለነገዴ ኅብረተሰብ ጥናት አድርገዋል ።

ተመራማሪዎቹ ስለነገዴ ኅብረተሰብ ጥንት አመጣጥ ፣ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፣ የግጭት አፈታት ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ፣ አደን ፣ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ስለሚደርሱ መገለሎች እና ስለሀገረሰባዊ ዕምነቶች እንዳጠኑ ለማወቅ ተችሏል።

---

[1] ነገዴዎች በሌላው ኅብረተሰብ ዘንድ ወይጦ ተብለው እስካሁን ድረስ ቢጠሩም በዚህ ጥናት ላይ ግን መደበኛውን በወታደራዊው መንግስት ዘመን በተሰጣቸው ስያሜ እና ኅብረተሰቡ በሚስማማበት መጠሪያ ነገዴ የሚለውን ስያሜ ተጠቅሜያለሁ። ምክኒያቱም ወይጦ የሚለው መጠሪያ በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደ ስድብ እና ንቀት ስለሚቆጠር ነው።

ይህ ጥናት የተካሄደው በባህር ዳር ከተማ በ03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ በሚገኘው የነገዴ ኅብረተሰብ ላይ ነው፡፡ በነዚህ ቀበሌዎች ነዋሪ የሆኑት የነገዴ ኅብረተሰቦች ከሚታወቁባቸው የቁሳዊ ባህል ዘርፎች መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት በሀገረሰባዊ እጅ ስራ (folk crafts) ላይ ነው፡፡ የነገዴ ኅብረተሰብ ከሚያከናውናቸው የሀገረሰባዊ እጅ ስራ (folk crafts) ውጤቶች መካከል ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በባህላዊ የስፌት ስራ ውጤቶች እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራር እና አገልግሎት ላይ ነው፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳኝ ምክንያት ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለትምህርት ሶስት ዓመታት በቆየሁበት ጊዜ የነገዴ ኅብረተሰብ አባላት በብዛት የሚኖሩት እና በርካታ የእጅ ስራዎች የሚሰሩበት ቦታ መሆኑን ማየት በመቻሌ እና የእጅ ስራ ጥበብ ውጤቶች ይማርኩኝ ስለነበር ይህን እድል ባገኘሁበት ጊዜ ጥናቱን ለማጥናት ተነሳስቻለው፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ተማሪዎች በርከት ያሉ ስነቃል ነክ ጥናቶችን ሰርተዋል፡፡ እነዚህ የጥናት ስራዎች ርዕሰ ጉዳይ ባደረጉዋቸው የስነቃል አይነቶች መሰረት ሲከፋፈሉ ከፍተኛ ድርሻውን የሚይዘው ቃል ግጥም ሲሆን ቁሳዊ ባህል ደግሞ አነስተኛ ቁጥር እንዳለው (አብርሃም፣23) ገልጿል፡፡ በመሆኑም የነገዴ ኅብረተሰብን የእጅ ስራዎች በማጥናት በቁሳዊ ባህል ጥናት ያለውን ክፍተት ለመሙላትና የበኩሌን አስተዋፅኦ ለማድረግ ካለኝ ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡

ሌላው አነሳሽ ምክንያት ጥናቱ በሚካሄድበት ባህር ዳር ከተማ 03 ቀበሌ እና በ16 ቀበሌ በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ ሙያው በስፋት ከጥንት ጀምሮ ሲሰራበት ቢቆይም በአሁኑ ወቅት ሙያው የመሰራት መጠኑ እየተመናመነ መሆኑ ነው፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች አሰራርና የቁሳቁሶቹን አገልግሎት ማሳየት ነው፡፡ ይህን ዋና ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- ✓ የነገዴ ኅብረተሰብ የሚታወቅባቸውን የእጅ ስራ ውጤቶች መለየት

- ✓ የእጅ ስራ ውጤቶቹን የአሰራር ሂደት መግለፅ
- ✓ የእጅ ስራ ውጤቶቹን አገልግሎት መዘርዘር
- ✓ የእጅ ስራ ባለሙያዎችን የለመዳ ሂደት ማመላከት
- ✓ ከሙያው ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሙያው ባለቤቶች ያላቸውን አመለካከት እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቁርኝት ማሳየት
- ✓ የሙያው ባለቤቶች ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር ያላቸውን የእርስ በእርስ ግንኙነት መግለፅ
- ✓ የእጅ ስራዎቹን የለውጥና የቀጣይነት ሂደት ማሳየት

## 1.4.የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱ ዋነኛና ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ሂደት የሚከተሉት ጥያቄዎች የሚመለሱ ይሆናል ፡፡

- ✓ የነገዴ ኅብረተሰብ የእጅ ስራ ውጤቶች ምን ምንድን ናቸው?
- ✓ የእጅ ስራ ውጤቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እና ግብዓቶች ምንድን ናቸው?
- ✓ የጥሬ ቁሶቹ መገኛ ቦታዎች እና የቁሶቹ አገልግሎቶች ምን ይመስላሉ?
- ✓ የሙያ ባለቤቶቹ የለመዳ ሂደት ምን ይመስላል?
- ✓ ከሙያው ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሙያው ባለቤቶች ያላቸው አመለካከት በምን ይገለፃል?
- ✓ የሙያው ባለቤቶች ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር ያላቸው የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?
- ✓ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያላቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቁርኝት ምን ይመስላል?

## 1.5.የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ ሲጠናቀቅ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

- ✓ ስለኅብረተሰቡ የእጅ ስራ ውጤቶች አሰራርና አገልግሎት ለሌሎች ለማሳየት፡፡
- ✓ ኅብረተሰቡ የሚታወቅባቸው የእጅ ስራ ውጤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየቀነሰና እየጠፉ በመሆናቸው እንዲሁም የሚጠናው ሙያዊ ክህሎት በእይታና በልምድ

ከመተላለፉ በተጨማሪ የእጅ ስራ ውጤቶች አሰራር ሂደትና ጠቀሜታ በፅሁፍና በፎቶ ምስሎች ሰፍሮ መቀመጡ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

- ✓ በቁሳዊ ባህል ጥናት መስክ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ያገለግላል፡፡
- ✓ በቁሳዊ ባህል በተለይም በሀገረሰባዊ እጅ ስራ (folk crafts) ዙሪያ ጥናት ለሚሰሩ አጥኚዎች በተወሰነ ደረጃ የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

የነገዴ ኀብረተሰብ በጎጃምና በጎንደር አካባቢ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ባህር ዳር 03 ቀበሌ ፣ 16 ቀበሌ ፣ እንፍራዝ ፣ ደንቢያ ፣ ጎርጎራ ፣ አልዋ ፣ ደልጊ ፣ ሰይደብር ፣ ደንገል በር ፣ ቆንዝላ እና ወንድዬ የሰፈረ ኀብረተሰብ ነው፡፡ ሆኖም ጥናቱ ከቦታ አንፃር ትኩረት ያደረገው በባህር ዳር ከተማ በ03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ በሚገኘው የነገዴ ኀብረተሰብ ላይ ነው፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት ባህር ዳር ከተማ ከዚህ በፊት ለሶስት ዓመት በመቆየቴ እና የተመረጠው አካባቢ መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ከመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእጅ ስራ ውጤቶቹ በስፋት የሚሰሩት እና ኀብረተሰቡ የሚኖረው 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ ስለሆነ ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ደግሞ በቁሳዊ ባህል ስር በሚካተተው የሀገረሰባዊ እጅ ስራ ዘርፍ የሆኑት ባህላዊ የስፌት ውጤቶች እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርና አገልግሎት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በተመረጠው ኀብረተሰብ አካባቢ እነዚህ የእጅ ስራዎች ብቻ ስለሚከወኑ ነው፡፡

## 1.7.የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

### 1.7.1.የናሙና አመራረጥ ስልት

ፎክሎራዊ የሆኑ መረጃዎችን ከባህሉ ባለቤቶች እና ከሚጠናው ጥናት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር በቂ መረጃ ካላቸው ሰዎች መቀበል ብንችልም በተለይ በሙያው የሰለጠኑና በጉዳዩ ዙርያ ጥልቅ የሆነ መረጃ ያላቸው ሰዎች ለሚሰበሰበው ጥናት ተመራጭ ናቸው፡፡

ዓላማ ተኮር ናሙና (purposeful,purposive,judgment or judgmental sampling) ከወሳኝ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ

አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮች ይመርጣል፡፡ (ያለው፣132)

በዚህ ጥናት ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴን በመጠቀም ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ለመምረጥ ተችሏል፡፡ የናሙና አመራረጡን ሁሉን አሳታፊ ለማድረግ መረጃ አቀባዮችን በኢኮኖሚ ፣ በትምህርት ደረጃ ፣ በዕድሜ ፣ በፆታ እና በኅብረተሰቡ ዘንድ ባላቸው ተቀባይነት መረጃ አቀባዮችን ለማሳተፍ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሙያው ውስጥ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ፣ ለጥናቱ የሚሆነውን መረጃ ለመስጠት በጎ ፈቃደኝነታቸውን ያሳዩትን ፣ በሙያው ዕውቀት እና ስለሙያው የአገላለፃቸው ክህሎት ከሌሎች ተሽለው የተገኙ እና የእጅ ስራ ውጤቶችን ወዘተ …፡፡

የእጅ ስራ ውጤቶችን አገልግሎት በተመለከተ ከመግለፅ አንፃር በሙያው ውስጥና ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመረጃ አቀባይነት ተካተዋል፡፡

## 1.7.2.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የዚህን ጥናት ዓላማ ከግብ ለማድረስ እና የምርምር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በካልዓይ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ ስራዎችና ጥናታዊ ፅሁፎች ከቤተ መጻህፍት ፣ እንዲሁም ከኢንተርኔት ታማኝ ምንጮች መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ምልከታ ፣ ቃለ መጠይቅ ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ ከሙያው ባለቤቶች መረጃዎች ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

### 1.7.2.1.ምልከታ

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ በዋናነት የምልከታ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል ፡፡ አንድን መረጃ ለመሰብሰብ መረጃው በሚገኝበት ቦታ ተገኝቶ እየተመለከቱ እየሰሙ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም ባህር ዳር ከተማ 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ በአካል በመገኘት የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎችን የአሰራር ሂደታቸውን በማየት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሶስት ዓይነት መቼቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነሱም ተፈጥሯዊ (Natural setting)፣ቅንብር ተፈጥሯዊ (Inducede Natural Setting) እና ሰው ሰራሽ (Artificial setting) እንደሆኑ (ፈቃደ፣122-124) ይገልፃል፡፡ ተፈጥሮአዊ መቼት የሚባለው የፎክሎር አይነቱ በባህል ወይም በተለምዶ የሚከወንበት ቦታና ጊዜ ሲሆን በእነዚህ ቦታዎች ላይ መስከኛው እየተገኘ በሚሰበስብበት ጊዜ የእጅ ስራውን በተፈጥሮአዊ መቼቱ ከነሙሉ ክዋኔው እየታየ የተሟላ መረጃ ለመያዝ ያስችላል ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የእጅ ስራ ውጤቶቹን አሰራርና አገልግሎት በአካል በመገኘት ምልከታ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል መስከኛው የስነቃል አይነቱ በተፈጥሮአዊ መቼቱ ሲከወን ባልተገኘበት ጊዜ ወይም አጋጣሚ ወይም ደግሞ የስነቃል አይነቱ ከክዋኔ ውጪ ሆኖ እየተረሳ ፣ እየተለወጠ በሚሄድበት ሁኔታ ያለን ስነቃላዊ አይነት ቅርስ የማስቀረትና የመሰነድ አስፈላጊነት ጎልቶ የሚታይበት ሆኖ ሲፈጠር መረጃ የሚሰበሰብበት መቼት ሰው ሰራሽ (አርቲፊሻል) መቼት ይሆናል፡፡ ሰው ሰራሽ መቼት ባንድ በኩል ከዚህ በፊት ይከወን የነበረ ዛሬ ግን የሌለን የስነቃል አይነት ክዋኔውን እያስታወሱና እያስመሰሉ የሚከውኑበት መቼት ሲሆን በሌላ በኩል አንድን የስነቃል አይነት ከአውድ ውጪ ማንኛውንም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ቦታና ጊዜ መስከኛው እየጠየቀ ስነ ቃሉን የሚሰበስብበት መቼት ነው (ፈቃደ፣123) ይላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት ይሰሩ የነበሩ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የማይሰሩ የእጅ ስራ ውጤቶችን አሰራርና አገልግሎት ለማወቅ ይህን የመቼት ዓይነት መስከኛው ተጠቅሟል፡፡

በመስክ ቆይታዬም ለጥናቱ የሚሆኑትን ተፈጥሮአዊ እና አርቲፊሻል መቼቶች በመጠቀም መረጃውን ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ፡፡ መረጃዎቹንም በማስታወሻ ፣ በመቅረፀ ድምፅ ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ እንደ መረጃ ሰጪዎች ፈቃድ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 1.7.2.2.ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያስችል ዘንድ ስራ ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ሲሆን የነገዴ ኅብረተሰብ በብዛት ባህላዊ የእጅ ስራዎችን የሚሰሩት 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ በመሄድ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ተሰብስበዋል ፡፡

ይህም የሆነበት ምክንያት ቦታው ድረስ በመገኘት መደበኛ ቃለ መጠይቅ የተደረገ ሲሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ደግሞ ኢመደበኛም በሆነ ቃለ መጠይቅ መረጃውን በተገቢው መንገድ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ አስራ ስድስት ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና አስራ አምስት ንዑስ መረጃ አቀባዮች በድምሩ ሰላሳ አንድ ሰዎች ተመርጠው በቃለመጠይቁ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ መረጃዎቹንም እንደ መረጃ ሰጪዎች ፈቃድ በማስታወሻ ደብተር ፣ በመቅረፀ ድምፅ ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ለመሰብሰብ  ተችሏል፡፡

## 1.7.2.3.ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በምልከታና በቃለ መጠይቅና የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ይበልጥ ለመረዳትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማካሄድ ተሞክሯል፡፡ በቡድን ውይይቱ ላይ አስራ ሶስት መረጃ አቀባዮች ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ቁጥር ከፍ በማድረግ ውይይቱን ለማካሄድ ተችሏል፡፡ በዚህ ዘዴ መረጃዎችን በማስታወሻ ፣ በመቅረፀ ድምፅ ፣ በፎቶ ካሜራና በቪዲዮ ካሜራ በመጠቀም ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

በቡድን ውይይቱ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች የተነሱ ሲሆን በተለይ ደግሞ በቁሶቹ አጠቃቀም ረገድ ያሉ ለውጦች ፣ ስለኅብረተሰብ መነሻ ታሪክ ፣ ሃይማኖት ፣ መተዳደሪያ እና ስለቁሶቹ አገልግሎት በተመለከተ ውይይት ተደርጓል ፤ መረጃዎችም ተሰብስበዋል፡፡

## 1.7.3.የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን ዓላማ ከተፈለገበት ግብ ይደርስ ዘንድ ጥናቱ የተካሄደው ገላጭ (descriptive) በሚባለው የጥናትና ምርምር ስልት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በዓይነት በዓይነታቸው በመመደብ በገለፃ መልክ አብራርቶ ለማቅረብ አመቺ ስለሆነ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ገላጭ የምርምር ስልት የተመረጠበት ምክንያት ኅብረተሰቡ ባህላዊ የእጅ ስራዎቹን እንዴት እንደሚሰራቸው ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ እና ከቁሳዊ ባህል መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ ስለሚካተት ነው፡፡

ቁሶችን መሰረት ያደረገ ትንተና ሶስት ደረጃዎችን ቢያልፍ የተሻለ መሆኑን Prown ይመክራል፡፡ " Having progressed from the object it self In **description** to the

interaction between object and perceiver in **deduction**,the analysis now move completely to the mind of the perceiver to **spectulation.** " (Prown፤9) ፡፡

እነዚህ ደረጃዎች በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ሊኖር የሚችለውን አድሏዊነት ለመቀነስ እና በተቻለ መጠን ግልፅ ለማድረግ እንደሚጠቅሙ ገልጿል፡፡ ደረጃዎቹም ገለፃ (Descriptive) ፤ ትርጓሜ (Deduction) ፤ ጥቆማ (Spectualation) ናቸው፡፡

ገለፃ (Descriptive) የትንተና ዘዴ የቁሱን ገፅታ የሚያሳይ ሲሆን ቁሱን ተመልክተን ስለቁሱ አጠቃላይ ገፅታ የምንገፅበት ነው፡፡ እኛ በጥናታችን ወቅት ያየነውን ነገር ላላዩ ሰዎች እንደማሳየት ያህል የሚቆጠር የመተንተኛ ዘዴ ነው፡፡ በገለፃው ጊዜ እጅግ የተንዛዛ ገለፃ ከማድረግ ይልቅ ገለፃው የተቆጠበ እንዲሆን Prown ይመክራል ፡፡ " descriptive is restricted to what can be observed in the object it self,that is,to internal evidence… " (Prown፤6-7)፡፡

ትርጓሜ (deduction) ከገለፃው በማስከተል የምንጠቀምበት የመተንተኛ ሂደት ነው፡፡ በዚህ የትንተና ሂደት ውስጥ በቁሱና በቁሱ ባለቤት ኅብረተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት የምናይበት ሲሆን ለምናየውም ነገር ትርጓሜ የምንሰጥበት ነው፡፡

ጥቆማ (speculation) የገለፃና የትርጓሜ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ የምንሰራው ስራ ሲሆን በዚህ ክፍል አጥኚው የራሱን ግንዛቤ ከቀደምት ትውሮች ጋር በማገናዘብ ትንታኔ የሚሰጥበት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሶስት የመተንተኛ ደረጃዎች ለዚህ ጥናት መተንተኛነት እንደ አስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

## 1.7.4.ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

አንድን የምርምር ስራ ለመስራት በመጀመሪያ የተቀናጀ ዕቅድ ያስፈልጋል፡፡ በመስክ ስራ ላይ የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሙን ስለሚችሉ እነዚያ ችግሮች የምንፈታበትን መንገድ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተደረጉ ዝግጅቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ስለነገዴ ኅብረተሰብ ቋንቋ ፤ ታሪክ ፤ ባህል እና የተፈጥሮ ሀብቶች የተፃፉ ዕሁፎችን ፤ ጥናታዊ ፅሁፎችን ፤ መፅሃፎችን እና መፅሄቶችን እንዲሁም ከኢንተርኔት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሞክሬያለሁ፡፡

በነገዴ ኅብረተሰብ ላይ የተሰሩ ስራዎችን በመዳሰስ አስፈላጊ መረጃዎችን ማጠናከር እና የመረጃ ምንጮችን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አካባቢውን እና ኅብረተሰቡን እንዲሁም ሙያውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ለመወያየት ጥረት ተደርጓል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱን ከተፈለገው ግብ ለማድረስ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጋዥ የሚሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የቪዲዮ ካሜራ ፣ የፎቶ ካሜራ ፣ መቅረፀ ድምፅ ፣ ባትሪ ድንጋይ እና የተለያዩ የፅህፈት መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ወደ ሚሰራበት ቦታ የተደረገ ጉዞና የመስክ ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከመስክ መረጃ የምሰበስብበት ጊዜ እየተቃረበ በመሆኑ የምልከታ ቼክ ሊስት ፣ ለቃለ መጠይቅና ለተተኳሪ ቡድን ውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉ የቪዲዮ ካሜራ ፣ የፎቶ ካሜራና መቅረፀ ድምፅ እንዲሁም የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያዎችን በማዘጋጀት መጋቢት 9 ቀን 2011 ዓ.ም የመስክ ጉዞዬን አደረኩ፡፡

መጋቢት 9 ቀን 2011 ዓ.ም ሰኞ ዕለት ከአዲስ አበባ 563 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው ባህር ዳር ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡ ከአድካሚ ጉዞ በኋላ ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ ባህር ዳር ከተማ ደረስኩ፡፡ ከዚህ በፊት በባህር ዳር ከተማ ለትምህርት ለሶስት ዓመታት ስለቆየሁ ለከተማዋ እንግዳ አይደለሁም፡፡ ባህር ዳር ከመድረሴ በፊት የሚጠናው የነገዴ ኅብረተሰብ መኖሪያ አካባቢ 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ የሚገኙ ጓደኞቼ ጋር በመደወል መረጃ ሰጪዎችን አዘጋጅተው እንዲጠብቁኝ አድርጌ ስለነበር መረጃ አቀባዮቼን ለማግኘትና መረጃ ለመሰብሰብ ብዙም አልተቸገርኩም ነበር፡፡

በማግስቱ መጋቢት10 ቀን 2011 ዓ.ም ወደ ሚጠናው ኅብረተሰብ መኖሪያ 16 ቀበሌ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ የመጣሁበትን ጉዳይ እና የጥናቱን ዓላማ በአግባቡ በማስረዳት በኅብረተሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች እና በፎቶና በቪዲዮ የተቀመጡ መረጃዎችን ለማግኘት ብሞክርም ምንም ዓይነት የተደራጀ መረጃ እንደሌለ የክፍሉ ኃላፊ ገለጹልኝ፡፡ ነገር ግን ስለ ኅብረተሰቡ የሚያውቁትን አንዳንድ መረጃዎች በቃል ከሰጡኝ በኋላ በምስጋና ተለያየን፡፡

መጋቢት 11 ቀን 2011 ዓ.ም ጉዞዬን 13 ቀበሌ ወደ ሚገኘው አማራ ቴሌቪዥን አደረኩ፡፡ የመጣሁበትን ጉዳይ እና የጥናቱን ዓላማ ለቴሌቪዥኑ ጣቢያ የህዝብ ግንኙነት ተጠሪ አቶ የሺ

ሀሳብ አበራ ካስረዳሁ በኋላ በጣቢያው የሚገኙ የፎቶና የቪዲዮ መረጃዎችን ለማየት ችያለሁ። ለተደረገልኝ ትብብር አመስግኜ የአማራ ቴሌቪዥን ጣቢያ ለቅቄ ወጣሁ።

በማስከተል የእጅ ስራ ባለሙያዎቹ በባህር ዳር ከተማ 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ እንደሚገኙ ቀድሞ የተለየ ስለሆነ ቀጣዩ ስራ በሙያው ውስጥ ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ፣ ለጥናቱ የሚሆነውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ ፣ በሙያው እውቀትና ስለሙያው ለመግለፅ ከሌሎች የተሻለ ችሎታ ያላቸው መረጃ አቀባዮችን እንዲሁም የእጅ ስራ ውጤቶችን እዛው ነዋሪ ከሆኑ ጓደኞቼ ጋር በመሆን የመለየት ስራ ሰራን።

ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የሰበሰብኩት ባለሙያዎቹ በሚኖሩበት መንደር፣ቁሶቹን በሚሰሩበት ቦታና በሚሸጡበት የገበያ ቦታ በአካል በመገኘት ነው። የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችን እስከ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም ከሰበሰብኩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ወደ ፍላሽ ገልብጫለሁ። በመጨረሻም መረጃዎቹን በማደራጀት ትንተና ተደርጎባቸዋል።

## 1.8.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሳቦች

### 1.8.1.ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚው ለሚጠናበት ቦታ ባህር ዳር ከተማ እንግዳ ባይሆንም በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የተለየና እንግዳ ከመሆኑ በተጨማሪ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ የሆኑበት የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ የመረጃ አቀባዮች መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አጥኚው ለራሱ ጥቅም እንጂ ለነሱ ምንም አይነት ጥቅም እንደማይሰጣቸው ማሰብ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ ተጠኚው ኅብረተሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር እምብዛም ቀረቤታ ስለሌለው መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን ፤ መረጃ ለመስጠት የገንዘብ ጥያቄ ማቅረብ። ባለሙያዎቹ የእጅ ስራ ውጤቶቻቸው በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ እንዲነሱ አለመፍቀድ በመስክ ቆይታ ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው።

## 1.8.2.የተወሰዱ መፍትሔዎች

ከሚጠናው ኀብረተሰብ ጋር ቀረቤታ በመፍጠር እና ጥናቱ ቢጠና ሊኖረው የሚችለውን ዕውነተኛ ጥቅም ሳያጋንኑ በማስረዳት መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም በአካባቢው ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች በማግኘት መረጃ ሰጪዎችን እንዲያግባቡልኝ እና እንዲያስተባብሩልኝ በመጠየቅ መረጃውን በቀላሉ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

የነገዴ ኀብረተሰብ አባላት በብዛት አነስተኛ ገቢ የሚያገኙ ስለሆኑ መረጃ በሰጡ ቁጥር ክፍያ መጠየቃቸው ከፍተኛው ችግር ቢሆንም ተማሪ መሆኔን በማስረዳት መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑት ሰዎች እና ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች በማላመን መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

## 1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ አምስት ምዕራፎችን ያካተተ ሲሆን በምዕራፍ አንድ ስምንት ንዑሳን ርዕሶች ተዳስሰዋል ። የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴዎች ፣ ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት እና የመስክ ክንውን ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሳቦች ናቸው።

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናትን ማለትም ጽንሰ ሐሳባዊ ቅኝት እና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ እንዲሁም የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ያካተተ ነው። ምዕራፍ ሶስት ደግሞ ጥናቱ የሚካሄድበት አካባቢያዊ ዳራ ፣ የማህበረሰቡ ቋንቋ ፣ ስያሜ ፣ ሃይማኖት ፣ ጥንተ አመጣጥ እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የተዳሰሱበት ነው።

በምዕራፍ አራት የነገዴ ኀብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎች ሂደትና ጠቀሜታ ለማሳየት ተሞክሯል። የመጨረሻው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ ሲሆን  ዋቢ ጽሁፎች እና አባሪዎች ተያይዘው ቀርበዋል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ጽንሰ ሐሳቦች እና ንድፈ ሐሳቦች እንዲሁም ከሚጠናው ኅብረተሰብ እና ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጥናት ስራዎች ከጥናቱ ርዕስ ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት የተዳሰሱበት ነው፡፡

## 2.1.ጽንሰ ሐሳባዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል በሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን ያነሷቸው ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ ጉዳዮቹም ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ለመተንተን ማገናዘቢያ በመሆን አገልግለዋል፡፡

አንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ወግና ልማዶች ይኖራሉ፡፡ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ፍክሎሮች በዘውግ በመከፋፈል ማጥናት አለበት፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች ለማጥናት አዳጋች ስለሚሆን ነው፡፡

የተለያዩ ምሁራን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ካላቸው ባህሪያት በመነሳት በተለያየ መልኩ ይከፋፍሏቸዋል፡፡ ፎክሎርን ስነ ቃል ፣ ቁሳዊ ባህል ፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚሉ አራት ዘውጎች (Dorson ፣1972) ከፍሏቸዋል፡፡ ፈቃደ አዘዘም የ Dorson ሀሳብ በመጋራት አራቱ የጥናት መስኮች በፎክሎር ውስጥ እንደሚካተቱ ገልጿል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ፎክሎርን በሶስት መክፈል ይቻላል፡፡ እነሱም ቃላዊ (verbal) ፣ ቁሳዊ (material) እና ማህበረሰባዊ ልማድ (customary) ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ዘውጎች የተለያዩ ልማዶችን (lore) በውስጣቸው የያዙ ናቸው (Sims and Stephens፣12)፡፡

ፎክሎርን በዘውግ ለመከፋፈል የተደረጉ የተለያዩ ጥረቶች ቢኖሩም በሁሉም የመክፈያ መንገዶች ውስጥ ወደሚገኘው  እና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ወደሆነው  ቁሳዊ ባህል ምንነት ማብራሪያ እንሄዳለን፡፡

## 2.1.1.ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል ሰዎች በአኗኗር ስልታቸው ውስጥ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸውን እንዲረዳ በማሰብ በአካባቢያቸው ወይም ከሚኖሩበት ስፍራ የሚያገኟቸውን ቁሶች በግብዓትነት ተጠቅመው እንደ እውቀታቸው ፣ ማንነታቸው ፣ ፍልስፍናቸው እና እምነታቸው እንዲሁም የኑሯቸውን ሁኔታ እንዲያንፀባርቁ አድርገው የሚሰሯቸውን ቁሶች የሚገልፁ ናቸው፡፡ ይህንን አስመልክቶ Jones እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

> Material culture is an abbrevation for the material manifestation of culture i.e. objects made by human beings. The tangible things that people make, later, use, and to which they often attribute. Meanings and significance beyond utility practically, artifacts relate to human values concerns needs and desired both past and present they may reflect the sprite of an age, the belief of the society or a sub group or the experience and individual' (Jones ፣9)

ከዚህ በመነሳት ቁሳዊ ባህል የምንላቸው የሰው ልጅ ውስጡ በፈለገው መንገድ እውቀቱን ተጠቅሞ አሻራውን ያሳረፈባቸው የጥበበ ዕድ ውጤቶችን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ ጥበቡን ያሳረፈባቸው ቁሶች በዕለት ተዕለት ህይወቱ ውስጥ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ለምግብ ማብሰያና መመገቢያ የሚሰራቸውን ፣ ለመጠለያነት የሚገለገልባቸውን እራሱን ከተለያዩ ጠላቶች እንዲሁም አደጋዎች የሚከላከልባቸውን ፣ የምግብ አዘገጃጀቶችን ፣ ካለው የአየር ንብረት ጋር በተያያዘ የሚገለገልባቸውን አልባሳት ከትንሽ ነገር ተነስቶ ትልቅ አስፈላጊ መገልገያዎች ድረስ አጠቃሎ የሚይዝ ሲሆን እነዚህ ቁሶችም ከሚሰጡት ጠቀሜታና አገልግሎት በተጨማሪ በቁሶቹ ምን ሊገልፅ እንደፈለገ ቁሶቹ በተሰሩበት ጊዜም የነበረው አመለካከት ቁሱን የሰሩትንም የኅብረተሰብ ክፍሎች እሴቶቻቸውን የዘመን መንፈስ እና የህይወት ልምድ ተሞክሮ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ፈቃደ Dorson ንን ጠቅሶ እንዲህ ብሎታል፡፡

> ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች ፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ

ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር ፣ የቅመማ አቀማመም ብልሀትን ፣ የልብስ ፣ የቤት ፣ የአጥር ወዘተ አሰራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸው መሳሪያዎችንና ሌሎችን ተመሳሳይ ጉዳዮች ያጠናል ማለት ነው። (ፈቃደ፣15)

ሌላው የፎክሎር ተመራማሪ ሰለሞን ከፈቃደ ጋር ተያያዥነት ያለው ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርቧል።

ቁሳዊ ባህል አንዱ የፎክሎር ዘርፍ ነው። በዚህ ዘርፍ ውስጥም የሚካተቱ በዐይን የሚታዩ ፣ በእጅ የሚዳሰሱና በምላስ የሚቀመሱ ተጨባጭ የፎክሎር አይነቶች ናቸው። እነዚህ የፎክሎር አይነቶች ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚያገኛቸውን ግብዓቶች በራሱ እውቀት የፈጠራቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች ፣ የራሱን የአሰራር ስልትና ዕውቀት መሰረት በማድረግ የሚሰራቸው ቁሶች ናቸው። (ሰለሞን፣248)

ይህም ማለት ቁሳዊ ባህሎች የሚሰሩት በእጅ በመሆኑ ሊታዩ ሊዳሰሱና በሰዎች የእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ ሊያገለግሉ የሚችሉ ቁሶች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ሰዎች በአካባቢያችን በሚገኙ ተፈጥሮአዊ ግብዓቶች ወይም ጥሬ ቁሶች አማካኝነት ባላቸው ዕውቀት ሊያበጇቸው የሚችሉ ናቸው።

ከዚህ በመነሳት Jones ፣ ፈቃደ እና ሰለሞን ቁሳዊ ባህል የቁሶቹን ምንነት ፣ የተሰሩበትን ዘዴ እና አገልግሎት የሚመረምር መሆኑን ገልፀዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ Prown ቁሳዊ ባህልን አስመልክቶ እንደሚከተለው ይገልፃል። " *Material culture is the study through artifacts of the belifes, values, ideas, attitudes and assumptions of particular community or society at a given time.* " (Prown ፣*1)* ። ቁሳዊ ባህል በቁሶቹ አማካኝነት የአንድን ኅብረተሰብ እምነት ፣ ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ አመለካከት እና ግምት ለማጥናት የሚያስችል ዘርፍ መሆኑን ይገልፃል። ከዚህ በተጨማሪም ቁሶች በተሰሩበት ዘመን በሰዎች ረቂቅ ሃሳብ ሊበጁ እንደሚችሉ ቁልጭ አድርጎ በማስረጃ የሚያቀርብ ነው ።

ሌላው ተመራማሪ Deetz ቁሳዊ ባህልን አስመልክቶ እንደሚከተለው ያብራራል " material culture is that sector of our physical environment that we modify through

culturally determined behavior. " (Deetz፣1996) ፡፡ ቁሳዊ ባህል በአካባቢያችን በሚገኙ ቁስ አካላት ባህላዊ መሰረቱን ጠብቀን የምናበጀው ቁስ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሀሳቦች ከፊሎች ቁሳዊ ባህል ማለት የቁሶች ስብስብ ብለው የሚያብራሩት ሲሆን  ሌሎች ደግሞ ቁሶች የሚጠኑበት የጥናት ዘርፍ እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ጥናት የቁሶቹን ስብስብ በዓይነት በማጥናት የኅብረተሰቡን ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድና ፍልስፍና የሚያሳይ ነው፡፡

## 2.1.2.የቁሳዊ ባህል ባህርያት

ቁሳዊ ባህል ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች የሚለይበት ባህሪያት አሉት፡፡ ባህርያቱንም ከተለያዩ ምሁራን ስራዎች ውስጥ በማውጣት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል፡፡

### 2.1.2.1.ተጨባጭነት

Sims and Stephens የቁሳዊ ባህል ባህርያትን አስመልክተው ሲገልፁ " material culture has in common that it is tangible can be touched seen, eaten or lived in." (Sims and Stephens፣13)  በማለት ይገልፃል፡፡ ይህም ማለት ቁሳዊ ባህል በእጅ ሊዳሰስ ፣ ሊታይ እና የተለያዩ መደበኛ አገልግሎቶችን ልናከናውንበት የሚያስችለን ነው፡፡

ቁሳዊ ባህል በእለት ተእለት ኑሯችን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ አካላዊ ገፅታ ያለው ልክ እንደ ማንኛውም ቁስ ልንገለገልበት የሚያስችለን አንዱ የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ለምሳሌ ቁሱን ለተለያዩ አገልግሎቶች በቤታችን ውስጥ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ለመመገቢያነት ፣ ለመጠጫነት እና ለማስቀመጫነት እንዲሁም ለተለያዩ አገልግሎቶች ቁሶችን በእጃን እየነካን በዓይናችን እያየን ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡፡ ነገር ግን በቤታችን ውስጥ ያሉትን ባህላዊ የሆኑትን እንጂ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን አያካትትም፡፡

### 2.1.2.2.ተፈጥሯዊነት

Oring የቁሳዊ ባህል ባህሪያትን አስመልክቶ ሲገልፅ " material cultureare emerged from an adaption to the natural environment and the creation of human environment. " (Oring፣2-10) ይላል፡፡ ይህም ማለት ቁሳዊ ባህል በአካባቢው ካሉ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ጋር

ሊስማማ የሚችል ከመሆኑም በላይ ሰዎች ቁሳዊ ባህልን ለመስራት በአካባቢያቸው ከሚያገኙት የተፈጥሮ ሀብቶች ሊሰሯቸው እንደሚችሉ ገልጿል፡፡

አንድ ቁስ ቁሳዊ ባህል ሊባል የሚችለው ተፈጥሮአዊ በሆኑ ጥሬ ቁሶች ሲሰራ ወይም ደግሞ ባህላዊ በሆኑ መሳሪያዎች ሲበጅ ሲሆን ይህ ባህሪው ደግሞ ተፈጥሮአዊ ሊያሰኘው ይችላል፡፡

### 2.1.2.3.ዘመን ተሻጋሪነት

Dorson የቁሳዊ ባህል ባህሪያት ዘመን ተሻጋሪነትን አስመልክቶእንዲህ በማለት ገልጿል ፡፡ " material cultures respondents to techniques, skills, recipes and formulas transmitted across the generation and subject to the same force of conservative tradition and individual variation as verbal art " (Dorson፣2)

በዚህ ሀሳብ መሰረት ቁሳዊ ባህል ዘመን ተሻጋሪ ቁሶች ብቻ ሳይሆኑ የባለሙያዎቹ የሙያ ክህሎት ፣ የአሰራር ሂደትና ስልት ባህልን መሰረት አድርገው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.3. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

ቁሳዊ ባህል ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች አንዱ ሲሆን በስሩም ሀገረሰባዊ እጅ ስራ (folk crafts) ፣ ሀገረሰባዊ ስዕል (folk arts) ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና (folk architecture) ፣ ሀገረሰባዊ ልብስ (folk custom) እና ሀገረሰባዊ ምግብ አሰራር (folk cookery) የሚባሉ አምስት ዘርፎችና እንደሚያቅፍ ሰለሞን Dorson ን ዋቢ በማድረግ አስፍሯል (ሰለሞን፣250) ፡፡

በቁሳዊ ባህል ስር ሊጠኑ የሚችሉ አምስት ዘርፎች ቢኖሩም የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው ግን ሀገረሰባዊ እጅ ስራ (folk crafts) ስር የሚገኘው የስፌት ስራ ውጤቶች እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን መመልከት ነው ፡፡

### 2.1.3.1 ሀገረሰባዊ እጅ ስራ

ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ሰዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሶችን በግብዓትነት ተጠቅመው የየራሳቸውን ዕውቀት በመጨመር ያሉበት ኅብረተሰብ ባህል ፣ እምነት እና አመለካከት ወዘተ በመጨመር እራሳቸውን እንዲያንፀባርቁ አድርገው የሚሰሯቸውን ቁሶች ይመለከታል፡፡

ሀገረሰባዊ እጅ ስራ አብዛኛውን ጊዜ በእጅ እና ባህላዊ በሆኑ መሳሪያዎች የሚሰሩ ቁሶች ናቸው፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ ሰለሞን " በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ከሚታወቁ ሀገረሰባዊ እጅ ስራዎች መካከል የሽመና ፣ የሸክላ ስራ ፣ የስፌት ስራ ፣ የብረት ስራ ፣ የቀርከሃ ስራ ፣ የእንጨት ስራ ፣ የቆዳ ስራ እና የቀንድ ስራ የመሳሰሉት ይገኛሉ " ሲል (ሰለሞን፣251) ገልጿል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ ቁሶች ከተሰሩ በኋላ ሰዎች በተለያየ ግልጋሎትነት እየተጠቀሙባቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩትን ቁሶችን ብቻ ሳይሆን አሁንም እየተሰሩ ያሉትን ያጠቃልላል ፡፡ ይህንን በማስመልከት oring እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡ " The Designation folk objects is not restricted to objects only from the past new folk objects are continally emerging " (oring፣216) ፡፡

Oring አያይዞም ሀገረሰባዊ እጅ ስራ የሚባሉት ምንነታቸው ሊታወቅ የሚችሉትንና ሀገረሰባዊ ካልሆኑት የእጅ ስራዎች ሊለዩ የሚችሉትን በዕድሜ መርዘምና ማጠር አለመሆኑን የገለፀ ሲሆን ከዚህም ባለፈ የሚገልፁትን የሰዎችን የፈጠራ ችሎታ የሚያንፀባርቁትን የኅብረተሰቡን ወግ ፣ ልማድ ፣ ባህል ጠብቀው እና አኑረው የተሰሩትን በልማድ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቀጣይነት የሚተላለፉ ባህላዊ ቁሶችን የሚመለከት ነው ብሎ ይገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ Dorson ቁሶችን በሀገረሰባዊ እጅ ስራ ውስጥ ለመመደብ የሚያስችሉ አጠቃላይ መመዘኛዎችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

> የእጅ ስራ ውጤቶች ከቆዩበት ዘመን ይልቅ የተሰሩበት ግብዓት ሀገረሰባዊ ያስብለዋል፡፡ ዕደ ጥበብ ናቸው ተብለው የምንጠቀምባቸው ቁሶች የሚኖራቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅም በመመልከት እንጂ የማህበረሰቡ አብዛኛው አባላት መደበኛ ትምህርት ወይም ቀጥ ያላለና መስመሩን ያልጠበቀ ሙያዊ ተስተላልፎ መኖር የለበትም፡፡ ሙያዊ ተስተላልፎውም በቀጣይነት ከትውልድ ወደ ትውልድ በልማድ እየተላለፈ የመጣ መሆን አለበት፡፡ የእጅ ሙያ ጥበብ ቀለል ባለ መልኩ በግለሰብ የንድፍ ጥበብ የሚሰሩ ውጤቶችን እንጂ በማሽን የሚሰሩትን አያካትትም፡፡ (Dorson፣233)

ከዚህ በመነሳት በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የሚባሉት የኅብረተሰቡን ማንነትና ምንነት የሚገልፁ የሰዎችን የመፍጠር አቅም የሚያንፀባርቁትን የኅብረተሰቡን ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድ

እና ሀይማኖት ጠብቀውና አኑረው የተሰሩትን የመተላለፊያ መንገዳቸውም ከመደበኛው ውጪ የሆኑትን ካለፈው ትውልድ በተለይም ሰዎች በቤተሰቦቻቸው ተሰርተው የተቀመጡትን እንዲሁም የሚሰሩትን የሚመለከት ነው፡፡

## 2.1.4.የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት

የሰው ልጅ ለህይወት ውጣ ውረዱ የሚሆኑ የተለያዩ ቁሶችን በመስራት ብዙ ዘመናትን አሳልፏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በርካታ የኢንዱስትሪ ምርቶች ቢስፋፉም ሰዎች በአካባቢያቸው በሚገኙ ጥሬ ቁሶች አማካኝነት የተለያዩ ቁሶችን ከመስራት አልቦዘኑም፡፡ በእጅ ስራ ባለሙያዎች የሚሰሩት እነዚህ ቁሶች ከዕለት ተዕለት ግልጋሎትነት ባለፈ የአንድ ዘመን የጥበብ አሻራ በማሳየት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዎ አላቸው፡፡ የቁሳዊ ባህል ጥናት የአንድን ኅብረተሰብ ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድና ማንነት ሊያሳይ ይችላል፡፡

ይህን አስመልክቶ Glassie እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡

> ሰዎች በቁሶች ላይ በውስጣቸው ያለውን ስሜት ትርጉምና ዋጋ እንዲኖረው በማድረግ የሚገልጹበት እንዲሁም ባህልን መነሻ በማደረግ የሚሰሩት ውጤቶች ቁሳዊ ባህል ይባላሉ፡፡ እነዚህ ቁሶች ከቁስነታቸው ባለፈ የአንድን ቡድን ስብስብ የእውቀት ፣ የድርጊት እና የአስተሳሰብ መገለጫ ናቸው ፡፡ በዚህም ምክኒያት ቁሳዊ ባህል በሚጠናበት ጊዜ ይህ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ቁሳዊ ባህል ማንነትን የመግለፅ አቅም እንዳለውና የኅብረተሰቡን እምነትና ፍልስፍና በቁሳዊ ባህል አማካኝነት እንደሚገለፅ በጥናት ወረቀትም እነዚህንም ጨምሮ ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡ (Glassie፣42)

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ቁሳዊ ባህል ተጨባጭ ለሆኑና የሰው ልጅ ባህልን መሰረት አድርጎ ለዕለት ተዕለት ኑሮው ማከናወኛ የሚሰራቸውን ቁሶች የሚመለከት ከመሆኑም በላይ የቁሶቹ ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅን አስተሳሰብና ፍልስፍና በቁሶቹ አማካኝነት መመርመር የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም Prown የቁሳዊ ባህል ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ አስመልክቶ ሲገልፅ " the fundamental purpose of the study of material culture is the quest for beliefs

systems, the patterns of belief of a particular group of people in a certain time and place. " (6) ይላል።

ከዚህ የምንረዳው የቁሳዊ ባህል ጥናት ዋና ጉዳይ በአንድ ኅብረተሰብ ባህል ውስጥ ያለ እምነት ፣ ወግ እና ታሪክ መፈለግና መመርመር መሆኑን ነው።

በተመሳሳይም Dorson ከ Glassie ጋር ሊዛመድ የሚችል ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርቧል።

> Folk material culture can provide evidence of the every day past and supply the visible proof of changing belifes and customs. Such studies help us understand creative impulse and interpret how personality is conveyed through objects and technical activities. (Dorson፣21)

ከጽሁፉ የምንረዳው የቁሳዊ ባህል ጥናት የሰዎችን ባህል ፣ ወግ ፣ ልማድና እምነት በማስረጃ አስደግፎ የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን ለማጥናት ስናስብ ቁሶቹን ያበጁ ባለሙያዎችን በጥምረት መመርመር እንደሚገባና ቁሳዊ የፈጠራ ጥበቡ በባለሙያዎች አህምሮ ውስጥ ተሸሽጎ የሚገኘውን ማንነት መመርመር ጠቀሜታ አለው። የሰው ልጅን የመፍጠር ችሎታ ፣ ማንነቱን የመግለፅ አቅም እና ሙያዊ ተግባራትን በቁሶቹ አማካኝነት ሊያንፀባርቅ እንደሚችል ጭምር መረዳት ያስችለናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ "ቁሳዊ ባህል የአንድን ኅብረተሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት ፣ ተግባቦት እንዲሁም ንድፍ ወይም ቅርፅ በቀላሉ እንድንረዳ ያግዘናል ( Dorson፡21)።

በአጠቃላይ ባህላዊ ቁሶችን ስናጠና ቁሶቹን ያበጁትን ባለሙያዎች አብሮ ማካተት ያስፈልጋል። ባለሙያዎቹን በምናጠናበት ጊዜ ቁሶቹ ምን ትዕምርት አላቸው? ባለሙያዎቹ ቁሶቹን ከምን እሳቤ በመነሳት ሰሯቸው? የባለሙያዎቹ የህይወት ፍስፍና ምንድን ነው? በኅብረተሰቡ ዘንድ ያሉ ያታዊ ክፍፍሎች ለምን አስፈለጉ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንድንመረምርና ምላሽ እንድናገኝ ያደርገናል።

## 2.1.5.የቁሳዊ ባህል ምደባ

በዚህ ጥናት ላይ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ያስችል ዘንድ የቁሳዊ ባህል ምደባ በመመልከት መረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱት ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች የተለያየ ገፅታ ፣ ቅርፅ እንዲሁም አገልግሎት ስለሚኖራቸው እና

ቁጥራቸው በርካታ ሊሆን ስለሚችል የዘርፉ ምሁራን ያስቀመጧቸውን የመመደቢያ ዘርፎች በመምረጥና በማዋገን ትንተና ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

(Ames፣20) ቅርፅ ፣ ዘመን እና ባለሙያ በመጠቀም ቁሶችን መመደብ እንደሚቻል ቢገልፅም መስፈርቶቹ ግን እያንዳንዳቸው  የተወሰነ ክፍተት እንዳለባቸው ገልጿል፡፡ በቅርፅ ለመመደብ ሲሞከር አብዛኛዎቹ ቁሶች የተለያየ ቅርፅ ስላላቸው ለመመደብ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በዘመን ለመመደብ ሲሞከር ደግሞ ቁሶቹ የተሰሩበትን ዘመን እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል ምደባው ጎዶሎ ይሆናል፡፡ ባለሙያዎችን መሰረት አድርጎ መመደብ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለመመደብ የሚረዳ ተግባር መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

(Prown፣2) ከላይ ከተጠቀሱት የመመደቢያ መስፈርቶች በተጨማሪ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ ፣ ከተሰሩበት ዘዴ እና ከቁሶቹ አገልግሎት አንፃር መመደብ እንደሚቻል አስቀምጧል፡፡ አሁንም ልክ እንደ Ames እነዚህም  መስፈርቶች የተወሰነ ክፍተት እንዳለባቸው ተጠቅሷል፡፡ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ ለመመደብ ሲሞከር ቁሶች ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ስለሚሰሩ ምደባውን አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በተሰሩበት ዘዴ ለመመደብ ሲሞከር ደግሞ እያንዳንዱ ባለሙያ የራሱ የሆነ ዘዴን ይጠቀማል፡፡ ከዚህ ሁሉ በቁሶቹ አገልግሎት መመደብ የተሻለ ነው ሲል አብራርቷል፡፡ አያይዞም አንድን መስፈርት ብቻ መጠቀም አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል የተለያዩ የመመደቢያ መስፈርቶችን መጠቀም ትንተናውን የተዋጣ ሊያደርገው ይችላል በማለት ያስረዳል፡፡

በዚህም መሰረት የመስኩ ምሁራን የመመደቢያ ዘርፎችን ያስቀመጡ ቢሆንም መስፈርቶቹ ግን ክፍተት እንዳለባቸው ሳይጠቅሱ አላለፉም፡፡

በጥቅሉ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች በመስክ ቆይታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመመደብ የሚያስችሉ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ቢሆንም ሁሉም መስፈርቶች የተወሰነ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ Prown ያስቀመጣቸውን ቁሶቹ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስ እና ከቁሶቹ አገልግሎት አንፃር ለመመደብ ሙከራ ተደርጓል፡፡

## 2.1.6.የቁሳዊ ባህል አገልግሎት

Glassie የቁሳዊ ባህልን አገልግሎት እንደሚከተለው ገልፆታል።

> All artifacts are multi functional. Among their functions, made to pass the time. It works to save the painter from madeness and boredom. It should to bring cash to the painter and prestige to the painter and patron. It is used decorate the home, to display taste, to represent its creator and customer. Helping to configure their fields to social relation. (Glassie፣79)

ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ቁሳዊ ባህሎች ፈርጀ ብዙ አገልግሎቶች አላቸው። እነሱም ጊዜን ለማሳለፍ ፣ ለገቢ ምንጭነት ፣ ለቤት ማስዋቢያነት ፣ ሰሪያቸውን ተጠቃሚያቸውን የመወከል አገልግሎትና ለማህበራዊ ግንኙነት ይውላሉ።

በባህላዊ መንገድ የተሰሩ ቁሶች በቤት ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብትና የኅብረተሰቡን እምነት ሊያንፀባርቁ ይችላሉ። ይህም የሚሆንበት ምክኒያት ቁሶቹ የሚሰሩት በአካባቢው በሚገኙ ተፈጥሮአዊ በሆኑ ጥሬ ቁሶች ከመሆኑም ባሻገር ባለሙያዎቹ ያላቸውን እምነት በቁሶቹ ላይ ሊያሳርፉ ስለሚችሉ ነው።

## 2.2. ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

## ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ

በፎክሎር ጥናት የተለያዩ ንድፍ ሐሳቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ። ለዚህ ጥናት የተመረጠው ክዋኔ ተኮር ንድፍ ሐሳብ ሲሆን በቀጣይ ስለክዋኔ ተኮር ንድፍ ሐሳብ ምንነት በዝርዝር እንመልክት።

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የሚከወነውን ነገር ከሚከወንበት አውድ ጋር የሚያጠና ነው። (Sims and Stephen፣28) ”Performance is still at the center of the study of folklore” ሲሉ ክዋኔ በአሁኑ ሰዓትም በፎክሎር የጥናት መስክ በማገልገል ላይ ያለ መሆኑን ገልፀዋል። ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሀሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው። “The performance approach helped to establish the core of the discipline as the study of artistic expression in groups and specific contexts.” /Sims and Stephen ፣26/። **ክዋኔ**

በአንድ በተወሰነ አውድ ወይም ቡድን ውስጥ ያለውን ጥበባዊ ገለፃ ለማጥናት ቁልፍ ነገር ነው፡፡

በመሆኑም እንደ sims and stephens ገለፃ " Folklorists pay attention to the performed act of expressive, artisitic communication —the when, where, with, whom, how and why people communicate. " (136)፡፡ የፎክሎር ተመራማሪዎች ክዋኔው እንዴት ፣ በማን ፣ መቼና የት ቦታ እንዲሁም በምን ዓይነት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንደሚቀርብ በክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ክዋኔ ገላጭ ድርጊት ሲሆን ክዋኔው ህያውና የተሳካ እንዲሆን የሚከወንበት የተደራጀ መቸት (ጊዜና ቦታ)፣ ከዋኝና ታዳሚ፣ በልምዳቸው የማዝናናትና ምላሽ የመስጠት ብቃት መኖር የግድ ነው፡፡

ይህ ንድፈ ሐሳብ ቁሳዊ ባህል በሚከወንበት ወቅት የሚታዩ መሰረታዊ ጉዳዮችን ነቅሶ በማውጣት በአግባቡ ለመተንተን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያሉት በመሆኑ እያንዳንዱን ነጥቦች በዝርዝር ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

ከዋኝ የክዋኔ አላባውያን ከሚባሉት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ከዋኙ ክዋኔውን በሚገባ አቀናጅቶ ለማቅረብም ሆነ የክዋኔውን አላማ ለማድረስ ማንነቱ፣ ማህበራዊው ደረጃው፣ እድሜው፣ የአከዋወን ብቃቱ ፣ የታዳሚን አያያዝ ችሎታው እና የፈጠራ ችሎታው ጉልህ ሚና አላቸው፡፡

ከዋኝን አስመልክቶ Finnegan ሲገልፁ “Performers are also of certain ages, gender, social position, training, reputation, and competence all needing investigation” (Finnegan፣90) በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከዋኝ በክዋኔው ወቅት የሚያሳያቸው አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና ድምጸቶች ለክዋኔው ወሳኝ ናቸው፡፡ እነዚህን በድል የተወጣ ከዋኝ በማህበረሰቡ ተመራጭ እና ተደናቂ ይሆናል፡፡

በአንድ ክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን የከዋኝነት ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በሌሎች ክዋኔዎች ደግሞ ታዳሚዎች ባሉበት ሊከውን ይችላል፡፡ ይህንን ሀሳብ Finnegan “ They may be acting singly; in pairs; in a small or a large group; interacting or exchanging with other single or collective performers as leader, follower, or

equal; overlapping or interchanging with more audience - like roles ." (Finnegan፣89) በማለት ይገልፁታል፡፡

ከዋኝ በተለይ በቁሳዊ ባህል ላይ በግል ወይም በጋራ በመሆን ስራውን ሊከውኑት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ታዳሚ በክዋኔ ውስጥ የሚነሳ ሌላው ጉዳይ ሲሆን ለክዋኔው ህልውና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የከዋኙም የከዋኝነት ሚና የሚረጋገጠው በታዳሚው በኩል የሚሰጡ አስተያየቶችና መስተጋብሮች ሲኖሩ ነው፡፡ የታዳሚዎች ሚና እንደፎክሎሩ አይነት ቢለያይም በአድማጭነት፣ በማጨብጨብ፣ በመቀበል ለክዋኔው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በአንዳንድ ቁሳዊ ባህሎች አሰራር በተለይ በለመዳ ወቅት የሚደረገው መስተጋብር ታዳሚው በክዋኔው ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቁሳዊ ባህል አሰራር ክዋኔ ወቅት በሚፈጠረው መስተጋብር በተጨማሪ በአንድነት መከወኑ የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡

አውድ ከክዋኔ አላባውያን ውስጥ የሚጠቀስ ነው፡፡ አውድን አስመልክቶ Sims and Stephens የሚከተለውን ብለዋል፡፡ "….context refers to anything and everthing that surrounds a text and performance ."(Sims and Stephens፣137)፡፡ አውድ አንድ ክዋኔ በሚከወንበት ወቅት ያለው አጠቃላይ ሁኔታ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ፣ በከዋኝ እና በታዳሚ መካከል ያለ መስተጋብር፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡ በዚህ ጥናት የክዋኔ አላባውያን ለመረጃ መተንተኛነት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

## 2.3.የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ የተለያዩ የጥናት ስራዎች የተዳሰሱ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ በነገዴ ኀብረተሰብ ላይ የተሰሩ ስራዎችን ለመዳሰስ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎችን ለመዳሰስ ሙከራ የተደረገ ሲሆን በጥናቱ ውስጥ አንድ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ እና አስራ አንድ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ፅሁፎች በድምሩ አስራ ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ ጥናቶቹ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር እንዲሁም በታሪክ ትምህርት ክፍሎች የተሰሩ ናቸው፡፡

ከተዳሰሱት ጥናቶች መካከል አራት የሚሆኑት በነገዴ ኅብረተሰብ ላይ የተሰሩ ስራዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስምንት ጥናታዊ ስራዎች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች ናቸው፡፡

## 2.3.1.ከነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ ጋር ተያይዘው የተሰሩ የጥናት ስራዎች

**ሐሰን ኡስማን** (1981) " በነገደ ወይጦ ለአዳኝና ለጣውንት የሚገጠሙ ስነ ቃላዊ ግጥሞች ማህበራዊ ረብነት " በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጽሁፍ ዋና ዓላማው የነበረው የኅብረተሰቡን ወግና ልማድ እንዳይጠፋ በፅሁፍ ዘግቦ ለማስቀረት እና ለሌሎች አጥኚዎች መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡ ይህን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ቃለ መጠይቅና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ምን ዓይነት የትንተና ዘዴ እንደተጠቀመ አለመግለፁ እንዲሁም የእኔ ጥናት የቡድን ውይይት ማካተቱ ልዩነታችን ነው፡፡ በርግጥ ጥናቱ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ለማወዳደር ይከብዳል፡፡

የሐሰን ሑስማን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የሚጠናው ኅብረተሰብ ሲሆን አጥኚው በጥናቱ ውስጥ የባህር ዳርን አጠቃላይ የተፈጥሮ አቀማመጥ እና ዳራ ላይ ትኩረት ማድረጉ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል ነገር ግን ይህ ጥናት በርዕሰ ጉዳይ ከኔ ጥናት ጋር አይገናኝም፡፡

**ተክለሃይማኖት ገብረስላሴ** (1984) " The wayto of lake Tana: An Ethino-Hstory " በሚል ርዕስ በታሪክ የትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ የነገዴ ኅብረተሰብ ባህሉ በዘመናት ሂደት ያሳየውን ለውጥ ማሳየት እና ኬት መጣ ማሳየት እንደሆነ በጥናቱ ገልጿል፡፡ አጥኚው ከጥንት ጀምሮ ስለነገዴ ወይጦ ኅብረተሰብ ኬት መጣነት የሚያወሱትን ጽሁፎች ከማየቱም በተጨማሪ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የኅብረተሰቡን አጠቃላይ ዳራ ማለትም ቋንቋ ፣ ሃይማኖት ፣ ማህበራዊ ግንኙነት እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የዳሰሰ መሆኑ ነው፡፡

በጥቅሉ ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አንዱ ነገር የሚጠናው ማህበረሰብ ነው፡፡ በርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር አይገናኝም፡፡ የኔ ጥናት የነገዴ ኅብረተሰብ ባህላዊ የእጅ ስራዎችን ከማሳየቱም በላይ ስለ ኅብረተሰቡ አጠቃላይ ዳራ ያሳየ ነው፡፡

**አየለ ፍቅሬ** (1998) " ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ " በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጽሁፍ ዋና ዓላማው የነበረው የነገዴ (ወይጦዎች) ማህበረሰብ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌሎች ኅብረተሰብ ጋር የሚፈጠረውን ግጭት እንዴት በባህላዊ መንገድ እንደሚፈቱት ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው የነገዴ ኅብረተሰብ ስያሜ፣ ጥንት አመጣጥ እና ሃይማኖት ለማሳየት የሞከረ ሲሆን ከሱ ስራ በፊት የተሰሩ ስራዎች በስያሜ ደረጃ በቀድሞው መጠሪያቸው ወይጦ ብቻ እያሉ ጥናታቸውን እንደሰሩ ገልጿል፡፡

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በጥናቱ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገላጭ የምርምር ዘዴን ጥናቱ ተጠቅሟል፡፡

የአየለ ፍቅሬ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የሚጠናው ኅብረተሰብ ብቻ ሲሆን አጥኚው በጥናቱ ውስጥ የባህር ዳር አጠቃላይ የተፈጥሮ አቀማመጥ እና ዳራ ላይ ትኩረት ማድረጉ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል ነገር ግን ይህ ጥናት ትኩረቱ ሃገረሰባዊ ልማድ ላይ በመሆኑ የእኔ ጥናት ደግሞ በቁሳዊ ባህል ላይ ያተኮረ በመሆኑ እንለያያለን፡፡

**ከሁሉም በላይ** (2004) " የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረችው ጽሁፍ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የነገዴ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች የኅብረተሰቡ አባላት ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ በኅብረተሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የኅብረተሰቡ ስያሜ ፣ ጥንት አመጣጥ ፣ የስራ ባህልና አምልኮ እንዴት እንደተገለፁ ለማሳየት ሞክራለች ፡፡ የኅብረተሰቡ አባላት በባህላዊ ስርዓቶቹ ላይ ያላቸው አመለካከት ለመፈተሽ ሞክራለች፡፡

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በጥናቱ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገላጭ የምርምር ዘዴን ጥናቱ ተጠቅሟል፡፡ የእኔ ጥናት የቡድን ተኮር ውይይትን ማካተቱ ልዩነታችን ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አጥኚው የነገዴ ኅብረተሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ፣ ጥንት አመጣጥ ፣ የአስተዳደር ሁኔታ ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ግንኙነትን ለማሳየት ችሏል፡፡

ነገር ግን ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በሚጠናው ኅብረተሰብ ይገናኝ እንጂ በርዕስ ጉዳይ ግን እንለያያለን ።

## 2.3.2.ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጥናት ስራዎች

ቁሳዊ ባህልን አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ የሚካተቱት ጥናታዊ ስራዎች ከሚጠናው ርዕስ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ስምንት ጥናታዊ ስራዎችን በተሰሩበት ዓመተ ምህረት ቅደም ተከተል ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

**አስቴር ሙሉ** (2000) " ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ዕቃዎች በዘጌ ባህረ ሰላጤ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማ አድርጋ የተነሳችው በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን ሳይንሳዊ በሆነ የአጠናን መንገድ መግለፅ ፣ መቅረፅ ፣ መሰነድና እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውና ፈፅሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚሰጡበትን መንገድ መጠቆም መሆኑን ገልፃለች፡፡ የጥናቷን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅማ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ ባህላዊ ቤቶቹ ማህበረሰቡ ቅርፁን ተከትሎ በሰጣቸው ስያሜ ፣ የሸክላ ቁሶቹን ደግሞ በአገልግሎታቸው መድባ በገላጭ ዘዴ ትንታኔ አቅርባለች ፡፡

በዚህም የዘጌ ባህረ ሰላጤ ኅብረተሰብ በባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ በተሰሩ የቤት ቁሶች አማካኝነት አስተሳሰቡን ፣ ኪነቱን እነ እውቀቱን ወዘተ ሲገልፅ የኖረ መሆኑን በደን ሃብት መጨፍጨፍ እንዲሁም በኢንዱስትሪ አብዮት መስፋፋት የተነሳ ህልውናቸውን በማጣት ላይ እንደሚገኙ በጥናቷ ለማረጋገጥ ችላለች፡፡ ለዚህም መፍትሔ ይሆናሉ ያለቻቸውን ሀሳቦች በይሁንታ ክፍሏ ጠቁማለች፡፡

በጥናቷ የቁሶቹን አገልግሎትና የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ህይወት መዳሰሷ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የእኔ ጥናት በሚጠናው ኅብረተሰብ የተለያየ መሆኑ ፣ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን ዋና ጉዳዩ ያደረገ በመሆኑ እና የአስቴር ጥናት በሸክላ ቁሶች ላይ በመወሰኑ ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስናን ጥናቷ በዋናነት በመዳሰሱ ይህ ጉዳይ ደግሞ የእኔ ጥናት ትኩረት ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

**ዋልተንጉስ መኮንን** (2000) " የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም " በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሳው የሽመናና የጥልፍ

ትውፊቶች በአክሱም እንዲከሰቱ ያደረጉና እነሱንም ከሌሎች የአኗኗር ዘይቤዎች ጋር ያስተሳሰሯቸውን የእምነት ፣ የአምልኮና የእሴት ገፅታዎች ማሳየት የሚል ነው።

ዓላማውን ለማሳካት ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል። ተፈጥሮአዊ መቼቱ ላይ በመገኘት ተፈላጊውን መረጃ ቁሶቹ ከበቀሉበት ኅብረተሰብ መረጃ ለመሰብሰብ ችሏል። መረጃዎቹም በምልከታና በቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተሰብስበዋል። የእኔ ጥናት ደግሞ የቡድን ተኮር ውይይትን ማካተቱ ልዩነታችን ነው።

የአክሱም ጥልፎች በርካታ የሰው ፣ የአትክልትና የቁሳቁስ ቅርፆችን የያዙ ናቸው። ቅርፆቹም ትዕምርት እንዳላቸው እና እያንዳንዱ ቅርፅ ከማህበረሰቡ የረጅም ጊዜ ታሪክ ፣ ባህልና እምነት ጋር የተያያዘ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል።

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። የዋልተንጉስ ጥናት የሽመናና የጥልፍ ስራ የሚዳስስ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን የዳሰሰ በመሆኑ እንዲሁም የሚጠናው ኅብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል።

***ሀብታሙ እንግዳ*** (2001) " በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሻሞ ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒዓለም የሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና " በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሳው የሸክላ ስራ የአሰራር ሂደት ፣ የሸክላ ስራ ውጤቶች የሆኑ ቁሶችን መሰብሰብ ፣ መሰነድ ከዚያም ባለፈ ቁሶች ያላቸውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መርምሮ ማሳየት የሚል ነው። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በጥናቱ ጥቅም ላይ ውለዋል። በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመሰብሰብ ተችሏል። የእኔ ጥናት ደግሞ የቡድን ተኮር ውይይት ማካተቱ ልዩነታችን ነው።

የእኔ ጥናት የስፌት ስራ ውጤቶችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን የመረመረ በመሆኑ ፤ የሀብታሙ ጥናት ደግሞ በሸክላ ቁሶች ላይ በመወሰኑ እንዲሁም የተጠኚው ኅብረተሰብ መገኛ ቦታ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል።

**ደግሰው ጥላሁን** (2003) " ባህላዊ የሸክላ ስራና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ " በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናታዊ ጽሁፍ የጥናቱ ዋና ዓላማ ባህላዊ የሸክላና

የቆዳን አሰራር ሂደትና ጥቅም ማሳየትና መቅረፅ ፣ የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ መዳሰስ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ከዳር ለማድረስ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመሰብሰብ ችላለች፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ የቡድን ተኮር ውይይትን ማካተቱ ልዩነታችን ሲሆን የመስኩ ምሁራን ካብራሯቸው የመተንተኛ ሂደቶች መካከል ገለፃንና ትርጓሜን ጥናቱ መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ቁሶቹ ከሚሰጡት አገልግሎት ባሻገር የተጠቃሚዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን በመጠቆም እና አንዳንድ ባህላዊ ክንዋኔዎችን ለመከወን እና የተጠቃሚዎችን እምነት መግለጫ በመሆን እንደሚያገለግሉ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የቁሱን የአሰራር ሂደት ከባህላዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም ጥናቱ በሽክላና በቆዳ ስራ ላይ ማተኮሩ እና የእኔ ጥናት ደግሞ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን በመዳሰሱ እንዲሁም የሚጠናው ኅብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

**አስማማው እስተዚያ** (2003ዓ.ም) ‹‹ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በወረዳው በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራር ብሎም በምን ተፅዕኖና እንዴት እንደጠፉ ማሳየት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ከዳር ለማድረስ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ እንዲሁም በቡድን ውይይት ለመሰብሰብ ችሏል፡፡

ባህላዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ይዘውት የነበረውን ቅርፅ ይሰጡት የነበረውን አገልግሎትና ጥበባዊ እሴት ከነተፈጥሯዊ አውዳቸው በተለያዩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክኒያቶች የተነሳ ጨርሶ የመጥፋት ፣ የቅርፅና የጥሬ ቁስ እንዲሁም የአገልግሎት ለውጥ እንደተከሰተባቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ ሀገረሰባዊ ምህንድስና ላይ ማተኮሩ ፣ የእኔ ጥናት የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራር ላይ በመወሰኑ እንዲሁም የሚጠናው ኅብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

**አብይ አክሊሉ አበበ** (2004ዓ.ም) ‹‹የክስታኔ ማህበረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ጥናት›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በክስታኔ ማህበረሰብ ምን ምን አይነት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች እንዳሉ በማሳየት፣አገልግሎታቸውንና ባህላዊ ፋይዳቸውን በመግለፅ አብራርቷል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በጥናቱ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ የቡድን ተኮር ውይይትን ማካተቱ ልዩነታችን ነው፡፡

ቁሶቹ በበቀሉበት ኀብረተሰብ ውስጥ ምን ምን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች እንዳሉ እንዲሁም ምን አገልግሎት አላቸው የሚሉትን ጉዳዩች ተመልክቶ የሚከተለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶቹ ከተለያዩ ጥሬ እቃዎች የሚሰሩ መሆናቸውን እንዱሁም ቁሶቹ በተለያየ መልኩ የእለት ተግባራትን መከወኛ በመሆን እንደሚያገለግሉ ገልጿል፡፡ ከዓላማ አንፃር የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ምን ምን እንደሆኑና የቁሶቹን አገልግሎት መግለፁ ጥንካሬውን ያሳያል፡፡  ከአንድ በላይ በሆነ ንጥረ ቁስ የሚሰሩ ቁሶችን ሲመድብ በምን አግባብ እንደመደባቸው በቅጡ አለማሳየቱ ድክመቱ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የአብይ ጥናት በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን ሁሉ የሚዳስስ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራር ላይ በመወሰኑ እንዲሁም የሚጠናው ኀብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

**ገዛኸኝ ጎሹ ገብረስላሴ** (2005) " ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ " በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በወረዳው ምን እንደሚመስል ማሳየትና መሰነድ ሲሆን ቁሶቹ ሲዘጋጁ የሚያልፉበትን አሰራር ሂደት ፣ ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች የሚሰሩባቸውን ጥሬ እቃዎችና ቁሶቹን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ ነው፡፡ የባለሙያዎቹን ባህላዊ ዳራ ፣ በወረዳው የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ ታሪካዊ አመጣጥ እና ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ፣ ባለሙያዎቹ ለማህበረሰቡ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም ባህላዊ የቆዳ ቁሶቹ ዓይነትና አገልግሎታቸው ምን እንደሚመስል በጥናቱ ቃኝቷል፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ ቃለመጠይቅና ምልከታን በዋና እንዲሁም የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ጥናቱ መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ቁሶቹ ከሚሰጡት አገልግሎት ባሻገር የተጠቃሚዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን በመጠቆም እና አንዳንድ ባህላዊ ክንዋኔዎችን ለመከወን እና የተጠቃሚዎችን እምነት መግለጫ በመሆን እንደሚያገለግሉ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የገዛኸኝ ጥናት ባህላዊ የቆዳ ስራ የዳሰሰ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን የዳሰሰ በመሆኑ እንዲሁም የሚጠናው ኅብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

**ደምስ መሸሻ** (2009ዓ.ም) ‹‹ባህላዊ የሸክላ ስራና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በክስታኔ ማህበረሰብ በሸክላና በአንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የኅብረተሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመር ነው፡፡ ከዓላማ አንፃር የሸክላና የአንጥረኛ ቁሶች ምን ምን እንደሆኑና የቁሶቹን አገልግሎት ገልጿል፡፡ ከአንድ በላይ በሆኑ ንጥረ ቁስ የሚሰሩ ቁሶችን ሲመድብ በምን አግባብ እንደመደባቸው በቅጡ ማሳየቱ ጥንካሬውን ያሳያል፡፡

የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በጥናቱ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ይህን ጉዳይ ከዳር ለማድረስ በጥናቱ አካባቢ የሚገኙና ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ እንዲሁም በቡድን ውይይት ለመሰብሰብ ችሏል፡፡

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የደምስ ጥናት ባህላዊ የሸክላና የአንጥረኛ ስራ የሚዳስስ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ የስፌት ስራዎችን እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን የዳሰሰ በመሆኑ እንዲሁም የሚጠናው ኅብረተሰብ መለያየቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያለያየዋል፡፡

በዚህ ክፍል ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፅንሰ ሐሳባዊ እና ንድፈ ሐሳባዊ ጉዳዮችን ለማንሳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የጥናት ስራዎችንም ለመዳሰስ ተሞክሯል ፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ ደግሞ የሚጠናው ኅብረተሰብ እና አካባቢ አጠቃላይ ዳራ የሚዳሰስ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1.የባህር ዳር ከተማ አካባቢያዊ ዳራ

ባህር ዳር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ ከተማ በመሆን የተመረጠችው በ1985ዓ.ም ሲሆን ከተማዋ ከአዲስ አበባ በሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ በ564 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የባህር ዳር ከተማ ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ በ11º 38º ሰሜን ላቲቲውድና በ37º 10º ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ በጣና ሃይቅ ደቡብ ዳርቻ ፣ ከባህር ወለል በላይ 1801 ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኝ ነች፡፡ የባህር ዳር ከተማ አጠቃላይ ስፋት 15.455 ሄክታር ሲሆን በአጠቃላይ ስፋቷ 17.2% በውሃ የተሸፈነ ከመሆኑም በላይ ከ2% በታች ተዳፋት ነች፡፡(ደመቀ፣3)

የባህር ዳር ከተማ አማካኝ የዝናብ መጠን 1224 ሚሊ ሜትር ሲሆን የከተማዋ አማካኝ የሙቀት መጠን ደግሞ ዝቅተኛው 23.2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ከፍተኛው 29.7 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው፡፡ ዝቅተኛው የሙቀት መጠን የተመዘገበው በሐምሌና በነሐሴ ወር ሲሆን መጠኑም 23.3 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወሩ ዝቅተኛ የቅዝቃዜ መጠን 7.1 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ይህም በጥር ወር ላይ የተመዘገበው ነው፡፡

የከተማዋ ነዋሪዎች ቁጥር በየዓመቱ እየጨመረ መምጣቱን በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የባህር ዳር ከተማ ህዝብ ቁጥር 649.429 በላይ እንደሚሆን ባህር ዳር መፅሄት(ደመቀ፣2) ላይ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡ በከተማዋ የተለያዩ የእምነት ተከታዮች የሚኖሩ ሲሆን 87.54% ያህሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ፣ 11.9% ያህሉ የእስልምና እምነት ተከታይ ቀሪው ደግሞ የሌሎች እምነት ተከታዮች እንደሆኑ ውቢቱ ባህር ዳር መፅሄት ላይ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል (ዘመኑ፣2)፡፡


የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር በዘጠኝ የከተማ ክፈለ ከተሞች ፣ በሶስት የገጠር ሳተላይት ከተሞችና በዘጠኝ የገጠር ቀበሌዎች በአጠቃላይ በ21 የቀበሌ አስተዳደሮች የተከፈለ ነው፡፡ የነገዴ ማህበረሰቦች በፋሲሎ ክፍለ ከተማ 03 ቀበሌ እና በጣና ክፍለ ከተማ 16 ቀበሌ ሰፍረው በመኖር ላይ እንደሚገኙ የአማራ ስፖርት መፅሄት ላይ የተገኘው መረጃ ያመላክታል (ጥላሁን፣12-13)፡፡

ባህር ዳር በርካታ የቱሪስት መስህቦች ያሏት በመሆኗ የሰዎችን/የጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜ ማራዘም የሚያስችል ሃይል አላት፡፡ ጣና ሃይቅ ካሏት የቱሪስት መስህቦች መካከል አንዱ ሲሆን በሃይቁ ውስጥ ሰላሳ ሰባት ደሴቶች ይገኛሉ፡፡ ከሰላሳ ሰባቱ ደሴቶች ሃያ አንድ ያህሉ ገዳማት ያሉባቸው ደሴቶች ናቸው፡፡ ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በፊት የተሰሩ ጥንታዊ ስዕሎች ፣ የብራና ላይ ጽሁፎች ፣ መስቀሎች በገዳሞቹ ውስጥ እንደሚገኙየአማራ ስፖርት መፅሄት ላይ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ (ጥላሁን፣2) ወደ ገዳሞቹ የመጣ ሰው የሚያገኘው የተለየ ነገር ቢኖር በእጅ የተሰሩ የተለያዩ የጥበበ ዕድ ስራዎችን ማግኘት ይችላል፡፡

ሌላኛው ውብ ስፍራ ከባህር ዳር በ30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ጢስ ዓባይ ነው፡፡ በ2010 ዓ.ም ባህር ዳርና አከባቢዋን የጎበኙ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶች ቁጥር ከ349 ሺህ በላይ ናቸው፡፡ በዚህም ከተማዋ ከ377 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አግኝታለች (ደመቀ፣12-13) ፡፡

በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ከ 56 በላይ ሆቴሎች ይገኛሉ፡፡ ከ32 በላይ የሚሆኑት ሆቴሎች በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ባለኮከብ ሆቴሎች ናቸው፡፡ ሌላው ደግሞ 10 የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ከአካባቢው ማህበረሰብ የተሰባሰቡ እንዲሁም ደግሞ ከተለያዩ ዓለም ሀገራት የመጡ ቱሪስቶች የሚያስተናግዱ የባህል ቤቶችም ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ባህል ቤቶች ውስጥ የተለያዩ የባህል ዕሴቶች ይንፀባረቃሉ፡፡ ኢትዮጵያዊነት የሚታይባቸው የባህል ትርሂቶች ጭምር ይቀርባሉ፡፡


Axum
Red Sea
Simyen Mountains National Park
Gondar
Lalibela
Djibouti
Bahir Dar
Blue Nile River
Awash National Park
Addis Ababa
Harar
Nazret
Great Rift Valley
Bale Mountains National Park
Harerge
Awassa
Sudan
Ogaden
Sidamo
Somalia
Kenya
Indian Ocean


Bahir Dar City
Legend
Belay Zeleke
Fasilo
Ginbot 20
Gish Abay
Hidar 11
Sefene Selam
Shimbit
Shum Abo
Tana
318000
321000
324000
327000
330000
1278000
1280000
1282000
1284000
1286000

## 3.2.የነገዴ ኅብረተሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ክፍል ስለነገዴ ኅብረተሰብ ስያሜ ፣ ጥንት አመጣጥ ፣ ቋንቋ ፣ ሃይማኖት ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች እንዲሁም አጠቃላይ ዳራ የተመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ በጥቅሉ ስለነገዴ ኅብረተሰብ ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች ፣ ከማህበራዊ ሚዲያ እና በመስክ ቆይታ ቦታው ድረስ በመገኘት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማቀናጀት የነገዴ ኅብረተሰብ አጠቃላይ ገፅታ ለማሳየት እንደሚከተለው ጥረት ተደርጓል፡፡

## 3.2.1.የነገዴ ኅብረተሰብ ጥንት አመጣጥ

ስለነገዴ ጥንት አመጣጥ ከቤተ መጻህፍት ካገኘዋቸው ጥናታዊ ስራዎች እንዲሁም በመስክ ቆይታ የተገኙ መረጃዎችን በማጣቀስ  በመጠኑም ቢሆን ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡ በርግጥ ሁሉም በመላምት እና በቃል ተረክ እንጂ እርግጠኛ የሆነ ታሪክ ማስቀመጥ የቻለ ስራ እና መረጃ አቀባይ የለም፡፡

የነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ በጎንደርና በጎጃም አካባቢ በጣና ሀይቅ ዙርያና ወደ ጣና የሚፈሱ ወንዞችን ተከትለው ይኖራሉ (Teclehaymanot:1)፡፡ የኅብረተሰቡን አመጣጥ በተመለከተ ግልፅና ተጨባጭ መረጃ እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም (Solomon:23)፡፡

መረጃ አቀባዩ  ግርማ ብርሀኑ ስለነገዴ ኅብረተሰብ ጥንት አመጣጥ እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፡፡

> ነገዴዎች በአሁኑ ሰዓት አኗኗራቸውና አሰፋፈራቸውን አማራ ክልል ላይ አድርገው ነው የሚገኙት፡፡ መነሻቸውም ከግብፅ ሆኖ የናይልን ተፋሰስ ይዘው የመጡ ሲሆን የኪሊዮፓትራ ቤተሰብ ከመሆናቸው በተጨማሪ በግብጥ ስልጣኔ ላይ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው የተከበሩ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ በዋናነት የውሃ ጥገኝነት ይታይባቸዋል፡፡ ከውሃ ተለይተው መኖር አይችሉም፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም)

ከላይ የቀረበውን ጉዳይ ይበልጥ ለማብራራት ያህል መረጃ አቀባዮቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት እንደሚከተለው ስለ ነገዴዎች ጥንት አመጣጥ ይገልፃሉ፡፡

> መነሻችን አባቶቻችን የሚነግሩን ተግብጥ ነው፡፡ ባህር ለባህር ሳንለቅ ከግብጥ አንስተን ወደ ባህር ዳር መጣን፡፡ ምህንያቱም ለዕለት የምንበላው ስለሌለን ምግባችንን በቀላሉ ለማግኘት ባህር ለባህር እንንዛለን፡፡ ዓሳውን አንባዛውን ጉማሬውን እየበሉ እነደመጡ

> አባት አያቶቻችን ነግረውናል፡፡ ውሃ ለውሃ ተጉዘን ለረጅም ጊዜ የረጋነው ባህር ዳር ላይ ነው፡፡ ምህንያቱም ባህር ዳር በውሃ የተከበበች በመሆኗ እና ብዙ ተረፈ ምርት ስለሚገኝበት ነው ብለውናል፡፡ (አህመዴ ዳውድ[2] ፣አንበሳው በለው፣መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም)

ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ አየለ ፍቅሬ ስለ ነገዴዎች ጥንት አመጣጥ የፃፈውን እንመልከት

> አባቶቻችን እንደነገሩን መጣን የሚባለው ተግብጥ ነው፡፡ በፈርዖን ጊዜ ጦርነት ተነስቶ ሲያባርሯቸው ወንዙ ደርቆላቸው ተሻገሩ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ሳይሻገሩ ቀርተው ነበረና ተወገናቸው ተቆርጠው ቀሩ፡፡ ተዚያ የሚበሉት አጡ፡፡ " እንግዲህ ምን ይሻለናል ? " ብለው ሲማከሩ " አውሬ እናድንና እንብላ " አሉና ሄዱ፡፡ በኃላ አውሬዋን አግኝተው ገድለው ገፈፉና " አንተ ብላ ፣ አንተ ብላ " ሲባባሉ ተመሃላቸው አንዱ ሥጋውን ቆርጦ ጉርስ ሲያደርገው ኧረ ዋጠው! ሲሉ ወይጦ ተባለ ሲል መረጃ አቀባዮቹን ጠቅሶ ፅፏል (አየለ፣13) ፡፡

አያይዞም zelalemን ጠቅሶ እንዲህ ሲል ፅፏል፡፡ " ነገዴዎች ከግብፅ ወደ ኢያሪኮ ይጓዙ ከነበሩት እስራኤላውያን ተነጥለው የዓባይን ወንዝ በመከተል የመጡ መሆናቸው ከሙስሊም አማሮች እንደሚታመን ገልጿል (አየለ፣13) ፡፡

ስለነገዴ ኅብረተሰብ ጥንት አመጣጥ በፅሁፍ የተቀመጠ እርግጠኛ የሆነ መረጀ እምብዛም የለም ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የፅሁፍ መረጃ በሌለው ኅብረተሰብ ውስጥ አፈታሪክ ዋነኛ የታሪክ ምንጭ እንደሆነ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይስፈልጋል፡፡ ስለነገዴ ኅብረተሰብ ጥንት አመጣጥ ከላይ የተጠቀሱት የጥናት ስራዎችና ታማኝ መረጃ አቀባዮች እንደተናገሩት ከሆነ መነሻቸው ከግብፅ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

## 3.2.2. የኅብረተሰቡ መጠሪያ (ስያሜ)

በነገዴ ስያሜ ላይ ብዙ ነገሮች ተብለዋል፡፡ አየለ ፍቅሬ ስለስያሜያቸው ሲያስረዳ " በደርግ ዘመን ነገዴ ተብለው መጠራት ጀመሩ፡፡ ምክንያቱም ወይጦ እንደ ስድብ ስለሚቆጠር፡፡ ነገር ግን እራሳቸው ነገዴ ወይጦዎች ትርጉሙን አያውቁትም " ብሏል (11) ፡፡

---

[2] አቶ አህመዴ ዳውድ የነገዴ ኅብረተሰብ ሽማግሌ ሲሆኑ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ ግንባር ቀደም ተሳታፊ የ70 ዓመት ሽማግሌ ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መረጃ አቀባዮቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት ስለስያሜያቸው እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ " ወይጦ የሚለውን ስያሜ ያገኙት ከውሃ አካላት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላላቸው እና አንዳንድ ጊዜም ወይጦዎች ያገኙትን ሲበሉ ሲውጡ የወጣላቸው መጠሪያ ነው። ስድብም አይደለም ሌላ ቋንቋም አይደለም። " (ግርማ ብርሃኑ፣ አህመዴ ዳውድ፣ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም)

(Teclehaymanot፣47) በበኩሉ ደግሞ ዋጠው ከሚለው ግስ ፀያፍ አባባል የመጣ ነው ይላል ። ኅብረተሰቡ ግን አዳኞች መባልን እንደሚፈልጉ ገልጿል።

አብዛኞቹ አጥኚዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደ ስድብ በሚቆጠረው መጠሪያቸው ወይጦ እያሉ ቢፅፉም አየለ ፍቅሬ ግን ኅብረተሰቡ በሚስማማበት ከደርግ ዘመን ጀምሮ በወጣላቸው ነገዴ በሚል ስያሜ መጥራቱ የተሻለ ያደርገዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ነገዴ የወይጦ መጠሪያ እንዲሆን ቢደረግም ነገዴ ያልሆኑ ብዙ ሰዎቹ ግን ስያሜውን አልተቀበሉትም ነበር ምክንያቱም ኅብረተሰቡን ከመፍራታቸው የተነሳ ነገዴዎች በሌሉበት ወይጦ ብለው ይጠሯቸዋል ፊት ለፊት ሲገናኙ ግን ነገዴ ብላው ይጠሯቸዋል ሲል (አየለ ፍቅሬ ፣11) ፅፏል።

በመስክ ቆይታዬ ምልከታ በማደርግበት ወቅት ነገዴዎች በበፊት መጠሪያቸው ወይጦ ሲባሉ እንደማይወዱ በአካል ተገኝቼ ለማረጋገጥ ችያለው።

### 3.2.3. ቋንቋ

ማንኛውም ኅብረተሰብ ለመግባባት ቋንቋን መጠቀሙ የግድ ነው። የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ በጣና ሃይቅ አካባቢ የሚገኙ የነገዴ ኅብረተሰብ ወይም ጉማሬ አዳኞች እስከ አሁን ድረስ የሚናገሩት ቋንቋ አማርኛ መሆኑን ነው። ይህንኑ በተመለከተ " ነገዴዎች የራሳቸው የሆነ ቋንቋ በአሁኑ ጊዜ የላቸውም። የሚናገሩት ቋንቋ አማርኛ ሲሆን በፊት ግን ዐረብኛ[3] ቋንቋ ይናገሩ እንደነበር የሀገር ሽማግሌዎች ሲናገሩ እንደሚያስታውስ ገልጿል። " (ግርማ ብርሃኑ፣ቃለመጠይቅ፣መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም)

[3] ዐረብኛ ቋንቋ ከእስልምና ጋር የተያያዘ እንጂ ከነገዴዎች ጋር ያለው ቅርርቦሽ አነስተኛ ነው። በ1890ዎቹ ዓመታት ከቦሩ ሜዳና ከዐጤ ዩሐንስ ፍጅት የሸሹ የወሎ ሙስሊሞች በዚያ ሲያልፉ እንዳሰለሚቸው ይነገራል። በዚህም የተነሳ አንዳንድ የዐረብኛ ጥራዝ ነጠቅ ቃላት ዐውቀው ይሆናል። በተቀር ግን ከዐረብኛው ይልቅ አገውኛ (አውንጊ) ይቀርባቸዋል። (አየለ)

ሌላው መረጃ አቀባዬ አህመዴ ዳውድ " የምንናገረው ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ግን አባቶቻችን ሚስጥር ለማውራት የተወሰነ የዐረብኛ ቃላትን ይጠቀሙ ነበር። " ሲሉ ተናግረዋል (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) ።

(Teclehaymanot፣9) በበኩሉ ነገዴዎች በመልክና በቁመና በአካባቢው ካሉ ከአማራና ከአገው ኅብረተሰብ የማይለዩ መሆናቸውን ጠቅሶ ፣ ነገዴዎች አማርኛ ከመናገራቸው በፊት የአገውኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልፃል።

በአጠቃላይ የነገዴ ኅብረተሰብ ቋንቋን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ከሚናገሩት የአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ባለፉት ጊዜያት ዐረብኛና አገውኛ ቋንቋ ይናገሩ እንደነበር ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ያመላክታሉ። ቢሆንም ግን ዐረብኛና አገውኛ ቋንቋዎችን ነገዴዎች ይናገሩ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም።

## 3.2.4. ሃይማኖት እና አምልኮ

በአሁኑ ወቅት ዘጠና አምስት በመቶ የሚሆነው የነገዴ ኅብረተሰብ የእስልምና ዕምነት ተከታይ ሲሆን ቀሪው አምስት በመቶ የሚሆነው የኅብረተሰቡ ክፍል የክርስትና ዕምነት ተከታይ ነው።

አምስት በመቶ የሚሆኑት የነገዴ ኅብረተሰብ 16 ቀበሌ የሚገኘው የኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን የፀሎት ጥሪ ሰምተው የክርስትና እምነት ተከታይ እንደሆኑ መረጃ አቀባዬ ፋሲል ሙጩ (ቃለመጠይቅ መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀውልኛል።

Teclehaimanot በበኩሉ ስለነገዴዎች ኢጣሊያዊው ፒያዚያ /እ.ኤ.አ ከ1871-75/ ኢትዮጵያን ሲጎበኝ በፃፈው ፅሁፍ ነገዴዎች ሃይማኖት እንደሌላቸው ፣ ለሙታን ክብር የማይሰጡ ፣ ልጆቻቸውን የማይንከባከቡ ፣ ሴቶችን የሚንቁ እንደነበሩ ፅፏል (2) ።

አየለ ፍቅሬም በጥናታዊ ጽሁፉ የነገዴ ኅብረተሰብ የእስልምና ዕምነት ተከታዮች ቢሆኑም መስጊዶቻቸው ግን ከሌሎች ሙስሊሞች መስጊዶች ተለይተው ለብቻቸው እንደሆኑ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 03 እና ቀበሌ 16 የሚገኙትን መመልከቱን መስጊዶቹ " የእነርሱ ናቸው " ከመባላቸው በቀር ከሌሎች የአማራ መስጊዶች በውጫዊ ገፅታቸው የተለየ ነገር እንደሌለባቸው ገልጿል (አየለ፣22)።

በርግጥ የነገዴ መሲጊዶች ከሌላው የአማራ መስጊዶች ባይለዩም ሌላው የአማራ ሙስሊም የነሱ መስጊድ ውስጥ የማይገባው ነገዴዎች ያገኙትን ስለሚበሉ እና እምነቱን ከመጠሪያነት በዘለለ ለእምነቱ ተገዢ ባለመሆናቸው በዚህ ምክኒያት በሌላው የእስልምና ዕምነት ተከታይ ዘንድ ስለሚናቁ እንደሆነ ነገር ግን የቀብር ቦታቸው አንድ ቦታ እንደሆነ መረጃ አቀባቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት (ወንድይፍራው ዘውዱ ፣ ወይንሸት አያሌው ፣ መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም) ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ከባዕድ አምልኮ ጋር ተያይዞ ህዳር 12 ከንፈሮ ዓባይ (ዓባይ ከጣና ሲወጣ) በመሄድ ወይፈን አርደው የግዮንን አምላክ ይለማመኑ እንደነበር እና በበዓሉ አከባበር ላይም ሁሉም አባል እንደሚገኙና እንደየአቅሙ ያለውን በማዋጣት እንደሚሳተፍ መረጃ አቀባዮቹ ጋር ባደረገው ውይይት መረዳቱን ጽፏል (አየለ፡ 22) ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሌላው ከአምልኮ ጋር የሚያያዘውን አፈታሪክ  መረጃ አቀባዬ አህመዴ ዳውድ እንዲህ ሲሉ ያስረዳሉ፡-

> አባቶቻችን እንደሚነግሩን ተሆነ በአንድ ወቅት ነገዴዎች ዓሳ ለማጥመድ መረብ ወደ ውሃ ሲጥሉ በአጋጣሚ ጅኒውን በመረብ ያጠምዱታል፡፡ ተሂያ በኋላ የጅኒው እናትና አባት ልጃችንን መልሱልን ብለው ነገዴዎችን ሲጠይቋቸው ባህር ለባህር ስለምንጓዝ እና የምንበላውንም የምናገኘው ከባህር ስለሆነ ከዚህ በኋላ ነገዴዎችን ጅኒዎች እንዳይነኩ ቃል አስገብተው ጅኒውን ለቀቁላቸው፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም)

ከዚህ ጉዳይ በኋላ ነገዴዎችን ጂኒ አይነካቸውም ይባላል፡፡ እንዲያውም ጣና ሃይቅ እና ዓባይ ወንዝ ውስጥ ገብቶ በጂኒ የሞተን ሰው የሚያወጡት እነርሱ ናቸው፡፡ ምክኒያቱም ሌላ ሰው ገብቶ አስክሬኑን ለማውጣት ቢሞክር ጅኒው ሬሳውን እንደሚሰውርበት በቡድን ውይይት ወቅት (ፋሲል ሙጬ ፣ ግርማ ብርሃኑ ፣መጋቢት 19 ቀን 2011ዓ.ም) ተናግረዋል፡፡

## 3.2.5. ማህበራዊ ግንኙነት

የነገዴ ኅብረተሰብ በጋራ በመሆን ያገኙትን ፍራፍሬና ጉማሬ በማደን ይመገቡ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ነገዴዎች በአፈታሪክ እንደሚታወቀው በጣና ሃይቅ ዙርያ የሚኖሩ ጉማሬ አዳኞች ይባሉ ነበር ፡፡

ነገዴዎች የጉማሬ ሥጋ በመብላታቸው ሳቢያ በአካባቢያቸው ባሉ አማሮች እጅግ እንደተናቁ አብዛኞቹም በነገዴ የተዘጋጀ ምግብ እንደማይበሉ ፣ እቤታቸውም እንደማይገቡ (Simoons ፣165) ጽፏል፡፡ እርሱ ስለፃፈ ብቻ ሳይሆን ዛሬም የሚታይ ሐቅ ነው፡፡

ነገዴዎች ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ አይነት የህይወት ዘይቤ የላቸውም፡፡ ያገኙትን የሚመገቡ ፣ ለማንኛውም ነገር ግድ የለሾች ፣ በሌላው ኅብረተሰብ ዘንድ የሚታዩ የስነ ምግባር እሴቶች የሌሏቸው ከመሆነቸው በተጨማሪ ያገኙትን በአንድ ቀን ውስጥ የማጥፋት ክፍት ቦታም ካገኙ በጋራ ሰፍሮ የመኖር በአጠቃላይ አንድ ቦታ ላይ ተረጋግቶ መቀመጥ እንደማይችሉ መረጃ አቀባዮቼ (ሱሌይማን በሽር ፣ ግርማ ብርሃኑ፣ፋሲል ሙጬ፣ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) ባደረጉት የቡድን ውይይት ይስማማሉ፡፡

ባለፉት ጊዜያት ነገዴዎች ባህር ዳርቻ የሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎችን እያጨሱ እዛው ይተኙ ስለነበር ጠረናቸው ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር እንዳይቀራረቡ አድርጓቸው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ከነገዴዎች ጋር መታየትም ሆነ ጋብቻ መፈፀም የሚያስተችና የሚያስንቅ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን የኑሮ ዘይቤያቸው በመለወጡ ምክንያት ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር የጋብቻ ህይወት እየመሰረቱ እንደሚገኙ መረጃ አቀባዬ (ቃለመጠይቅ፣ግርማ ብርሃኑ፣መጋቢት 18 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀዋል፡፡

" ባለፉት ጊዜያት አማሮች በአመጋገባችን ፣ በአኗኗራችን ይጠየፉን ይንቁን ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ከኛ ጋር እየተጋቡ እየተቀላቀሉን ነው፡፡ " ሲሉ የኅብረተሰቡ ተወላጅ የሆኑት መረጃ አቀባዬ አህመዴ ዳውድ ገልፀውልኛል (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) ፡፡

በዚህም ምክንያት ነገዴዎች ያላቸው ባህል እየጠፋና እየተበረዘ ይገኛል፡፡ ከዚህ በፊትም በአማራ ኅብረተሰብ ውስጥ የነበሩ ፋቂ ፣ ቀጥቃጭ ፣ ቡዳ …ወዘተ የሚባሉ ኅብረተሰቦች በአሁኑ ጊዜ ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር በመቀላቀላቸው የጠፉበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ ነገዴዎችም ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር በመቀላቀላቸው ሳቢያ ያላቸውን ባህል እና ማንነት እያጡ መሆኑን የኅብረተሰቡ ተወላጅ የሆኑት መረጃ አቀባዮቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት (መሐመድ ሁሴን እና እማ ዘመድ፣መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀዋል፡፡

ነገዴዎች በአማራዎች ተፅዕኖ ስር የወደቁ ውስን ግዛት ላይ የሚኖሩ ናቸው ፡፡ በአማራና በሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚገለሉ እንደ ባርያ የሚቆጠሩ ናቸው ፡፡ ይህንን በይበልጥ

ለማስረዳት ያህል " እናት አለም ጠኑ " የተሰኘው የፀጋዬ ገብረመድህን የመድረክ ቲአትር ላይ ደበበ እሸቱ ተላብሶት የነበረው ገጸ ባህሪይ የነገዴ ኅብረተሰብ ሲሆን ቲአትሩ ላይም

> ወይጦ !ወይጦ ነገደ ወይጦ መናጢ ደሀ የመናጢ ገራፊ ነኝ፡፡ ወይጦ ምን እንደሆን ታውቃለህ ? ዘር ነው ፡፡ የሰው ዘር ፡፡ ሰሜንኛ ፡፡ ባለእጅ ፡፡ ጥበበኛ ፡፡ መኛጢ ደሀ ፡፡ ሳባ ሳትመጣ ሜዳ ሳትወጣ ሳትቀናጣ ጥሬ ዘር የምድሯካም ነኝ አሉ ኢትዮጵያዊ ፡፡

ከቲአትሩ ጽሁፍ የምንረዳው ነገር ነገዴዎች መናጢ ደሀ እነደሆኑ የተናቁና የተገለሉ እንደሆኑ ነገር ግን ጥበበኛ ባለ እጅ እንደሆኑ የዕደ ጥበብ ስራ እንዳላቸው የሚያመላክት ነው፡፡ ነገር ግን ቲአትር የፈጠራ ስራ እንደመሆኑ መጠን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡

በአጠቃላይ በሀገራችን ኢትዮጵያ ልክ እንደ ነገዴዎች ሁሉ በአደንና በሚመገቡት ምግብ ምክንያት የሚገለሉ ኅብረተሰቦች አሉ፡፡ እነሱም የጉራጌው ፉጋ ፣ የኦሮሞው ዋታ ፣ የከፋው ማንጆ ፣ የሙርሲው ኩዋጉ ፣ የሱማሌው ሚድጋን ተጠቃሽ ኅብረተሰቦች ናቸው፡፡

### 3.2.6. አስተዳደራዊ ሁኔታ

ነገዴዎች በአካባቢው ገዢዎች በሚደረግባቸው ተፅዕኖ በፖለቲካ ረገድ ይህ ነው የሚባል ቦታ እንዳልነበራቸው ከሁሉም በላይ Solomon ንን ጠቅሳ (21) ጽፋለች፡፡ ሆኖም ቀደም ብሎ ኅብረተሰቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ነጋድራስ የሚባል ስርዓት እንደነበረው አንዳንድ በኅብረተሰቡ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራንን ጠቅሳ ጽፋለች (ዝኒ ከማሁ፡21) ፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አየለ ፍቅሬ የነገዴዎች አስተዳደር ጥንታዊው አሳዳኝ " ነጋድራስ[4] " ዘመናዊው ደግሞ " አባጋር " እንደሚባሉ ገልጿል (አየለ፣17፣18) ፡፡ ነጋድራስ ከፋሺስት ኢጣልያ ወረራ በፊት የነበረ የአስተዳደር ስርዓት ሲሆን ዋነኛ ስራው የነበረው ጉማሬ ማሳደንና ከሸማግሌዎች ጋር በጋራ በመሆን የዳኝነት ስራ መስራት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ከወሎ ሙስሊሞች ባህላዊ ዳኝነትና አስተዳደር ጋር ተያያዥ ነው የሚባለው የአባጋር ስርዓት ተክቶታል፡፡

[4] ነጋድራስ በአማራው ኅብረተሰብ ዘንድ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡ በነገዴ ኅብረተሰብ ግን አሳዳኝ ተብሎ ይጠራል፡፡

እስልምናን ከመቀበላቸው በፊት በነጋድራስ ስርዓት ሲተዳደሩ ቆይተዋል፡፡ አሳዳኙ ካጠፋም በሽማግሌዎች ሽንጎ አማካኝነት ከስልጣኑ ይባረር ነበር፡፡ ይህም ስርዓት ቀስበቀስ ከእስልምና እምነት ጋር ተያይዞ በመጣው ሃይማኖታዊ አስተዳደር አባጋር ተተክቷል (ቃለመጠይቅ፣አህመዴ ዳውድ፣መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም) ፡፡

## 3.2.7. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ነገዴዎች ከጥንት ጀምሮ በአያትና በቅድመ አያቶቻቸው እንደሚደረገው በሃይቅና በወንዝ ዳርቻ በመኖር በውሃ ውስጥና ከአካባቢው የሚያገኟቸውን ነገሮች እንደሚመገቡና እንደ ዋነኛ የገቢ ምንጭ አድርገው የሚጠቀሙባቸው ስራዎች ወንዶች ዓሳ ማስገር ፣ የድንጋይ ወፍጮ መውቀር ፣ ታንኳ ከደንገል መስራት ፣ ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደ ጉማሬ የመሳሰሉትን እንስሳት በማደን ፣ ሴቶች ደግሞ ስፌት በመስፋት በመፍተል እና የማገዶ እንጨት በማቅረብ እንደሆነ ከሁሉም በላይ ታፈሰን ጠቅሳ ገልፃለች (23) ፡፡

" ከደንገል በተሰራ ታንኳ ላይ የድንጋይ ወፍጮ ጭነው ወደ እፍራዝ እና ጎርጎራ ወስደው ይሸጣሉ፡፡ በምትኩም ምጣድና ወጪት ከእንፍራዝና ጎርጎራ ያመጡ ነበር " (ቃለመጠይቅ፣አህመዴ ዳውድ፣መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም) ፡፡

ጣና ሃይቅ በአሁኑ ወቅት በባለሀብቶች ቁጥጥር ስር እየዋለ በመሆኑ ምክንያት ነገዴዎች ይተዳደሩባቸው የነበሩ የእጅ ስራዎችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ጥሬ ቁሶችን የማግኘት እድላቸው በመጣበቡ እንዲሁም ጣና ሃይቅ ከጊዜ ወደጊዜ የራሱን ህልውና እያጣ የመጣበት ጊዜ ስለሆነ ብዙም ተረፈ ምርት የለውም፡፡ በዚህም የተነሳ ለምግብነት ፍጆታ ፣ ለስፌት ስራ የሚሆን ደንገል ስለሌለው ነገዴዎች ልክ እንደ ሌላው ኅብረተሰብ ማንኛውንም ስራ በመስራት ላይ እንደሚገኙ መረጃ አቀባዮቹ ባደረጉት የቡድን ውይይት (አህመዴ ዳውድ እና ግርማ ብርሃኑ፣መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀዋል፡፡

ነገዴዎች ለወደፊት ህይወታቸው ስለማይጨነቁ የወር ደሞዝ ያለው ስራ መስራት አይፈልጉም፡፡ አሁን ላይ ግን ያለፈው አመለካከታቸውን ቀይረው ገንዘብ አጠራቅመው ቤት ሰርተው ኑሯቸውን ለውጠው መኖር ጀምረዋል፡፡ በውስጣቸውም የተለያዩ ሙዚቀኞችን ፣ ትራፊክ ፖሊሶችን እና የተለያዩ ምሁራንን ማፍለቅ እንደቻሉ መረጃ አቀባዮቹ ግርማ ብርሃኑ እና ፋሲል ሙጬ ነግረውኛል፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት 18 ቀን 2011ዓ.ም)

በባህር ዳር ከተማ ያሉት ነገዶዎች ከዚህ በፊት በልመናና በአደን ይተዳደሩ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ሴቶቹ ስፌት በመስፋትና በመሸጥ ይኖራሉ። ሌሎች አረብ ሀገር ድረስ እየሄዱ ስራ ይሰራሉ። ከዚህ በተጨማሪም በከተማዋ በሚገኙ የምሽት ቤቶች ውስጥ ተቀጥረው የተለያዩ ስራዎችን ይሰራሉ። ወንዶቹ የድንጋይ ወፍጮ ሰርተው ለገበያ ያውሉታል። እንዲሁም የቀን ስራና በልዩ ልዩ የግልና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጥረው እንደሚሰሩ መረጃ አቀባዮቹ ባደረጉት የቡድን ውይይት ገልፀዋል። (አህመዴ ዳውድ፣ ግርማ ብርሃኑ፣ፋሲል ሙጩ መጋቢት20 ቀን 2011ዓ.ም)

## 3.2.8.የጋብቻ ሁኔታ

ነገዶዎች " በማጭዶ በወስፌሽ " ተባብለው በቀላሉ ይጋባሉ። በማጭዶ በወስፌሽ ማለት ሀብትሽ በሀብቴ እንደማለት ነው። ወንዱ ከዓባይና ጣና ሃይቅ ዳርቻ ደንገል አጭዶ ይመጣል። ሴቲቱ ዳግሞ ደንገሉን አድርቃ የስፌት ውጤቶችን ትሰራለች። ነገር ግን ከሌላው ኅብረተሰብ የተለየ የሰርግ ስርዓተ ከበራ እንደሌላቸው እና የደንገል ተክል በኅብረተሰቡ ዘንድ ልዩ ቦታ የሚሰጠው የሳር ዓይነት እንደሆነ መረጃ አቀባዩ ግርማ ብርሃኑ ገልፀውልኛል። (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 18 ቀን 2011ዓ.ም)

# ምዕራፍ አራት

## 4.የነገዴ ኅብረተሰብ የእጅ ስራዎች መረጃ እና ትንተና

በዚህ ክፍል በስፌትና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን አሰራርና አገልግሎት መተንተን ዋናው ጉዳይ ሲሆን በቁሶቹ አማካኝነት የኅብረተሰቡን የህይወት ፍልስፍና መመርመር ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ቁሶቹን ለማዘጋጀት የሚታለፉ ደረጃዎች እና በእጅ ስራ ውጤቶቹ ሙያ የኅብረተሰቡን ፆታዊ ተሳትፎ መፈተሽ  እንዲሁም የቁሶቹ ወቅታዊ ሁኔታ ሌላኛው የዚህ ክፍል ትኩረት ነው፡፡

በመሆኑም በስፌትና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የአሰራር ሂደታቸውና አገልግሎታቸው እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶች የበቀሉበት ኅብረተሰብ ባህል ፣ ወግና ልማድ  ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 4.1.የስፌት ስራ

የስፌት ስራ ቁሳዊ ባህል ውስጥ ከሚመደበው ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ የስፌት ስራዎች በአንድ ኅብረተሰብ አካባቢ በሚገኙ ተፈጥሮአዊ በሆኑ የሳር ዓይነቶች የሚሰሩ ሲሆን የአንድን ኅብረተሰብ ማንነት ፣ እምነት ፣ ልማድ ፣ ባህልና ወግ በቅጡ ሊያሳዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የስፌት ውጤቶችን መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ፣ የጥሬ ቁሶች መገኛ ቦታ ፣ የስፌት ውጤቶች ሂደትና አሰራር ፣ አገልግሎት ፣ ፆታዊ ተሳትፎ እና በስፌት ባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ጠቀሜታ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች እንደሚከተለው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

### 4.1.1.የስፌት ውጤቶችን መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች

የነገዴ ኅብረተሰብ የስፌት ስራ ውጤቶችን ለመስራት የተለያዩ ጥሬ ቁሶችን እና ባህላዊ የሆኑ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ የጥበብ ውጤቶች ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳ ቁሶች እና መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑና ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ መረጃ አቀባዮቹ ናናዬ ገዳም እና ካሳዬ ማስረሻ (ቃለመጠይቅ መጋቢት12 ቀን 2011ዓ.ም) እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

1) **ማጭድ**፡- ለስፌት ስራ የሚያስፈልገውን ደንገል ለማጨድ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ ማጭድ ከብረት የሚሰራና ስለታማ ጥርስ ያለው ሲሆን ለማጨጃነት አመቺ እንዲሆን እጅ እንዳይጎዳ በማለት ሰዎች እጀታ ይገጥሙለታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እጃቸውን እንዳይከረክራቸው በእጀታው ላይ ጨርቅ ይጠመጥሙበታል፡፡ ይህም ማጭድ አገልግሎቱ ተሊስ የተባለውን የደንገል ተክል አቆጥቁጦ ከወጣበት ውሃ ውስጥ ከመሀል ወገቡ ላይ በእጅ በመያዝ ከስሩ ለመቁረጥ ያገለግላል፡፡ ይህ ቁስ በሀገር ቤት ባለሙያዎች ተሰርቶ ይሸጣል፡፡

ፎቶ ግራፍ 1 ማጭድ



ጣና ሃይቅ ዳርቻ በአጥኚው የተነሳ

2) **ደንገል** ፡- ይህ ጣና ሃይቅ እና ዓባይ ወንዝ ዳር የሚገኝ ሲሆን ለስፌት ስራ አገልግሎት የሚውል የሣር ዝርያ ነው፡፡ የደንገል ተክሎች ሶስት ዓይነት ሲሆኑ አንደኛውን ቪላ ብለው ይጠሩታል፡፡ ይህም በጣም ስስ የሆነና የዘንባባ ዓይነት ቅርፅ ያለው ነው፡፡ ስፌቱ ሲሰራ በቀለበት መልክ በክብ በማዞር የሚጀምሩበት ነው፡፡ ሁለተኛው ተሊስ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህ የደንገል ተክል በማጭድ የሚቆረጥና አንድ ወጥ የሆነ አግድም ቅርፅ ያለው ነው፡፡ ውጤቶቹ ሲሰሩ በወስፌ በመሰነጣጠቅ እንደ ግራምጣና አለላ በመሆን የሚያገለግል ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ አጎበር ይባላል፡፡ ይህም ደንገል በቀላሉ በውሃ ውስጥ በእጅ የሚነቀልና ባለ ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያለውና በቅርፁ ልክ ሶስት ቦታ

በመሰንጠቅ በክብ የሚዞረውን ተሊስ በላይ በኩል ለማሰሪያነት እንደ ሰበዝ በመሆን የሚያገለግል የደንገል ተክል ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 2 ዓባና ጣና ዳር የሚገኝ ተሊስ



ጣና ሃይቅ በአጥኚው የተነሳ


ፎቶ ግራፍ 3 ዓባና ጣና ዳር የሚገኝ ቪላ



ጣና ሃይቅ በአጥኚው የተነሳ

3) **ወስፌ፡-** ይህ ከብረት የሚሠራ ሹል ቁስ ሲሆን ስፌት ለመስፋት የሚያገለግል ነው፡፡ የሚገኘውም ከገበያ ላይ እንዲሁም የስፌት ባለሙያዎቹ በሚፈልጉት መጠንና ቅርፅ በባህላዊ መንገድ ብረታ ብረት በሚሠሩ ሰዎች በትዕዛዝ የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ቅርፁም ቀጥ ብሎ ሾለል ያለና ጫፉ ላይ የተሳለ መውጊያ ያለው ሲሆን ከላዩ በክብ ቅርፅ የተጠቀለለ የብረት ዘንግ ያለው ነው፡፡ ይህ ቁስ አገልግሎቱ የስፌት መስሪያ ደንገሉን የሚሰነጥቁበት ሲሆን በዋናነት ስፌቶችን ለመስፊያነት ያገለግላል፡፡

ፎቶ ግራፍ 4 ወስፌ




ቀበሌ 16 በአጥኚው የተነሳ

4) **ግራምጣ፡-** ከሳራማ ሜዳ የሚገኝ የሳር ዓይነት ሲሆን ሴቶች ከገበያ በመግዛት ለስፌት አገልግሎት የሚጠቀሙበት ቁስ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 5 ግራምጣ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

5) **አለላ፡-** ቀለም የተነከረ ግራምጣ ሲሆን ሴቶች ከገበያ በመግዛት ለስፌት ማስዋቢያነት የሚጠቀሙበት ቁስ ነው፡፡ አለላዎች የተለያዩ ቀለማትን የያዙ ናቸው፡፡ ቀይ ፣ አረንጓዴና ሰማያዊ ወዘተ የሆኑ አለላዎች በሰዎች ምርጫና ፍላጎት እነዚህ አለላዎች ከገበያው ተገዝተው ለስፌት ውጤቶች ማስዋቢያነት ይጠቅማሉ፡፡

ፎቶ ግራፍ 6 ቀለም የተነከረ አለላ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ


ፎቶ ግራፍ 7 አለላ ቀለም ሲነከር



03 ቀበሌ የነገዴዎች መኖርያ አካባቢ በአጥኚው የተነሳ

6) **ምላጭ (ቤሳ)፦** ይህ ከብረት የሚሰራ ስለታማ ቁስ ሲሆን ነገዴዎች ስፌት በሚሰፉበት ጊዜ የስፌት ውጤቱን ለማስተካከልና ለመቁረጫነት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ይህን ቁስ የሚያገኙት ከሱቅ ሲሆን ቤሳ የሚለው ስያሜ በራሳቸው በባለሙያዎቹ እንደወጣለት ይነገራል፡፡ ትርጉሙም ስለታማ መቁረጫ ማለት ነው፡፡ በቀድሞው ጊዜ ይህን ቁስ እየተዋዋሱ ይጠቀሙበት የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን በየግላቸው ይጠቀሙበታል፡፡ ምክንያቱ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንዳይዟቸው በመስጋት ነው፡፡ ይህ ቁስ አገልግሎቱ አጎበሩን ወደ ተሊሱ ለማሾለክ ጫፉ ላይ የሚቆርጡበትና ከስፌቱ ላይ የሚሎገመውን ላስቲክ ወይም ቆዳ ለመቁረጫነትና ስፌቱ ተሰርቶ ሲያልቅ ትርፍ የሆኑትን ደንገሎች ለመቁረጥ ይጠቀሙበታል፡፡

ፎቶ ግራፍ 8 ምላጭ



ከማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተገኘ

7) **ቆዳ**[5]**፦** ይህ ለምንጣፍነት የሚሸጠውን ቆዳ ከገበያ በመግዛት በትንሹ እየቆራረጡ የሚሰራውን የስፌት ዓይነት አለስልሶና አስውቦ ለመስራት የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ትንሽ ቆዳ በውሃ እየደጋገሙ በመንከር የሚሰራውን የስፌት ስራ ውጤት ለማጠናከርና የተለያዩ ቅርፆችን ለማውጣት አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የስፌት ስራ ውጤቶቹን የሚጠቀሙ ሰዎች እየሸተተ አይጥ እየበላብን ነው በማለታቸው በላስቲክ እየተተካ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች (ቃለመጠይቅ፣ተገኘች ተሾመ፣ መጋቢት12 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቆዳ ከላስቲኩ ዋጋ በመብለጡ የተነሳ የስፌት ውጤቶቹን በቆዳ ከተለጎመ የምናገኘው ገቢ ተመጣጣኝ ዋጋ አያስገኝም ሲሉ ሙያተኞች ይናገራሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ቆዳው በብዛት በላስቲክ እየተተካ ነው፡፡

---

[5] ቆዳው ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው ጀንዲ (የተመለጠው) ለመሶብ ፣ ለወንፊት ፣ ለወራንታ እና ለሌማት መለጎሚያነት የሚያገለግል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ላምነት (ከነፀጉሩ) ለአገልግል መለጎሚያነት ይጠቀሙበታል፡፡

ፎቶ ግራፍ 9 ቆዳ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

8) **ላስቲክ፡-** ይህ የስፌት ስራ ውጤቶችን ለማስዋቢያነት ባለሙያዎች ከገበያ በመግዛት የሚጠቀሙት ነው፡፡ ባለሙያዎቹ በሚፈልጉት መጠን በሜትር አስለክተው ከገበያ የሚገዙት ሲሆን አገልግሎቱ ተሰርቶ የተጠናቀቀውን ስፌት ከላይ ለመለጎም ሲሆን በአብዛኛው ጊዜ ባለሙያዎቹ የሚጠቀሙበትም የእንጀራ ማስቀመጫ መሶብ የታችኛውና የላይኛውን መጋጠሚያ እንዲሁም የመሶቡ መቀመጫ እግር ለመሸፈን ነው፡፡ የስፌት ቁሶቹ የሚለጎሙት ሲንፏቀቁና ሲፈጋፈጉ በቀላሉ እንዳይጎዱ ፣ እንዳይበጣጠሱና ስራው ውበት እንደኖረው ነው፡፡

9) **ጎማ (ማስታጠቢያ)፡-** ይህ ቁስ የደረቀውን ደንገል በመዘፍዘፍ እንደልብ እንዲታዘዝ ለማድረግና ቁሱን በተለያየ ቅርፅ ለመስራት ያገለግላል፡፡ ባለሙያዎቹ ይህንን ቁስ የሚያገኙት ከገበያ ሲሆን የሚሰራውም በዘመናዊ መንገድ በፋብሪካ ውስጥ ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ በቅል እንደሚጠቀሙ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ይህም ቁስ አገልግሎቱ ደንገሉ ደርቆ ከተሰነጠቀ በኋላ የስፌት ስራው ተጀምሮ በሚሰራበት ጊዜ የደረቁትን ደንገሎች በውሃ በመዘፍዘፍ ሲሰፉ እንዳይቸገሩ ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ስፌቱን ወደ ላይ

በሚያጥፉበት ጊዜ እንዳይከር ለማለስለስ የሚረዳውን ውሃ የሚያስቀምጡበት ቁስ ነው፡፡ በመጨረሻም ስራቸውን ሰርተው ሲጨርሱ እጃቸውን ውስጡ ለመታጠብ ይጠቀሙበታል፡፡

ፎቶ ግራፍ 10 ማስታጠቢያ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

10) **ውሃ፡-** ይህ አገልግሎቱ የደረቀውን የስፌት ጥሬ ቁስ ደንገል እንዲሁም ከገበያ ላይ ለሚገዙት አለላ ግራምጣና ሰበዝ እጃቸውን እንዳይቆርጣቸው በማራስ የሚጠቀሙበት ነው፡፡

## 4.1.2.የስፌት ስራ ውጤቶችን ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መገኛ ቦታ

ሰዎች ሀገረሰባዊ እጅ ስራን ለመስራት ሲፈልጉ በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሀገር በቀል የሆኑ ጥሬ ቁሶችን ይጠቀማሉ፡፡ የነገዴ ኀብረተሰብ ለስፌት መስሪያ የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን የሚያገኙት ከተለያየ ቦታ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ በስፌት ስራ ላይ የተሰማሩት መረጃ አቀባዮቼ የ03 ቀበሌ ነዋሪዎች ተገኘች ተሾመና ካሳዬ ጌታሁን እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> ለስፌት ስራ የሚውሉ ጥሬ ቁሶችን ደንገል ፣ ተሊስ እና አጎበር ከዓባይና ጣና ሃይቅ ሙያውን የሚሰሩት ሴቶች እራሳቸው ከቦታው ድረስ በመሄድ ያመጣሉ፡፡ ከነዚህ የስፌት መስሪያ ተክሎች ጋር ተያይዘው ለስፌት ስራ ውጤቶች መስሪያነት እንዲሁም ውበትን ለመጨመር የሚያገለግሉ እንደ ግራምጣ ፣ አለላ ፣ ወስፌ ፣ ምላጭ ደግሞ ተገበያ በመግዛት የስፌት ስራችንን እንሰራለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት12 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 11 ጢስ ዓባይ



ከማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተገኘ

ፎቶ ግራፍ 12 ጣና ሃይቅ



13 ቀበሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ በአጥኚው የተነሳ

በአጠቃላይ ለስፌት ስራ የሚውሉ ጥሬ ቁሶች ከዓባይና ጣና ሙያተኞቹ በማምጣት እንዲሁም ከገበያ በመግዛት ለስፌት ስራ ይጠቀሙባቸዋል፡፡

## 4.1.3.የስፌት ስራ አሰራር ሂደት እና ደረጃዎች

በባህር ዳር ከተማ 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ አካባቢ በነገዴ ኅብረተሰብ የስፌት ስራ ሙያተኞች ዘንድ ከጥንት ጀምሮ እየተሰሩ ያሉና አሁንም ድረስ እየተሰሩ የሚገኙ የስፌት ስራ ውጤቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ የስፌት ስራዎች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ አገልግሎት እስኪሰጡና ለገበያ እስኪደርሱ ድረስ የተለያዩ የአሰራር ሂደቶችን ያልፋሉ፡፡ ይህንንም የአሰራር ሂደት ደረጃዎችን አስመልክተው የቀበሌ 16 ነዋሪና የስፌት ስራ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ እናና[6] አያሌው እንደሚከተለው ይናገራሉ፡-

> በመጀመሪያ ለስፌት ስራ የሚሆነው ደንገል የሚገኘው ከዓባይና ጣና ሲሆን ወንዶቹ በሽህም አልያም ደግሞ እኛው እራሳችን በባጃጅ በመደብ የታሰረውን ከ100 ብር እስከ 120 ብር ከሻጮች ላይ እንገዛለን፡፡ ተሂያ በኋላ ደንገሉን በፀሃይ እናደርቀውና የፈለግነውን ወይም ደግሞ የታዘዝነውን የስፌት ዓይነት በወስፌ ከሰነጠቅን በኋላ በቪላ ከስሩ እንቋጥረዋለን፡፡ ከላይ ተሊሱን በማዞር አጎበሩን በየመሃሉ እያዞርን ተዚያ ወዲህ በውሃ እያራስን እንሰፋለን፡፡ ተላያቸው ላይ የተለያዩ ቅርፆችን ጌጦችን እንሰራለን ምህኒያቱም ዲዛይን እያወጣን ለመሸጥ ሰውን ለመሳብ ስለሚጠቅመንና በሰዎች ትዕዛዝ እላያቸው ላይ ቅርፆችን እንሰራለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት12 ቀን 2011ዓ.ም)

በመስክ ምልከታዬ ወቅት የስፌት ስራ ለመስራት ወ/ሮ አናና አያሌው የጠቀሷቸውን ተግባራት የመቁረጥ ፣ የማድረቅ ፣ የመስፋት እና የማስጌጥ ተግባራትን ለመመልከት ችያለሁ፡፡

[6] እናና ማለት በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ ለሴቶች የሚሰጥ የአክብሮት ስም ነው፡፡

እያንዳንዱ የአሰራር ሂደት የባለሙያዎቹን ጉልበት ፣ ጊዜ ፣ ገንዘብና ጥበብ የሚጠይቅ ነው። ሂደቶቹም ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። እያንዳንዱን የስፌት ደረጃ በቅደም ተከተል እንመልከት።

## 4.1.3.1.የመቁረጥ ተግባር

በስፌት ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ለመጠቀሚያ ቁስነት ደረጃ የሚደርሱት ብዙ ሂደቶችን በማለፍ ነው። ከነዚህ ሂደቶች ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው ደንገል የመቁረጥ ተግባር ነው። በመስክ ምልከታዬ ወቅት ለስፌት የሚሆነውን ደንገል ሲቆርጡ ለመመልከት አልቻልኩም። ምክንያቱም ደንገሉን የሚቆርጡት እኩለ ለሊት በመሆኑ ነው። ይህም የሆነበት ምክኒያት መንግስት ደንገሉን እንዳይቆርጡ በማድረጉና በሚቆርጡት ላይ ህጋዊ እርምጃ ስለሚወስድ ነው። በመሆኑም ከመረጃ አቀባዮቼን በመጠየቅ የደንገል መቁረጥ ተግባርን በሚመለከት መረጃ ማግኘት ችያለሁ።

የስፌት ባለሙያዎቹ ቁሶችን ለመስራት ሲያቅዱ ተቀዳሚው ተግባር ደንገል የመቁረጥ ተግባር መከወን ነው። በዚህ ወቅት ለመቁረጫነት የሚያገለግለውን መሳሪያ ማጭድ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ደንገሉን ለመቁረጥና ለመያዝ የሚያገለግሉ ቁሶች ማጭድና ታንኳ በመያዝ ወደ ዓባይና ጣና ያመራሉ።

ፎቶ ግራፍ 13 ነገዴዎች ደንገል ቆርጠው ሲመለሱ



ጣና 13 ቀበሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ጀርባ በአጥኚው የተነሳ

ፎቶ ግራፍ 14 የተቆረጠውን ደንገል ከታንኳ ላይ በሸክም ሲያወርዱ



ከመረጃ አቀባዮች ላይ የተገኘ

ዓባይና ጣና ከደረሱ በኋላ ባለሙያዎቹ ጎረቤታሞች ከሆኑ ፣ እርስ በእርሳቸው የሚግባቡ በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ የሚተጋገዙ ከሆነ በመረዳዳት በህብረት ደንገሉን ይቆርጣሉ። ነገር ግን በግላቸውም የሚቆርጡ በርካታ ናቸው። ደንገሉን የመቁረጥ ተግባር የሚያከናውኑት

በአብዛኛው ወንዶች ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ ሴቶች እራሳቸው በእግራቸው ውሃ ውስጥ ገብተው ደንገሉን ይቆርጣሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ግርማ ብርሃኑ ፣መጋቢት12 ቀን 2011ዓ.ም)

## 4.1.3.2.የማድረቅ ተግባር

የስፌት ባለሙያዎቹ ለቁሶች መስሪያ የሚያገለግለውን ደንገል ቆርጠው ካመጡ በኋላ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ከዓባይና ጣና ተቆርጦ የሚመጣውን ደንገል ለአንድ ሳምንት በፀሃይ እንዲደርቅ ያደርጉታል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ደንገሉ ሲደርቅና የስፌቱ ውጤት ሲሰራ የሚዞረው አክርማው እንዲያምርና ለስፌት ስራው እንዳያስቸግር ለመቁረጥና ለመሰነጣጠቅ ስለሚያመች እንዲሁም የሚሰራው ዕቃ ጠንካራ እንዲሆን ስለሚረዳ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 15 ፀሃይ ላይ የተሰጣ ደንገል



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

## 4.1.3.3.ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር

ደንገሉ ቁሶቹን ለመስራት አመቺነት ባለው መልኩ ከተዘጋጀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የደረቀውን ደንገል ወደ ጥላ ቦታ ይዞ መሄድ ነው፡፡ በማስከተልም ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር ይጀመራል፡፡ ቁሶቹ በሚሰሩበት ጊዜ የደረቀውን ደንገል እጅ እንዳይቆርጥ እና ለመስራት እንዳያስቸግር በውሃ እየነከሩ እንደሚሰፉ በመስክ ምልከታዬ አረጋግጫለሁ፡፡

ፎቶ ግራፍ 16 እናና ቢያዝን የመሶብ ክዳን ሲሰሩ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

የቁሶቹ መጠንና ቅርፅ በኅብረተሰቡ ውስጥ ምን ትዕምርት አላቸው? ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በተለያየ ቅርፅና መጠን የሚሰሩት ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? የቁሶቹ መጠንና ቅርፅ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር በቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

በቁሶቹ በአንድ ላይ አብረው ተሰብስበው መብላት መጠጣታቸው በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የአብሮነት ባህል ሊያሳዩ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሚሰሩት ለቤት ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት በመነሳት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቁሶቹን በመዋዋስ እንዲሁም በጋራ በመስራት ቁሶቹ የኅብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ፣ ባህል ፣ ወግ ፣ እምነት እንዲሁም ፍልስፍና በቅጡ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

## 4.1.3.4.ቁሶቹን የማስጌጥ ተግባር

ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ከሰሩ በኋላ ያለውን ሂደት የሚያሳይ ነው፡፡ ስፌቱን የተለያየ ቀለም ባለው አለላ እና ቆዳ ወይም ላስቲክ ለተጠቃሚ እይታ አስደሳች የሆኑ ቅርፆችን ያወጡላቸዋል ያስጌጧቸዋል፡፡ ቁሶቹን በማስጌጥ ተግባር ላይ ከኅበረሰቡ ውጪ ያሉ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታም አለ፡፡

ባለሙያዎቹ በቁሶቹ ላይ የተለያዩ ቅርፆችን የሚሰሩት ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ባለሙያዎቹ በቁሶቹ ላይ የተለያዩ ቅርፆችን የሚሰሩት የሰዎችን ቀልብ ለመሳብና በሰዎች ትዕዛዝ ነው፡፡ በርግጥ በቅርፆቹ አማካኝነት የራሳቸውን የህይወት ፍልስፍና ባይገልፁም ቁሶቹ የሚሰሩበት ዋነኛ ጥሬ ቁስ ደንገል የኅብረተሰቡን የህይወት ፍልስፍና ሊያሳይ የሚችል ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 17 የማስጌጥ ተግባር



03 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

በአጠቃላይ ለስፌት ስራ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው በማካተት የስፌት ስራ ሂደቱ ተወጥኖ እንደሚጀመር በመስክ ቆይታዬ መመልከት ችያለሁ፡፡ በመቀጠል የስፌት ስራ ውጤቶችን አሰራርና አገልግሎት በዝርዝር እንመልከት፡፡

## 4.1.4.የስፌት ስራ ውጤቶች ዓይነት የአሰራር ሂደትና አገልግሎት

በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የሚሰሩ የስፌት ስራዎች ዓይነት አሰራርና አገልግሎት የሚመለከት ሲሆን መረጃ የተሰበሰበባቸው የስፌት ስራ ውጤቶች ብዛት አስራ አንድ ናቸው፡፡ እነሱም መሶብ ፣ አገልግል ፣ ቁና (ወራንታ) ፣ ወንፊት ፣ ወለወል (ወለል) ፣ ሰበጥራ ፣ ሰፌድ ፣ ሙዳይ ፣ የጀበና ማስቀመጫ (ማቶት) ፣ ሌማት (ቀለም ሻሽ) እና ታንኳ ናቸው፡፡ እነዚህ የስፌት ስራ ውጤቶች ከሳር ዓይነት ጥሬ ቁሶች የተሰሩ በመሆናቸው በአንድ ምድብ ማስቀመጥ ይቻል እንጂ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ ግን ይለያያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከአሰራርና አገልግሎት አንፃር በመመደብ በፎቶ ግራፍ በማስደገፍ እንደሚከተለው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

### 4.1.4.1.ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች

### መሶብ (ዝንበ ከልክል)

በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ መሶብ " ዝንበ ከልክል " ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህ መሶብ በመባል የሚታወቀው የስፌት ስራ ውጤት በባህላዊ መንገድ ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የሚሰራውም ከዓባይና ጣና ተቆርጦ ለሳምንት ያህል በፀሀይ እንዲደርቅ ከተደረገ በኋላ እንደ አስፈላጊነታቸው ከተሰነጣጠቁ የደንገል ተክሎች የሚዘጋጅ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 18 መሶብ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

የዚህን የስፌት ስራ ውጤት አሰራርን በማስመልከት ወ/ሮ እናና አያሌው የተባሉ የነገዴ ኅብረተሰብ አባልና የስፌት ስራ ባለሙያ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> የዘንባባ ዓይነት ቅርፅ ባላት አነስተኛ ቪላ የደንገል ተክል በቀለበት ዓይነት ቅርፅ ካዞርን በኋላ በደንብ የተሸነሸነውን ተሊስ በመሀሉ በማሾለክ ዙር በዙር እያሰርን በመያዝ በክብ ቅርፅ የዞረው ላይ መሀሉን በወስፌ በመሰንጠቅ አጎበሩን በምላጭ ጫፉን አሞጥሙጠን በቀዳዳው በማስገባት ከአናቱ ላይ በማዞር እንሰፋዋለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

ይህን ሂደትም በማስቀጠል ዙር በማዞር አስፈላጊው ቦታ አስራ አምስት ዙር ላይ ሲደርስ በዳርና በዳር በውሀ በማራስ ወደ ላይ አቃንተው ያስሩታል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ሲታጠፍ ደርቆ እንዳያስቸግርና በቀላሉ ለመስፋት እንዲያመችና የመሶቡን ሆድ (ግድግዳ) ለመስራት ነው፡፡ በመቀጠል የመሶቡ ግድግዳ ሲጠናቀቅ ከአናቱ አፍ ላይ አጎበሩ ይቋጠራል፡፡ ለዚህም መሶብ ግጣም ይሆን ዘንድ በእነርሱ አጠራር እፊያው ማለትም የመሶቡ መክደኛ ከመሶቡ አፍ

ላይ በመለካት ግጣሙን ይሰሩታል። በማስከተልም ለግጣሙ አንገት የሚሰሩለት ሲሆን ግጣሙን በእጅ በመያዝ ለመክፈትና ለመዝጋት እንዲያመች ተደርጎ የሚሰራ ነው።

ፎቶ ግራፍ 19 ወ/ሮ እናና ቢያዝን የመሶቡን ክዳን ለመስራት የመሶቡን አፍ ሲለኩ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

በመቀጠል በእፊያው ማለቂያ ጠርዝ ላይ ተሊሱ ሳይቋጠር ወደታችና ወደ ላይ በመከፋፈል በየመሃሉ ለስፌቱ ማስጌጫነት ላስቲክ እየከተቱ ከላዩ ላይ በተሊስ አለፍ አለፍ እያሉ ይሰፉታል። ከላይ በኩል ላስቲክ የሚለብሰው ድልድል ሲባል በታችኛው በኩል ደግሞ ላስቲክ የሚያለብሰው ጥርስ ያባላል። እነዚህም የመሶቡን እናትና እፊያ አፍ ለማያያዝ የሚረዱ ናቸው። በመጨረሻም ከእናቱ ወለወል(መቀመጫ) ስር ተሊስ በማዞር በአጎበር በመስፋትና ላስቲክ በማስገባት ለጉመው የመሶቡን መቀመጫ እግር በመስራት እንዲሁም መሶቡን ለማስዋብ የሚጠቀሙባቸው የተለያየ ቀለም ያላቸው የሳር ዓይነቶች አለላ፣ ሰበዝ፣ ወዘተ እና ዲዛይኖች ልዩ ውበትን በማጎናፀፍ ስራቸውን ጥበባዊ በሆነ መንገድ ያጠናቅቃሉ።

ፎቶ ግራፍ 20 ወ/ሮ እናና አያሌው መሶብ በላስቲክ ሲለጉሙ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

ጠንካራ ሴት በአንድ ሳምንት ደካማ ሴት በሁለት ሳምንት አንድን መሶብ ሰርታ ትጨርሳለች፡፡ በመጨረሻም ወደ ገበያ ይዘው ይወጡና ለገበያ ያውሉታል፡፡ አንድ የነገዴ ኅብረተሰብ መሶብ 500 ብር እንደሚሸጥ መረጃ አቀባዮቼ ወ/ሮ ተገኝች ተሾመና ወ/ሮ ካሳዬ ጌታሁን (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

መሶብ መጠኑ በምናይበት ጊዜ የአፉ ዙርያ 1.70 ሜትር ፣ የመደቡ ስፋት 40 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ 50 ሳ.ሜ ነው፡፡ የክዳኑ መጠን ደግሞ የአፉ ዙርያ 1.70 ሜትር ፣ ቁመቱ 30 ሳ.ሜ ነው፡፡ የመሶቡና የክዳኑ የአፍ ዙርያ እኩል የሆነበት ምክንያት ሁለቱም እኩል በአንድ ላይ መግጠም ስላለባቸው ነው፡፡

መሶብ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን በአብዛኛው ለእንጀራ ማስቀመጫነት ፣ አልፎ አልፎ ዳቦና ጥራጥሬ ለማስቀመጥ በገጠርም ሆነ በከተማ ውስጥ ይህን የስፌት ውጤት ኅብረተሰቡ ይጠቀምበታል፡፡ ይህ ቁስ እንጀራን ለተወሰኑ ቀናት እንዳይበላሽና በቀላሉ ሊበክሉት ከሚችሉ ነፍሳት ለመከላከል ጠቀሜታ አለው፡፡

ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በ03 ቀበሌና 16 ቀበሌ የነገዴ ማህበረሰብ የስፌት ስራ ባለሙያዎች ይህንን የስፌት ስራ በሚሰሩበት ጊዜ በመሀል በመሀል ክፍተት የሚተውት መሶቡ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በቀላሉ ንፋስ ወደ ውስጥ እንዲገባና ምግቡ እንዳይበላሽ በማሰብ ነው፡፡ ይህን የመሶብ አገልግሎት በማስመልከት የስፌት ባለሙያዋ እናና ዘመድ እንደሚከተለው ትገልፃለች፡፡ " በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ መሶብን የምንሰራው ከደንገል ተክል ሲሆን ይህን ተክል በቀላሉ በፀሀይ የሚደርቅና የስፌት ስራው ከተሰራበት በኋላ ውስጡ

የሚገባው ምግብ በሙቀት እንዳይበላሽ እና ነፍሳት እንዳይገባበት ያደርጋል፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 21 እንጀራ የያዘ መሶብ



16 ቀበሌ ወ/ሮ እናና ቢያዝን መኖርያ ቤት በአጥኚው የተነሳ

## ሰበጥራ[7]

ይህ የስፌት አይነት በክብ ቅርፅ የሚሰራ  ዝርግ የሆነ የስፌት ዓይነት ነው፡፡ የዚህ የስፌት ዓይነት አሰራር ሂደት ደርቀው ከተቀመጡ የደንገል ተክሎች የሚሰራ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ   22 ሰበጥራ



ስቱዲዮ ውስጥ በካሜራ ባለሙያ የተነሳ

ይህንኑ አስመልክቶ በቀበሌ 16 ነዋሪ የሆኑት የስፌት ሙያተኛ ወ/ሮ እማ ዘመድ ሲገልፁ

ደንገሉ መጀመሪያ ላይ በቀለበት መሰል አሰራር ይቋጠርና ዙር በማዞር ይወጠናል፡፡ በመቀጠል ከገበያ ላይ ግራምጣ ፣ አለላና ሰበዝ በመግዛት በተወጠነው ላይ አለላ በየመሀሉ

[7] ሰበጥራ በብዛት የሚታወቀው ሰፌድ በሚለው ስያሜ ቢሆንም በነገዶ ኅብረተሰብ ዘንድ ሰበጥራ ተብሎ ይጠራል፡፡

በመክተት በሰበዝ ይሰፋል፡፡ ከገበያ ላይ ግራምጣ ፣ ሰበዝ ፣ አለላ በደንገሉ ላይ የሚጨመረው ስፌቱ ቀጠን ያለና ውበት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡ በሰበዝ የተሰፋውን ግራምጣ ዙር በዙር በውሃ በማራስ ስፌቱ ይቀጠላል፡፡ ውሃ በየመሀሉ የሚነከረው እጅ እንዳይቆርጥና እንዳያስቸግር ሲሆን ስፌቱ ክብ ዓይነት ቅርፅ ሲይዝ ይበቃዋል ተብሎ ሲገመት ወይም ሰላሳ አምስት ዙር ላይ ሲደርስ ሰበዙን በተደጋጋሚ በመቋጠር በምላጭ ይቆረጣል፡፡(ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

በማለት የሰበጥራ አሰራርን አብራርተውልኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የ03 ቀበሌ ነዋሪና የስፌት ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ተገኘች ተሾመ የሰበጥራ አሰራርን እና ቁሱን ለመስራት የሚያስፈልገውን ጊዜ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

ሰበጥራ ብዙውን ጊዜ የሚሰራው ከደንገል ሳይሆን ከግራምጣ ፣ አለላ እና ከሰበዝ ነው፡፡ ምክኒያቱም ብዙ ጊዜ ተጠቃሚዎች ለእንጀራ ማውጫነት ስለሚፈልጉት ደንገሉ ከሆነ ይወፍራል እንደ ልብ እንጀራውን ለማውጣት ያስቸግረናል ስለሚሉ በደንገል አንሰራም፡፡ በግራምጣ አለላና ሰበዝ የሚሰራው ቀጠን ቀጠን ያሉ ስለሆኑና በሚሰሩበት ሰዓትም ብዙ የመወፈር ነገር ስለማይታያባቸው በክበደትም ከደንገሉ ያነሱ በመሆናቸው ከገበያ በመግዛት እንጠቀምባቸዋለን፡፡ ከገበያ የገዛነውንም በግራምጣ ከወጠንን (ከጀመርን) በኃላ ከላይ በኩል በክብ ቅርፅ አለላ በማዞር ሰበዙን በውሃ እየነከርን መሀል መሀሉን በወስፌ በመክፈት በአለላውና በግራምጣው መሀል ሰበዙን እንሰፋዋለን፡፡ በመጨረሻም ቅርፁ ከተፈለገው ቦታ ሰላሳ አምስት ዙር ላይ ሲደርስ ግራምጣውን ጫፉ ላይ በሰበዝ በመቋጠር የተቋጠረውን ጫፍ በምላጭ በመቁረጥ እናጠናቅቃለን፡፡ አንድ ሰበጥራ ለመስራት ቢያንስ አንድ ሳምንት ይፈጅብናል፡፡ በወር ውስጥ እስከ አራት ወይም አምስት ሰበጥራ እንሰራለን፡፡ የአንድ ሰበጥራ ዋጋም 120 ብር ነው፡፡ ከኛ ገዝተው እላዩ ላይ የተለያዩ ጌጣጌጦችን የሚሰሩት ሌሎች ናቸው፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

ሰበጥራ እንደሌሎቹ የስፌት ውጤቶች ከዓባይና ጣና ተቆርጦ በመጣ ደንገል የሚሰራ ሲሆን ባለሙያዎቹ ከተጠቃሚው ፍላጎትና ምርጫ አኳያ ከገበያ ላይ ግራምጣ ፣ አለላና ሰበዝ በመግዛት በአብዛኛው በነዚህ ግብአቶች የሚሰራ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

በመሆኑም ሰበጥራው ውስጥ ግራምጣና አለላ በመቋጠር ዙር በዙር እያዞሩ በቀጫጭኑ ተሰንጥቀው ከገበያ የተገዙትን ሰበዝ በየመሀሉ በወስፌ በመክፈል በውሃ በማራስ ሰበዙ ደርቆ

እጃቸውን እንዳይቆርጣቸውና የስፌቱ አክርማም እንዲያምር ካደረጉ በኋላ የስፌት ውጤቱን ያስሩታል፡፡ ይህን የስፌት ውጤት አለላ ፣ ግራምጣና ሰበዝ በሚጠፋበት ጊዜ በደንገል እንደሚሰሩት በመስክ ቆይታዬ መመልከት ችያለሁ፡፡

የሰበጥራን መጠን በምናይበት ጊዜ ዙርያው 2 ሜትር ፣ መደቡ 60 ሳ.ሜ እና ቁመቱ ደግሞ የግራምጣው 0.5 ሳ.ሜ የደንገሉ 1 ሳ.ሜ የሚደርስ ነው፡፡

ሰበጥራ የሚባለው የስፌት ውጤት ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የተለያዩ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን እነሱም፡-

- ለእንጀራ ማውጫነት፡- ይህም ሴቶች እንጀራ ጋግረው ከምጣዱ ላይ ለማውጣት የሚጠቀሙበት ሲሆን እንጀራውን ከምጣዱ ላይ በሚያወጡበት ጊዜ እጃቸውን እሳት እንዳይፈጃቸው እና እንጀራውም ሳይቆራረስ ወደ መሶብ ላይ ከመሸጋገሩ በፊት ንፋስ እንዲያገኘው የሚደረግበት የስፌት ውጤት ነው፡፡
- ለእህል ማበጠሪያነት ፡- እህል በአንድ ላይ ካስቀመጡ በኋላ ገለባውን በማስወገድ ጥቅም ይሰጣል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ሰበጥራው ጫፍ ላይ በእጃቸው በመያዝ ወደ ግራ ወደ ቀኝ በማራገብና ከዚህ በተጨማሪም ለጥራጥሬ ማበጠሪያነትም በመሆን ያገለግላል፡፡ በመስክ ወቅት በወፍጮ ቤቶች ፣ በቤት ውስጥ ይህን የስፌት ውጤት ኅብረተሰቡ ሲጠቀምበት መመልከት ችያለሁ፡፡
- ለጌጣጌጥነት ፡- ይህን የስፌት ውጤት በተለያዩ የባህል ምግብ አዳራሾችና የባህል ምሽት ቤቶች  በስፌቱ ዙሪያ ዳር ላይ ዶቃ ተሰፍቶበት ለጌጣጌጥነት ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ባለሙያዎች ከነገዶዎች ላይ በመግዛት የግድግዳ ሰዓት መቁጠሪያ እላያቸው ላይ በመግጠም ለገበያ ያውሉታል፡፡ አልፎ አልፎም ለብቻቸው በግድግዳ ላይ ተሰቅለው ባህልን እያስተዋወቁና ለቤቶቹ ድምቀትና ውበትን እየሰጡ እንደሚገኙ በከተማዋ ባደረኩት ቅኝት ለመመልከት ችያለሁ፡፡

## የጀበና ማስቀመጫ (ማቶት)

ይህ የስፌት ውጤት ግድግዳው ክብ የሆነ ሲሆን መሀሉ ደግሞ ክፍት ተደርጎ የሚሰራ የስፌት ስራ ውጤት ነው፡፡ የጀበና ማስቀመጫ አሰራርን አስመልክቶ የ03 ቀበሌ ነዋሪና የስፌት ባለሙያ የሆኑት ናናዬ ገዳም እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

የጀበና ማስቀመጫ ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው ከዓባይና ጣና ተቆርጦ በሚመጣው ደንገል የሚሰራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከግራምጣ በተገመደ ቃንጫ (ገመድ) የሚሰራ ነው፡፡ አሰራሩም በመጀመሪያ በጀበናው መቀመጫ ልክ በመለካት ስራው ልክ እንደማንኛውም የስፌት ስራ የሚሰራ ሲሆን ከግራምጣ በተገመደ ገመድ አማካኝነት ድርና ማግ ሆኖ ግድግዳ ብቻ የሚሰራለት ነው፡፡ በመሀሉ ላይ አለላ ጣል ጣል በማድረግ አለፍ አለፍ ተደርጎ ይሰፋለታል፡፡ አለላው ይበልጥ ውበትን እንዲጎናፀፍ ያደርገዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 23 የጀበና ማስቀመጫ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

ከደንገል የሚሰራው የጀበና ማስቀመጫ በመጀመሪያ ልክ እንደሌሎች የስፌት ውጤቶች ደንገሉ ተሰንጥቆ በቀለበት ቅርፅ ይቋጠርና ይወጠናል፡፡ በመቀጠልም በተቋጠረው ደንገል መሀል አጎበሩን ለማሾለክ ዙር በማዞር ከላይ ተሊሱን በመስፋት ከ4-5 ዙር ላይ ሲደርስ ወዲያው በውሃ በመንከር አንገቱን ወደላይ በማቃናት ይሰበርና ይሰፋል፡፡ በመጨረሻም የሚፈለገው መጠን ላይ ሲደርስ ወይም የጀበና መቀመጫውን ሲያክል ይበቃዋል ተብሎ ሲታሰብ ተሊሱ በአጎበር ይቋጠርና ይቆረጣል፡፡

የጀበና ማስቀመጫ መጠኑ የተለያየ ነው ፤ ምክኒያቱም ደግሞ የጀበናዎች መጠን ስለሚለያይ ነው፡፡ አንድን የጀበና ማስቀመጫ ለመስራት ከ1-3 ሰዓት የሚፈጅ ሲሆን የአንዱ የጀበና ማስቀመጫ ዋጋም ከ20 ብር ያልበለጠ መሆኑን ባደረኩት ምልከታ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

የጀበና ማስቀመጫ ልክ እንደስሙ ሴቶች በቤት ውስጥና በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቡና በሚያፈሉበት ጊዜ ጀበና ለማስቀመጫነት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ጀበና ከሸክላ የሚሰራ ቁስ በመሆኑ እንዳይጎዳ እንዲሁም የጀበና የታችኛው ክፍል ቅርፅ ክብ በመሆኑ

መሬት ላይ ረግቶ መቀመጥ ስለማይችል በስርዓቱ ለማስቀመጥ እንዲያገለግል ተደርጎ የሚዘጋጅ አንዱ የስፌት ውጤት ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው የጀበና ማስቀመጫ ጥቅም በተጨማሪ ልክ እንደሌሎቹ የስፌት ውጤቶች በተለያዩ የባህል ምግብ አዳራሾች እና የባህል ምሽት ቤቶች ውስጥ በተለይ ደግሞ የቡና ጠጡ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቦታዎች ላይ በግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ለጌጣጌጥነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡

## 4.1.4.2.ለእርሻ ስራ የሚያገለግሉ የስፌት ቁሶች

### ቁና(ወራንታ)

ይህ የስፌት ስራ ውጤት ከግራምጣ የሚሰራ ሲሆን ትልቁ ወራንታ ትንሹ ደግሞ ቁና ይባላል፡፡ የአሰራር ሂደቱም በመጀመሪያ ከመሀሉ ላይ ወጣ ብሎ የሚታይ ቅርፅ በማስያዝና በውሀ በማራስ ወደ ላይ በማቃናት የሚሰራ ሲሆን በአለላና በግራምጣ በመቀላቀል በማስዋብ የሚሰራ ነው፡፡ በብዛት ይህ ቁስ መቀመጫው ላይ እና ከንፈሩ ላይ ስለሚጎዳ የመለጎሙ ስራ ሚከናወነው በዚህ የቁስ አካል ላይ እንደሆነ ከመረጃ አቀባዩ ወ/ሮ ተገኝች ተሾመ ጋር ባደረኩት ውይይት (ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም) ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የቁና (ወራንታ) አሰፋፍን በተመለከተ የ16 ቀበሌ ነዋሪና የስፌት ስራ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ እማ ዘመድ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

> ወራንታ ሰፋ ያለው ሲሆን በመጠኑ ከቁና ይበልጣል፡፡ መደቡ እንደ ሰፌድ ሰፋ ያለ ሲሆን ዙሩ በጨመረ ቁጥር ወደላይ ሰበር እያለ ይሰፋል፡፡ የቁና አሰፋፍም በዚሁ መልክ ነው፡፡ ግን ጠባብና አነስ ያለ ነው፡፡ ወራንታውን ቀጠን አድርገን የምንሰፋው ከሆነ እስከ 50 ዙር እንሰፋለን፡፡ ካወፈርነው ግን ዙሩ 40 ላይ ሲደርስ እንቆርጠዋለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተሰፋ በኋላ አንዳንዶች በቆዳ ይለጉሙታል፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም)

ወራንታ በጋሻ መልክ ወይም ቅርፅ የሚሰፋ ነው፡፡ መጠኑ በምናይበት ጊዜ የአፉ ዙርያ 2 ሜትር ፣ የመደቡ ስፋት 0.30 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ 0.20 ሳ.ሜ ነው፡፡ የቁና መጠን ደግሞ የአፉ ዙርያ 1 ሜትር ፣ የመደቡ ስፋት 0.15 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ 0.10 ሳ.ሜ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 24 ወራንታ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ


ወራንታ ተሰርቶ ካለቀ በኋላም የሚሰጠው አገልግሎት ሰዎች በአውድማ ምርት በሚያመርቱበት ወቅት ለእህል መስፈሪያነት የሚጠቀሙበት እና ለሰዎች የእህል ብድር ለማበደር እንደ መስፈሪያነት የሚገለገሉበት ቁስ ነው፡፡ ቁና ደግሞ በቤት ውስጥ ቡና በሚፈላበት ወቅት ለቡና ቁርስ ማቅረቢያነት እና የተቆላውን ቡና ለማውጣት ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ልክ እንደ አገልግል በተለያዩ መኖሪያ ቤቶችና የባህል ቤቶች ውስጥ በግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ውበትን ለቤቱ ያጎናፅፋል፡፡

ፎቶ ግራፍ 25 የተቆላ ቡና በቁና ላይ



16 ቀበሌ መኖርያ ቤት ውስጥ በአጥኚው የተነሳ

ፎቶ ግራፍ 26 ፈንድሻ በቁና ላይ



03 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

## ወንፌት

ወንፌት ከግራምጣና ከሰበዝ የሚሰራ የዕለት ተዕለት መገልገያ ቁስ ነው፡፡ የአሰራር ሂደቱም መሀሉ በክብ ቅርፅ ከተሰራ በኂላ ዙርያውን በግራምጣ እና በሰበዝ አማካኝነት ከፍ ተደርጎ በዙር ይሰራል፡፡ መሃሉ ደግሞ ከግራምጣ በተገመደ ገመድ አማካኝነት ድርና ማግ ሆኖ የሚሰራ ነው፡፡ ይህን ቁስ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግልና ውበት እንዲኖረው ሲባል ወንፌቱ የላይኛው ክፍል ዙርያውን በቆዳ ይለበጣል፡፡

የወንፌት አሰራርን አስመልክቶ የ03 ቀበሌ ነዋሪና የስፌት ስራ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ አንሻ ቸሩ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-

> ግራምጣ እንሰነጥቅና በውሃ አርሰን እንፈትላለን፡፡ መደቡን ከስንዝር በሚበልጥ ሁኔታ እንጎነጉነውና ዙርያውን እየጠቀለልን እህሉን ደግፎ የሚይዘውን ግድግዳ በሰባት ዙር በደንገል እንሰፋለን፡፡ በመደቡ ደግሞ ዳርና ዳር ዙርያውን እግር በሁለት ዙር እንሰፋለታለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም)

" በአሁኑ ወቅት ይህ ቁስ ግድግዳው ከደንገል እና መሀሉ ከሸቦ በተሰራ ወንፌት እየተተካ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም በፊት የሚሰራው ከግራምጣ የተገመደ ገመድ ለረጅም ጊዜ ስለማያገለግል እና ስፌቱ ረጅም ጊዜ ስለሚፈጅ  ነው፡፡ " (ቃለመጠይቅ፣ተገኘች ተሾመ፣መጋቢት 17 ቀን 2011ዓ.ም) ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የስፌት ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና የተጠቃሚው ማህበረሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሱ ድሮ ከሚሰራበት መልክ እና ጥሬ ቁስ በአሁኑ ወቅት የተቀየረ መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡

ፎቶ ግራፍ 27 ወንፌት



ስቱዲዮ ውስጥ በካሜራ ባለሙያ የተነሳ

ፎቶ ግራፍ 28 የሸቦ ወንፌት



03 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

ወንፊት መጠኑ በምናይበት ጊዜ የአፉ ዙርያ 1.20 ሳ.ሜ ፣ የመደቡ ስፋት 0.30 ሳ.ሜ ፣ ቁመቱ 0.8 ሳ.ሜ ፣ የእግሩ ቁመቱ ደግሞ 0.3 ሳ.ሜ ነው፡፡

ይህ ቁስ በእርሻ ቦታ ፣ በቤት ውስጥ እና በወፍጮ ቤት ውስጥ የተለያዩ እህሎችን ለመንፋት የሚያገለግል ነው፡፡ እህሉን ከቆሻሻው ለመለየት የሚያስችል ቁስ ነው፡፡ ሰዎች በአውድማ ምርት በሚያመርቱበት ወቅት ምርቱን ከግርዱ ለመለየት ይገለገሉበታል፡፡

## ሰፌድ

ይህ የስፌት ውጤት ልክ እንደ ሰበጥራ አይነት ቅርፅ ያለው ሲሆን ከሰበጥራ የሚለየው ዳሩ ላይ ወደላይ የተቃና በመሆኑ ነው፡፡ ይህ የስፌት ውጤት የሚሰራው በብዛት ከግራምጣ ሲሆን የስፌት ስራው በመጀመሪያ ሰበጥራው ውስጥ ግራምጣና አለላ በመቋጠር ዙር በዙር እያዞሩ በቀጫጭኑ ተሰንጥቀው ከገበያ የተገዛውን ሰበዝ በየመሀሉ በወስፌ በመክፈል በውሃ በማራስ ሰበዙ ደርቆ እጃቸውን እንዳይቆርጣቸውና የስፌቱ አክርማም እንዲያምር ካደረጉ በኋላ የስፌት ውጤቱን ያስሩታል፡፡ ይህን የስፌት ውጤት አለላ ግራምጣና ሰበዝ በሚጠፋበት ጊዜ በደንገል እንደሚሰሩት በመስክ ቆይታዬ መመልከት ችያለሁ፡፡

የስፌት ስራው ቅርፅም በመጀመሪያ በክብ ቅርፅ ዙር በማዞርና ወደላይ በማቃናት በአለላና በግራምጣ እየቀላቀሉ በማስዋብ የሚሰራ ነው፡፡ አንድን ሰፌድ ሰርቶ ለማጠናቀቅ የአንድ ሳምንት ጊዜ የሚፈጅ ሲሆን አንዱ ሰፌድ እስከ 200 ብር ድረስ ይሸጣል፡፡ (ተገኘች ተሾመ፣ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም) ሰፌድ መጠኑ በምናይበት ጊዜ ዙርያው 2 ሜትር ፣ ቁመቱ ደግሞ የግራምጣው 0.5 ሳ.ሜ የደንገሉ ደግሞ 1 ሳ.ሜ ነው፡፡

ሰፌድ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ በእርሻ አውድማ ላይ እህል ለማበጠር ወይም ለማነፈስ የሚያገለግል ነው፡፡ ልክ እንደሌሎቹ የስፌት ውጤቶች በአለላ ያጌጠ ሰፌድ በተለያዩ የባህል ምግብ አዳራሾች እና የባህል ምሽት ቤቶች ውስጥ ለጌጣጌጥነት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 29 ሰፌድ



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

## 4.1.4.3.ለማህበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት የሚሰጡ የስፌት ቁሶች

### አገልግል

አገልግል ልክ እንደ መሶብ ዓይነት ቅርፅ ያለው የስፌት ውጤት ነው፡፡ ከመሶብ የሚለየው አነስ በማለቱና በሚሰጠው አገልግሎት ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ የስፌት ባለሙያ የሆኑ መረጃ አቀባዮቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት የአገልግልን አሰራር እንደሚከተለው ገልፀዋል ፡-

> አገልግል የሚሰራው ከደንገል ሲሆን ቪላ በመጀመሪያ በቀለበት መልክ በመቋጠር ልክ እንደሌሎቹ ስፌቶች በተሊሱ ከዞረ በኋላ ዙር በማዞር አለፍ አለፍ ብሎ ይሰፋል፡፡ በመቀጠል በዙር በዙር ከ6-7 እንደ አገልግሉ ማነስና መተለቅ በመለካት ከተሰፋ በኋላ የአገልግሉን መቀመጫ ወለል ተሰርቶ ሲያልቅ ከዳሩ ላይ ውሃ በማፍሰስ ደንገሉን በማራስ ወደ ላይ እንደ መሶብ ይሰበራል፡፡ በርግጥ መሶብ ሆዱ በጣም ሰፊ ሲሆነ አገልግል ግን ሆዱ ጠበብ ያለ ነው፡፡ ግድግዳው ተሰርቶ ካለቀ በኋላ እፊያውን ከላይ በማሾል ወደታች በማዞር በየመሀሉ በመስበር እፊያውን (ግጣሙን) ተሰርቶ ይጠናቀቃል ማለት ነው፡፡(ተገኝች ተሾመ፣ናናዬ ገዳም፣ መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም) በማለት ገልፀዋል፡፡

ከቀረበው ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው አገልግል የሚሰራው በመጀመሪያ ከዓባይና ጣና መጥቶ በደረቀ ደንገል ሲሆን የደረቀውን ደንገል በመቋጠር ይጀመራል፡፡ ከዚህ በኋላም የተቋጠረው ላይ በመሀሉ ተሊስ በማሾለክ ክብ በማድረግ ይጀመራል፡፡ የተጀመረው አጎበር ዙር በዙር በክብ ቅርፅ ከስድስት ዙር እስከ ሰባት ዙር ስፌቱ ሲደርስ በውሃ በመንከር ወደ ላይ ያስሩታል፡፡ ከላይ ታስሮ ያለው የአገልግሉ ግድግዳ ሲሆን ሙሉው ሲጠናቀቅ የአገልግሉ ሆድ ይሆናል፡፡ የታችኛውን የአገልግሉን ሆድ አፉን ከጨረሱ በኋላ በአጎበሩ በደንብ አድርገው በመቋጠር ለአገልግሉ ሆድ (እናት) እፊያ ግጣም ይሰሩለታል፡፡ ይህም አሰራሩ ልክ እንደ አገልግሉ ተወጥኖ ሲሆን ከአገልግሉ ሆድ የሚለየው ከላይ በቀጭኑ ያለው ክብ ወደታች የሚታጠፍና ጠበብ ያለ በመሆኑ ነው፡፡ በየመሀሉም ግጣሙ ከአፉ ጋር እየተለካ ይሰራል፡፡ የተሰራውን አገልግል በመግዛት እላዩ ላይ ቆዳ በመለጎም የሚሰሩት ሌሎች ናቸው፡፡ በቆዳ የሚለጎመው ውበት እንዲኖረው እና ለረጅም ዘመናት እንዲቆይ ሲባል ነው፡፡ አንድ አገልግል የቆዳውን ልጓም ሳያካትት ስፌቱ ብቻ ከአንድ እስከ ሶስት ቀን እንደሚፈጅ መረጃ አቀባዬ ወ/ሮ ተገኝች ተሾመ (ቃለመጠይቅ መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡ ይህም የሆነበት ምክኒያት እንደ ባለሙያዋ ችሎታ ፣ ጥንካሬ እና ፍጥነት የሚወሰን በመሆኑ ነው፡፡ ባለፉት ጊዜያት አገልግል

በግራምጣ ይሰራ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በደንገል የሚሰራ አገልግል በጣም ተፈላጊነቱ እየጨመረ ነው፡፡ ቢሆንም ግን በአሁኑ ጊዜ የግራምጣ አገልግል በብዛት አይሰራም ምክኒያቱም ዘመናዊ የምሳ መያዣዎች በመበራከታቸው ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣እናና ቢያዝን፣መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም) ይህም የሚያሳየው የስፌት ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና የተጠቃሚው ማህበረሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሱ ድሮ ከሚሰራበት መልክ እና ጥሬ ቁስ በአሁኑ ወቅት የተቀየረ መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡

ፎቶ ግራፍ 30 ወ/ሮ እናና ቢያዝን የደንገል አገልግል አሰራርን ሲያሳዩ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

የአንድ አገልግል ዋጋ በአሁኑ ጊዜ መቶ ብር ነው፡፡ በነገዴ ማህበረሰብ የሚሰራው አገልግል መጠኑ በምናይበት ጊዜ  የአፉ ዙርያ 80 ሳ.ሜ ፣ ቁመቱ ደግሞ 20 ሳ.ሜ ነው፡፡ ግጣሙ(ክዳኑ) ደግሞ የአፉ ዙርያ 80 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ 10 ሳ.ሜ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 31 በቆዳ የተለጎመ አገልግል



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

አገልግል የተለያዩ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል ፡-

- ትንሹ አገልግል በጋብቻ ወቅት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ተገኝች ተሾመ ሲገልፁ " በነገዶ ኅብረተሰብ አገልግል ለመዳሪያነት ያገለግላል፡፡ እናቶች አናት ላይ ተደርጎ የእንሶስላ ቅሌ እየተባለ ይኬዳል፡፡ " (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም)
- ለጌጣጌጥ ማስቀመጫነት ፡- በተለይ በገጠሩ ኅብረተሰብ ዘንድ አገልግልን የመዋቢያ ጌጣጌጦችን ለማስቀመጫነት ይጠቀሙበታል፡፡ አንዲት ልጃገረድ በምታገባበት ወቅት ከቤተሰቦቿ የሚሰጧትን የተለያዩ ቁሶችን ለማኖሪያነት የምትጠቀምበት ነው፡፡ ለምሳሌ መቀነት ፣ ሻሽ (የፀጉር ማሰሪያ) ፣ ድሪ ፣ የአንገት ክታብ ፣ አልቦና መሰል ጌጣጌጦችን ለማኖሪያነት የሚጠቀሙበት ቁስ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አገልግል ለማህበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት እንደሚውል መረዳት ይቻላል፡፡
- ለምግብ ማስቀመጫነት እና ለምግብ መቋጠሪያነት ፡- አገልግል ዘመናዊ የምሳ ዕቃዎች ባልተስፋፉበት ጊዜ ለምግብ መያዣነት ሲያገለግል የነበረ ነው፡፡ እስከ አሁንም ድረስ በገጠር አካባቢ በእርሻ ስራ ለተሰማሩ ሰዎች የምሳ መያዣ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቅቤ ፣ ማር ፣ ዳቦ ቆሎና መሰል የእህል ዘሮችን ኅብረተሰቡ በውስጣቸው ለማስቀመጫነት ይገለገልባቸዋል፡፡ ሰዎች ዘመድ ጥየቃ ፣ እስረኛ ለመጠየቅ እሩቅ ወዳለበት ቦታ ሲጓዙ ምግብ ይዘውበት ይሄዳሉ፡፡
- ለቤት ማስዋቢያነት ፡- አገልግልን የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች እና የባህል ቤቶች ውስጥ ግድግዳ ላይ በማንጠልጠል ለቤቱ ውበትና ድምቀት ሲሰጡ ባደረኩት ምልከታ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ አልፎ አልፎ በገጠር መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ለቤት ማስዋቢያነት ግድግዳ ላይ እንደሚሰቅሉ ለመወቅ ተችሏል፡፡

### ሙዳይ

ሙዳይ የሚሰራው ከደንገል ሲሆን ጥሬ ዕቃውም የሚገኘው ከዓባይና ጣና ነው፡፡ ይህ የስፌት ውጤት ከሌሎች የስፌት ውጤቶች በጣም ያነሰ እና ለመስራትም ብዙ ጊዜን የማይጠይቅ ነው፡፡ የ03 ቀበሌ ነዋሪና የስፌት ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ካሳዬ ጌታሁን የተባሉ ስለሙዳይ አሰራር ሲገልፁ ፡-

ይህ የስፌት ስራ አሰራር በመጀመሪያ ልክ እንደሌሎች የስፌት ውጤቶች ደንገሉ ተሰንጥቆ በቀለበት ቅርፅ ይቋጠርና ይወጠራል፡፡ በመቀጠልም በተቋጠረው ደንገል መሀል አጎበሩን ለማሾለክ ዙር በማዞር ከላይ ተሊሱን እየሰፋን ከ4-5 ዙር ላይ ሲደርስ ወዲያው በውሃ በመንከር አንገቱን ወደላይ በማቃናት እንሰብረውና ግድግዳ እንሰራለታለን፡፡ ግድግዳውም ወደ ላይ ከ8-10 ዙር ሲደርስ አፉን በመቋጠር በአጎበሩ እንቋጥረዋለን ፡፡ ቀጥሎም የሙዳዩን ግጣም እንሰራዋለን፡፡ ይህም ልክ እደ አገልግል ቆዳውን ሌሎች ባለሙያዎች ከእኛ ላይ በመግዛት በቆዳ ይለጉሙታል፡፡(ቃለመጠይቅ መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም)በማለት ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ሙዳይ የሚሰራው ከደንገል ተክል ሲሆን ቅርፁ አገልግል የሚመስል ነው፡፡ ነገር ግን ከአገልግል የሚለየው በጣም አነስተኛና ወደ ላይ ከፍ ያለ ሳይሆን አጠር ብሎ ወደ ጎን የሰፋ ነው፡፡ ይህ ስፌት በትንሹ ዙር በዙር ባለሙያዎቹ እየቆጠሩ ከሰፉ በኋላ ከጫፍ ላይ በመቋጠር የሙዳዩን መክደኛ በራሱ ዓይነት አሰራር ይሰሩታል፡፡

የሙዳይን መጠን በምናይበት ጊዜ  የአፉ ዙርያ 60 ሳ.ሜ ፣ ቁመቱ ደግሞ 8 ሳ.ሜ ነው፡፡ ግጣሙ(ክዳኑ) ደግሞ የአፉ ዙርያ 60 ሳ.ሜ ቁመቱ ደግሞ 1 ሳ.ሜ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 32 ሙዳይ



ስቱዲዮ በካሜራ ባለሙያ የተነሳ

ሙዳይ አገልግሎቱ ሰፊ ነው፡፡ በገጠሩ አካባቢ ለሙሽራ የመዋቢያ እቃዎች ጌጣጌጦች ማስቀመጫነት የሚውል ሲሆን ለሴቷ ሙሽራም ስም ለማውጫነት ይጠቀሙበታል፡፡ ይህም የወንዱ ሙሽራ ቤተሰቦች እናት ፣ አባት፣ አክስት እንዲሁም ወንድምና እህቶቹ በወረቀት በመፃፍ ማንም ሳያየው ተጠቅልሎ ሙዳዩ ውስጥ በመግባት ዕጣ ከተጣጣለ በኋላ ለሙሽሪት ስም ያወጣበታል፡፡ ይህ የምራት ስም የሙሽራው ቤተሰቦች ከጋብቻ በኋላ የሚጠሩበት አዲስ የሙሽሪት ስም እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ባደረጉት የቡድን ውይይት ገልፀዋል፡፡ (ካሳዬ ጌታሁን፣ስመኝ መርሻ፣መጋቢት 15 ቀን 2011ዓ.ም)

አንድ አንድ ቦታዎች ደግሞ ለምግብ ማስቀመጫነትም የሚውል ሲሆን በአብዛኛው ለኅብረተሰቡ ለእጣን ፣ ለባርከና ፣ ለሉባንጃ ፣ ለዋልያ ፣ ለከሴ ፣ ለወይራ ፣ ለጡንጂት ወዘተ ለሚጨሱ ጢሳ ጢሶች ማስቀመጫነት በመሆን ያገለግላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለባህላዊ ምግብ አዳራሾችና ምሽት ቤቶች ልክ እንደ አገልግል በግድግዳ ላይ በመንጠልጠል ለቤቱ ውበት በመስጠት እንደሚያገለግል ባደረኩት ቅኝት ለመመልከት ችያለሁ፡፡

## ሌማት (ቀለም ሻሽ)

ፎቶ ግራፍ 33 ሌማት (ቀለም ሻሽ)



ስቱዲዮ በካሜራ ባለሙያ የተነሳ

ሌማት አንዱ የነገዶ ኅብረተሰብ የስፌት ስራ ውጤት ሲሆን ልክ እንደመሶብ አይንት ሆኖ ሌማት ግን እግሩ ወደታች ረዘም ያለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሆዱ ግድግዳ መጠን ከመሶብ ያነሰ ነው፡፡ የመሶብ የሆዱ ግድግዳ መጠን አስራ አምስት ዙር ሲሆን የሌማት ደግሞ አስር ዙር ነው፡፡ መጠናቸው ይለያይ እንጂ በቅርፅና በአሰፋፍ ጥበብ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የሌማትን አሰራር አስመልክቶ ወ/ሮ ተገኘች ተሾመ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

> ሌማት ልክ እንደመሶብ የሚሰራ ሲሆን በመጀመሪያ ተሊሱን በቀለበት መልክ በመቋጠር ይወጠናል፡፡ ተሂያ በኋላ አለፍ አለፍ ብሎ ደንገሉ መሀል አጎበሩን ለማሾለክ ዙር በማዞር ከላይ ተሊሱን እየሰፋን በውሃ በመንከር አንገቱን ወደላይ በማቃናት እንሰብረውና ግድግዳ እንሰራለታለን፡፡ በመቀጠልም ግድግዳው ካለቀ በኋላ ግጣሙን (እፊያውን) በአፉ ልክ እንሰራለታለን፡፡ በመጨረሻም ከወለሉ ላይ እግር እንቀጥልለትና ወደታች በረጅሙ እንሰራለታል፡፡ ታስፈለገም በዐይነት በዓይነት እናውቅበታለን አለላ ጣል ጣል አድርገን እንሰፋለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም)

ሌማቱን ከጀመሩ በኋላ ዙር በማዞር አስፈላጊው ቦታ አስር ዙር ላይ ሲደርስ በዳርና በዳር በውሀ በማራስ ወደ ላይ አቃንተው ያስሩታል፡፡ ይህንኑ የሚያደርጉት ሲታጠፍ ደርቆ እንዳያስቸግርና በቀላሉ ለመስፋት እንዲያመችና የሌማቱ ሆድ (ግድግዳ) ለመስራት ነው፡፡ በመቀጠል የሌማቱ ግድግዳ በአስር ዙር ሲጠናቀቅ ከአናቱ አፍ ላይ አጎበሩ ይቋጠራል፡፡ ለዚህም ሌማት ግጣም ይሆን ዘንድ በእነርሱ አጠራር እፊያው ማለትም የሌማቱን መክደኛ ከሌማቱ አፍ ላይ በመለካት ግጣሙን ይሰሩታል፡፡ በማስከተልም ለግጣሙ አንገት የሚሰሩለት ሲሆን ግጣሙን በእጅ በመያዝ ለመክፈትና ለመዝጋት እንዲያመች ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡ በመቀጠል በእፊያው ማለቂያ ጠርዝ ላይ ተሊሱ ሳይቋጠር ወደታችና ወደ ላይ በመከፋፈል በየመሃሉ ለስፌቱ ማስጌጫነት ላስቲክ እየከተቱ ከላዩ ላይ በተሊስ አለፍ አለፍ እያሉ ይሰፉታል፡፡ ከላይ በኩል ላስቲክ የሚለብሰው ድልድል ሲባል በታችኛው በኩል ደግሞ ላስቲክ የሚያለብሰው ጥርስ ይባላል፡፡ እነዚህም የሌማት እናትና እፊያ አፍ ለማያያዝ የሚረዱ ናቸው፡፡ ለንሚዎቹ እራሳቸው የስፌት ባለሙያዎች ሲሆኑ በመጨረሻም ከእናቱ ወለወል(መቀመጫ) ስር ተሊስ በማዞር በአጎበር በመስፋትና ላስቲክ በማስገባት ለጉመው የሌማቱን መቀመጫ እግር ከላይ ጠበብ አድርገው ጀምረው ወደታች ሲወርድ ስፋቱን እየጨመሩ በመስራት እንዲሁም ሌማቱን ለማስዋብ የሚጠቀሙባቸው የተለያየ ቀለም ያላቸው የሳር ዓይነቶች አለላ፣ ሰበዝ፣ ወዘተ እና ዲዛይኖች ልዩ ውበትን በማጎናፀፍ ስራቸውን ጥበባዊ በሆነ መንገድ ያጠናቅቃሉ፡፡

አንድን ሌማት ሰርቶ ለመጨረስ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የሚፈጅ ሲሆን የአንዱ ሌማት ዋጋ ከ500 ብር በላይ ይሸጣል፡፡ የእግሩ ቁመት 80 ሳ.ሜ ፣ የእግሩ ዙርያ 1.30 ሳ.ሜ ፣ የአፉ ዙርያ 1.60 ሳ.ሜ እና መደቡ 30 ሳ.ሜ ሲሆን የግጣሙ(ክዳን) መጠን የአፉ ዙርያ 1.60 ሳ.ሜ ፣ ቁመቱ 30 ሳ.ሜ ነው፡፡

ሌማት (ቀለም ሻሽ) የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያሉት የስፌት ውጤት ሲሆን እነሱም ፡-

- ከኅብረተሰቡ መካከል አንድ ሰው ሲሞት ለማስተዛዘኛነት የሚውል ምግብ ሰዎች በመያዝ የሚወስዱበት የስፌት ውጤት ነው፡፡
- ሰዎች በቤታቸው ውስጥ በጋራ በመሆን ምግብ ለመመገቢያነት እንዲሁም ለማስቀመጫነት ይጠቀሙበታል፡፡ በባህላት ቀን ዳቦ ለመቁረሻነት ፣ ለመመገቢያነት እና ለማስቀመጫነት ይገለገሉበታል፡፡
- በተለያዩ የባህል ምግብ አዳራሾች ውስጥ ለምግብ ማቅረቢያነት እንዲሁም እንደ ምግብ ጠረጴዛ የሚያገለግል የስፌት ውጤት ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 34 ሌማት በቤት ውስጥ ለምግብ መመገቢያነት ሲያገለግል



ከማህበራዊ ሚዲያ የተገኘ

### 4.1.4.4.ለመጓጓዣነት አገልግሎት የሚውሉ የስፌት ቁሶች

#### ወለወል

ወለወል ከስፌት ስራ ውጤቶች መካከል አንዱ ሲሆን የሚሰራውም ከደንገል ነው፡፡ የወለወልን አሰራር በተመለከተ ወ/ሮ ካሳዬ ጌታሁን የተባሉ የ03 ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የስፌት ሙያተኛ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> ወለወል የሚሰራው እንደሌሎች የስፌት ውጤቶች ከደንገል ሲሆን በሌላ አካባቢም በግራምጣና አለላና ሰበዝ እንደሚሰራ ከሰዎች ሰምተናል፡፡ እኛ ግን የምንሰራው ከዓባይና ጣና ተቆርጦ በመጣው ደንገል ሲሆን ደንገሉን ተሊስ አስራ ሁለት ቦታ ከሰነጠቅን በኋላ በዙር ይቋጠርና በውስጡ አጎበሩ እንዲሾልክ በማድረግ ስራው ይጀመራል፡፡ በመቀጠልም ተሊሱን ዙር በዙር እየቀጠልን በቁጥር ከ13-15 ስፌቱ ዙር ሲደርስ በአጎበሩ በመቋጠር ስራችንን እናጠናቅቃለን፡፡ አልፎ አልፎ ግን በትዕዛዝ ትከሻ ያለው ወለወል እንሰራለን፡፡ ይህንንም የምንሰራው ከነበረው ወለወል ላይ አንድ ግድም ግድግዳ በመስራት ነው፡፡(ቃለመጠይቅ፣መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 35 ወ/ሮ ካሳዬ ጌታሁን ወለወል ሲሰፉ



03 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

ለወለወል መስሪያ የሚሆኑ ቁሶች ከዓባይና ጣና እንደሚገዙና በመሬት ላይ ተዘርረው ለተወሰነ ቀናት በፀሀይ እንዲደርቁ ተደርገው በወስፌ ከተሰነጠቁ በኃላ በቀላሉ በቀለበት መልክ ታስረው በውስጣቸው ተሊሱን እያሾለኩ በአጎበር ሲሰፉና ቁጥራቸውም ባለሙያዋ እንደገለፀችው ከ13-15 ዙር ሲደርስ እንደሚቋጠርና አልፎ አልፎም በሰዎች ትዕዛዝ በተሰራው ወለወል ላይ በአንድ በኩል እስከ ትከሻ ድረስ የሚደርስ ግድግዳ መሰል መደገፊያ ለከባድ መኪና አሽከርካሪዎች እንደሚሰሩ በመስክ ቆይታዬ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ የወለወል መጠን የመደቡ ስፋት 30 ሳ.ሜ ፣ ቁመቱ 2 ሳ.ሜ ሲሆን ዙርያው ደግሞ 60 ሳ.ሜ ነው፡፡

የወለወል አገልግሎት በአብዛኛው ይህን የስፌት ውጤት የሚጠቀሙበት የባጃጅ ሹፌሮችና እና በተወሰነ መልኩ የቤትና የከባድ ተሽከርካሪ ሹፌሮች ናቸው፡፡ ወለወል በባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚገኙ ባጃጅ አሽከርካሪዎች በብዛት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ባጃጅ በሚሾፍሩበት ጊዜ የሚቀመጡበት ከላስቲክ የተሰራ ወንበር በመሆኑ በቀላሉ ሙቀት የመሳብ አቅም አለው፡፡ በመሆኑም ሙቀቱ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣቸዋል፡፡ በዋናነት የኪንታሮት በሽታ ተጠቃሽ ሲሆን ይህን የስፌት ውጤት በመጠቀማቸው ስጋታቸው እንደሚቀንስላቸውና ወለወሉ ሙቀት የማይስብ መሆኑን እንዲሁም እንደ ባጃጅ ወንበር የማይጎረብጥ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ የባጃጅ ሹፌር የሆኑት መረጃ አቀባዬ ወንደሰን ጥበቡ ተናግረዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም) ከዚህ በተጨማሪም በወንዶች ፀጉር ቤት ፀጉራቸውን ለሚቆረጡ ሰዎች ለመቀመጫነት ያገለግላል፡፡

በሌላ በኩል የወለወል አገልግሎት በከተማዋ የሚገኙ የባህላዊ የምግብ አዳራሾችና ምሽት ቤቶች በግድግዳዎች ላይ ተሰቅለው የማስጌጥ አገልግሎት ሲሰጡ መመልከት ችያለሁ፡፡

ፎቶ ግራፍ 36 ወለወል (ወለል)



03 ቀበሌ ከገበያ ላይ በአጥኚው የተነሳ

## ታንኳ

ታንኳ የጀልባ ዓይነት ቅርፅ ያለው የውሃ ላይ መጓጓዣ ነው፡፡ ታንኳ ልክ እንደማንኛውም የስፌት አይነት ተቆርጦ በደረቀ ወፍራም ደንገል የሚሰራ ነው፡፡ ነገር ግን ታንኳ እንደ ሌሎች የስፌት ስራ ውጤቶች በሴቶች የሚሰራ ሳይሆን በወንዶች የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክኒያት ለታንኳ መስሪያ የሚያስፈልገው የደንገል መጠን እጅግ ከፍተኛና ከባድ በመሆኑ እና ለመስራት ከፍተኛ ጉልበትን የሚፈልግ ስለሆነ እንዲሁም የመስሪያ ቦታው ዓባይና ጣና ዳር በመሆኑ ነው፡፡

የአሰራር ሂደቱም ደንገሉን በረጅሙ መሬት ላይ በማጋደም ከገበያ በሜትር በተገዛ ገመድ አለፍ አለፍ ተደርጎ በእግር እየወጠሩ በውሃ እያራሱ ወደ ላይ በማቃናት ከዳርና ዳሩ ላይ በደንብ በገመድ በመወጠር ወደ መሀሉ ላይ ለቀቅ አድርገው በገመድ ያስሩትና ታንኳው ይበቃዋል ብለው ሲያስቡ ገመዱን ቋጥረው በምላጭ ይቆርጡታል፡፡ በመጨረሻም የታንኳውን መቀመጫ በአጫጭር ደንገሎች ደራርበው በገመድ በማሰር መቀመጫውን ይሰሩለታል፡፡ መቀመጫው የሚሰራበት ምክኒያት ታንኳው ሲሰራ ትንንሽ ቀዳዳዎች ስለሚኖሩት ውሃ እንዳያበሰብሳቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፎቶ ግራፍ 37 ጣና ዳር ታንኳ ሲሰራ



ከመረጃ አቀባዮች የተገኘ

ፎቶ ግራፍ 38 የታንኳ መቀመጫ



ጣና ዳር በአጥኚው የተነሳ

ታንኳ በተለያየ መጠን የሚሰራ ሲሆን እስከ አርባ ሰው ድረስ እንደሚይዝ ታንኳ ሰራተኛ የሆኑት መረጃ አቀባዩ በሃይሉ ግዛው (ቃለመጠይቅ መጋቢት16 ቀን 2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

ፎቶ ግራፍ 39 ለሰዎች መጓጓዣ



ጣና ሃይቅ በአጥኚው የተነሳ

ፎቶ ግራፍ 40 ለዓሳ ማጥመጃነት



ጣና ሃይቅ በአጥኚው የተነሳ

## 4.1.5.የስፌት ቁሶች ጠቀሜታ

የስፌት ቁሶች የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህም መካከል ማህበራዊ ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን ጠቀሜታዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው እንመልከት፡

- **ማህበራዊ ጠቀሜታ** ፡- የስፌት ውጤቶች በቤት ውስጥ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ ለምግብ ማቅረቢያነት ፣ ለምግብ ማስቀመጫነት ፣ ለቤት ማስጌጫነት ፣ ሙዳይ እና አገልግል ለጋብቻ ፣ ሌማት ለሀዘን አገልግሎት ፣ ወራንታና ሰፌድ በእርሻ ቦታ እንዲሁም ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚውሉ የስፌት ቁሶች ማህበራዊ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስፌት ባለሙያዎቹ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር እንደጠቀማቸው በመስክ ቆይታዩ ለመመልክት ችያለው፡፡
- **ባህላዊ ጠቀሜታ** ፡- የስፌት ቁሶች ካላቸው ጠቀሜታ መካከል አንዱ የሆነው ባህላዊ ጠቀሜታ ነው፡፡ የስፌት ውጤቶች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ የእለት ተእለት ተግባራትን

ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የኅብረተሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ ፍልስፍና ፣ ማንነት ፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማስተዋወቅ በኩል አስተዋፅዎ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ሙያውን ለተተኪው ትውልድ በማስተማር እንዲሁም ቁሶቹን ሰርቶ ባህልን ለማስተዋወቅ በሚደረግ ጥረት ነው፡፡

በዚህም መነሻ እሳቤ በስፌት ስራ በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውለው " ውሃ " ከኅብረተሰቡ ህይወትና ጥንት አመጣጥ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ሌላው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰዎች በጋራ በመሆን በሌማት ምግብ መመገባቸው እንዲሁም ቡና በሚፈላበት ጊዜ በቁና የቡና ቁርስ መብላታቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የአብሮነት ባህል የሚያሳዩና የሚያጠናክሩ መሆናቸው የኅብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ፣ ወግና ልማድ የስፌት ቁሶች በቅጡ የሚያሳዩ  መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የስፌት ቁሶቹን በተለያየ ቅርፅና መጠን የሚሰሩት ለቤት ውስጥ የዕለት ተዕልት መገልገያነት አመቺ አድርጎ ከመስራት የመነጨ ነው፡፡ በቁሶቹ ላይ የተለያየ ቅርፆችን የሚሰሩት በሁለት ምክንያት ሲሆን አንደኛው የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ቀልብ ለመሳብ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በተጠቃሚዎች ትዕዛዝ የተነሳ ነው፡፡

- **ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ** ፡- የስፌት ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው የኅብረተሰብ ክፍል ያቀርባሉ፡፡ ቁሶችን ለሚያበጁቸው ባለሙያዎች እንዲሁም ለተጠቃሚው የኅብረተሰብ ክፍል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ባለሙያዎቹ የሰሩትን ቁሶች በመሸጥ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመምራት የሚያግዝ ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ የስፌት ቁሶቹን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስመልከት ወ/ሮ ካሳዬ ጌታሁን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ " የስፌት ስራ ቋሚ የሁል ጊዜ ስራችን ነው፡፡ ስፌት እየሰራን እቁብ እየጣልን ልጆቻችንን እናስተምርበታለን ፣ ቤታችንን እናሟላበታለን፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት17 ቀን 2011ዓ.ም)

የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ደግሞ በሚፈልጉት መጠንና ቅርፅ ቁሶቹን በትዕዛዝ አሰርተው መጠቀም መቻላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ወ/ሮ እናና አያሌው እንደሚከተለው ገልፀውታል፡-

> የፈለግነውን ወይም የታዘዝነውን ስፌት እንሰፋለን፡፡ ተላያቸው ላይ የተለያዩ ቅርፆችን እንሰራለን ምህኒያቱም ዲዛይን እያወጣን ለመሸጥ ሰዎችን ለመሳብ ስለሚጠቅመን እና በሰዎች ትዕዛዝ እላያቸው ላይ ቅርፆችን እንሰራለን፡፡ በዲዛይን

ስሩልን ታሉን በዓይነት በዓይነት እናውቅበታለን እንሰራላቸውን እንሸጣለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት17 ቀን 2011ዓ.ም)

በማለት ባለሙያዎቹ እና ተጠቃሚዎች የሚያገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ገልፀዋል፡፡

## 4.1.6.በስፌት ስራ ላይ የባለሙያዎች ፆታዊ ተሳትፎ

የጥናቱ ትኩረት በሆኑት ቀበሌዎች የስፌት ስራ የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የስፌት ስራ በሴቶች የሚከወንበት ምክንያት በተመለከተ ወ/ሮ ተገኘች ተሾመ እንዲህ ይላሉ፡፡

ሴቶች ተጥንት ሲተለቅ ፣ ሲሰራ ፣ ሲሰማራ ወስፌም ለሴት ነው፡፡ ስፌትም በባህላችን መሰረት ለሴት ነው፡፡ እንዝርትም ለሴት ነው፡፡ በዚህም ምህኒያት ሴቶች ተናቶቻችን ይዘነው ዘለቅን፡፡ በዚያ ላይ ለቤት ውስጥ መገልገያችን የሚሆኑትን ስፌቶች የማናውቅ እኛው ሴቶች ነን፡፡ ስፌቱም ቀለል ያለ በመሆኑ ብዙም ጉልበት የማይፈጅ ስለሆነ ሴቶች በቀላሉ እንሰራዋለን፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

በተመሳሳይም ይህን ፆታዊ ተሳትፎ አስመልክቶ መረጃ አቀባዬ ግርማ ብርሃኑ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የስፌት ስራ የሚሰራው በሴቶች ነው፡፡ ይህን ስፌት ወንዶች እንዲሰሩት ባህላቸው አይፈቅድም፡፡ ነገር ግን ወንዶች የስፌት መስሪያ ደንገሉን ከአባይና ጣና በታንኳ በመንዝ ቆርጠው በማምጣት ያግዟቸዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት13 ቀን 2011ዓ.ም)

የስፌት ስራ በሴቶች የሚከወን ተግባር ነው፡፡ በነገዴ ኅብረተሰብ ውስጥ በሴቶችና በወንዶች የሚሰሩ ስራዎች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የስፌት ስራ ላይ ሴቶች ብቻ የሚሳተፉበት ምክኒያት በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ስለሚያያዙ ነው፡፡ የስፌት ቁስ ስራ ሲሰራ ደንገል መቁረጥ ፣ ማድረቅ ፣ መስፋትና ማስዋብ የሚባሉ ሂደቶች አሉ፡፡ በተመሳሳይም ሴቶች በቤት ውስጥ የሚሰሯቸው የተለያዩ ስራዎች ከዚሁ ሂደት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች አብዛኛዎቹ በቤት ውስጥ ለምግብና መጠጥ ማቅረቢያነትና ማስቀመጫነት የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው፡፡ በኅብረተሰቡ ባህል ደግሞ ምግብና

መጠጥ የማዘጋጀትና የማቅረብ ተግባር የሚተገበረው በሴቶች አማካኝነት መሆኑና የቤት ውስጥ ስራዎችን በቅርበት ሁነው እንዲተገብሩ ማስቻላቸው ሌላኛው ተጠቃሽ ምክኒያት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ደንገሉን ከመቁረጥ ተግባር በስተቀር ጉልበት የማይጠይቅና ፀሃይ ሳይመታቸው ስለሚሰሩ እንዲሁም በኅብረተሰቡ ባህል የተነሳ ሴቶች የስፌት ስራን ይሰራሉ፡፡ የስፌት ስራ ከስፌት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእጅ ቅልጥፍና የሚጠይቅና ጌጣጌጥ የሚደረግበት ስራ በመሆኑ ሴቶች ምርጫችን ነው ይላሉ፡፡ በዚህም መነሻ ምክንያት ሴቶች እናታቸው የምትሰራቸውን ቁሶች እየተመለከቱ እንደ እድሜያቸውና ግንዛቤያቸው መጠን ይሰራሉ፡፡ ወንዶች ግን የስፌት አሰራርን እንዲለምዱ የኅብረተሰቡ ባህል አይፈቅድላቸውም፡፡ ይልቁንም አባቶቻቸው የሚሰሩትን ተግባር እንዲለምዱ ይደረጋል፡፡

## 4.2.የድንጋይ ወፍጮ ስራ

የድንጋይ ወፍጮ ስራ ቁሳዊ ባህል ውስጥ ከሚመደበው ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ውስጥ የሚካተት ሀገረሰባዊ ጥበብ ነው፡፡ በዚህ ክፍል የድንጋይ ወፍጮ አሰራር ፣ ሂደትና አገልግሎት ፣ የድንጋይ ወፍጮ መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች ፣ ፆታዊ ተሳትፎ ፣ በቁሶቹና በሰዎች መካከል ያለው ተፈጥሯዊ ግንኙነት እና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ወቅታዊ ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮች እንደሚከተለው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

### 4.2.1.የድንጋይ ወፍጮ መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎች

የድንጋይ ወፍጮ በነገዴ ኅብረተሰብ በወንዶች ከሚሰሩ የእጅ ስራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ጥሬ ቁሶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- **ድንጋይ** ፡- ይህ ለወፍጮ የሚሆን ድንጋይ የሚገኘው የከተማዋ መግቢያ አካባቢ በሚገኘው መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ጀርባ ነው፡፡ ድንጋዩ እጅግ ጠንካራና በቀላሉ የማይሰበር ጥቁር ድንጋይ ነው፡፡ ለድንጋይ ወፍጮ ጥሬ ዕቃ በመሆን ያገለግላል፡፡ ከመሬት ውስጥ ተፈልፍሎ ከወጣ በኋላ ወደ ቀጣዩ ስራ ይገባል፡፡
- **ዶማ** ፡- ከብረት የሚሰራ ለአፈር መቆፈሪያነት የሚያገለግል ሲሆን እረጅም የእንጨት እጀታ ያለው ነው፡፡ ድንጋዩን ከመሬት ውስጥ ፈልፍሎ ለማውጣት ጥቅም ላይ ይውለሳል፡፡

ፎቶ ግራፍ 41 ዶማ



ከማህበራዊ ሚዲያ የተገኘ

- **ማሳ** ፡- ከብረት የሚሰራ ከ4-6 ኪሎ የሚመዝን ትልቅ ብረት ሲሆን እጀታውም እረጅም እንጨት ነው፡፡ አገልግሎቱም ድንጋዩን ከመሬት ፈልፍሎ ለማውጣትና ድንጋዩን ለመጥረብ እንዲሁም ቅርፅ ለማስያዝ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 42 ማሳ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

- **መጠብጠቢያ** ፡- ከማሳ ያነሰ ከብረት የተሰራ መምቻ ሲሆን በእንጨት የተሰራ አጭር እጀታ ያለው መሆኑ ከማሳ ይለየዋል፡፡ የመጠብጠቢያ ጥቅም የተጠረበውን ድንጋይ ለመጠብጠብና ለመውቀር እንዲሁም ለማለስለስ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 43 መጠብጠቢያ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

- **ከረጢት እና ገመድ ፡-** እነዚህ ቁሶች ግልጋሎታቸው ከመሬት ተፈልፍሎና ተጠርቦ የወጣው ድንጋይ አህያው ላይ በሚጫንበት ጊዜ ከረጢቱን አህያው ጀርባ ላይ በማንጠፍ ድንጋዩን ከጫኑበት በኋላ በገመዱ ደግሞ ድንጋዩ ከአህያው ላይ ተንሸራቶ እንዳይወድቅ ለማሰሪያነት ያገለግላል።

## 4.2.2.የድንጋይ ወፍጮ አሰራርና ደረጃዎች

### የመፈልፈል ተግባር

በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከቁስነት ደረጃ የሚደርሱት ብዙ ሂደቶችን በማለፍ ነው። ከነዚህ ሂደቶች ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው ድንጋዩን ቆፍሮ የማውጣት ተግባር ነው። በመስክ ምልከታዬ ወቅት ለወፍጮ የሚሆነውን ድንጋይ ቆፍረው ሲያወጡ ለመመልከት ችያለሁ።

የወፍጮ ባለሙያዎቹ ቁሶችን ለመስራት ሲያቅዱ ተቀዳሚው ተግባር ድንጋዩን ቆፍሮ የማውጣት ተግባር መከወን ነው። በዚህ ወቅት ለመቆፈሪያነት እና ለመጥረቢያነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ዶማና ማሳ (መዶሻ) ያዘጋጃሉ። በመቀጠል ድንጋዩን ለማውጣት እና ለመያዝ የሚያገለግሉ ቁሶችን በመያዝ ወደ ቦታው ያመራሉ።

ፎቶ ግራፍ 44 ድንጋይ የመፈልፈል ተግባር



መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ጀርባ በአጥኚው የተነሳ

ቦታው ጋር ከደረሱ በኋላ ባለሙያዎቹ ጎረቤታሞች ከሆኑ ፣ እርስ በርሳቸው የሚግባቡ በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ የሚተጋገዙ ከሆነ በመረዳዳት በህብረት ድንጋዩን ቆፍረው ያወጣሉ። ነገር ግን በግላቸውም የሚቆፍሩ በርካታ ናቸው። ድንጋዩን ቆፍሮ የማውጣት ተግባር የሚያከናውኑት እራሳቸው ባለሙያዎቹ ወንዶች ናቸው።

## የመጥረብ ተግባር

የወፍጮ ባለሙያዎቹ ለቁሶች መስሪያ የሚያገለግለውን ድንጋይ ቆፍረው ፍልፈለው ካመጡ በኋላ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ከመድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ተቆፍሮ የሚመጣውን ድንጋይ በማሳ በመጥረብ ለማለስለስ እና ለመውቀር እንዲመች ያደርጉታል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉበት ምክኒያት ድንጋዩ ሲጠረብ ወፍጮው ሲሰራ ስራው እንዳያስቸግር ለማለስለስና ለመውቀር ስለሚያመች እንዲሁም ቁሱ በቀላሉ እንዲሰራ ስለሚያደርግ ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 45 ድንጋይ የመጥረብ ተግባር



16 ቀበሌ በአጥኘው የተነሳ

## የመውቀር ተግባር

ድንጋዩ ቁሶቹን ለመስራት አመቺነት ባለው መልኩ ከተዘጋጀ በኃላ ቀጣዩ ተግባር የተጠረበውን ድንጋይ ወደ መኖሪያ ቦታ በአህያ ይዞ መሄድ ነው፡፡ በማስከተልም ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ የመስራት ተግባር ይጀመራል፡፡ ቁሶቹ በሚሰሩበት ጊዜ የተጠረበውን ድንጋይ እንደሚወቅሩ በመስክ ምልከታዬ አረጋግጫለሁ፡፡

ፎቶ ግራፍ 46 የመውቀር ተግባር



16 ቀበሌ በአጥኘው የተነሳ

### የማለስለስ ተግባር

ባለሙያዎቹ ቁሶቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ ከወቀሩ በኋላ ያለውን ሂደት የሚያሳይ ነው፡፡ የድንጋይ ወፍጮው በትንሽ መዶሻ አማካኝነት ለተጠቃሚ እይታ አስደሳች እና አመቺ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ወፍጮውን የሚያለሰልሱት እህል በሚከካበት ወይም በሚፈጭበት ጊዜ በአግባቡ የተፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጥ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለወፍጮ ስራ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ሙሉ በሙሉ በማካተት የድንጋይ ወፍጮ ስራ ሂደቱ ተወጥኖ እንደሚጀመር በመስክ ቆይታዬ መመልከት ችያለሁ፡፡ በመቀጠል የድንጋይ ወፍጮ ስራ ውጤቶችን አሰራርና አገልግሎት በዝርዝር እንመልከት፡፡

## 4.2.3.የድንጋይ ወፍጮ የአሰራር ሂደትና አገልግሎት

የድንጋይ ወፍጮ አሰራር በቅድሚያ ለወፍጮ የሚሆነውን ድንጋይ የሚያገኙበት መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ጀርባ አህያና ከረጢት ፣ ዶማ እንዲሁም የድንጋይ መጥረቢያ ማሳ ይዘው በመሄድ ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡ በመቀጠል ጥሩ ነው ተብሎ የሚታሰበውን ማለትም ዓይናማና ጥቃቅን ዓይኖች ያለውን ድንጋይ በመምረጥ ድንጋዩን ከመሬት ውስጥ ይፈለፍላሉ፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ የ16 ቀበሌ ነዋሪና የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያ የሆኑት አቶ መሐመድ ሁሴን " ዓይናማው ድንጋይ ለጥራጥሬ የሚሆን ሲሆን አይኑ ድቅቅ ያለው ድንጋይ ደግሞ ለጤፍ የሚሆን ነው፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) በማለት ገልፀውልኛል፡፡

ድንጋዩ ተፈልፍሎ ከወጣ በኋላ በትልቁ ማሳ (መዶሻ) ይጠረባል፡፡ የተጠረበውም ድንጋይ በድጋሚ የተሻለ ቅርፅ እንዲኖረው በደንብ ይጠበጠባል፡፡

ከዚህም በማስከተል በተለምዶ ይበቃዋል ተብሎ ሲታሰብ በአህያ ወደመኖሪያ ስፍራቸው ወስደው በትንሹ መጠብጠቢያ ይወቅሩታል፡፡ የተወቀረውንም ድንጋይ በማለስለስ ድንጋዩ ለወፍጮ መሳሪያነት እንዲበቃ ያደርጉታል፡፡

ፎቶ ግራፍ 47 የድንጋይ ወፍጮ ክምር



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

የድንጋይ ወፍጮ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛው ትልቁ መሬት ላይ የሚቀመጠው ወፍጮ የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ከወፍጮው ላይ የሚቀመጠው ትንሹ መደቆሻ በመባል ይጠራል፡፡ ትንሹን መደቆሻ የሚሰራው መጠኑ ይነስ እንጂ ልክ አንደ ትልቁ ወፍጮ ድንጋይ ከመሬት ተፈልፍሎ ይወጣና ይጠረባል፡፡ በማስከተል ይጠበጠብ ፣ ይለሰልስና በደንብ ተወቅሮ ለግልጋሎት ዝግጁ ይሆናል ሲሉ መረጃ አቀባዩ የሆኑት አቶ የሺዋስ ብርሃኑ (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

የድንጋይ ወፍጮ አስራርን አስመልክቶ የ16 ቀበሌ ነዋሪና የድንጋይ ወፍጮ ሙያተኛ የሆነው የሺዋስ ብርሃኑ እንደሚከተለው ይገልፃል፡-

> የድንጋይ ወፍጮ የሚሰራው ተፈልፍሎ ከመድሐኒዓለም ቤተስኪያን ጀርባ በሚመጣ ድንጋይ ነው፡፡ ተዛ ይቀደድና ቅርፅ ከያዘ በኋላ እንደገና ደግሞ ይጠበጠባል፡፡ ተሂያ በኋላ ድብን ተደርጎ ይወቀርና በማለስለሻ ይለሰልሳል፡፡ ይህን ለመስራት አስከ ሁለት ሰዓት ይፈጅብናል፡፡ ቢሆንም ግን ድንጋዩን ፈልፍሎ ለማውጣት አንድ ቀን ይፈጃል፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም)

ሲል የድንጋይ ወፍጮን አሰራርን ይገልፃል፡፡ በተመሳሳይም መረጃ አቀባዩ የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያ አቶ መሐመድ ሁሴን " ለባለጋሬዎች ከፍለን ወዲያ መደኒያለም ሄደን ድንጋዩን እናመጣለን፡፡ ተዚህ ታመጣን በኋላ ድንጋዩን በማሳ ጠርበን በመጠብጠቢያ ጠብጥበን ወቅረን አለስልሰን ለገበያ እናውላለን " ሲሉ (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) የድንጋይ ወፍጮን አሰራር ገልፀውልኛል፡፡

የአንዱ የድንጋይ ወፍጮ ዋጋ 200 ብር ሲሆን ብዙውን ጊዜ የቁሱ ተጠቃሚዎች ዘመናዊ ወፍጮ በመስፋፋቱ እየቀነሱ በመምጣታቸው ምክንያት በተገኘው ዋጋ እንደሚሸጡ መረጃ አቀባዮቹ አቶ የሺዋስ ብርሃኑና መሐመድ ሁሴን (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) ነግረውኛል፡፡

የድንጋይ ወፍጮ መጠኑ እንደ መረጃ ሰጪዎች ግምታዊ ሃሳብ የጥራጥሬውም ሆነ የጤፉ ክብደት እና መጠን እኩል ነው፡፡ እናትየው ቁመቱ 60 ሳ.ሜ ፣ የጎን ስፋቱ 40 ሳ.ሜ ፣ ክብደቱ 12 ኪ.ግ ሲሆን መጁ (መደቆሻው) ደግሞ ቁመቱ 40 ሳ.ሜ ፣ የጎን ስፋቱ 20 ሳ.ሜ ፣ ክብደቱ 4 ኪ.ግ ነው፡፡

የድንጋይ ወፍጮ የተለያዩ አገልግሎቶች ያሉት ሲሆን ዘመናዊ ወፍጮ ልክ እንደ አሁኑ ጊዜ ባልተስፋፋበት ወቅት አብዛኛው የማህበረሰባችን ሴቶች የድንጋይ ወፍጮን በቤት ውስጥ የተለያዩ የእህል ዘሮችን ይከኩበት ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅትም በገጠሩ አካባቢ ሴቶች መሰል አገልግሎቶችን እንደሚጠቀሙበት መረጃ አቀባዩ ወ/ሮ እማ ዘመድ (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀውልኛል ፡፡

ከቤት ውስጥ በተጨማሪ የተለያዩ ገዳማት ውስጥ ለክክ መከኪያነት እና ለስንዴ መፍጫነት ይጠቀሙበታል፡፡ በአንዳንድ ትልልቅ የባህል ምግብ አዳራሾች ውስጥ ለእይታ በሚመች ቦታ በማስቀመጥ የሰዎችን ቀልብ ለመሳብ እና የቤቱን ውበት ይበልጥ ለማጎነፀፍ እንደሚጠቀሙበት ባደረኩት ቅኝት ለመመልከት ችያለሁ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጥቅሞች በተጨማሪም የድንጋይ ወፍጮ ለሸክላ ስራ የሚሆኑ አፈሮችን ለመፍጨት የሚያገለግል ቁስ ነው፡፡ ይህም ማለት ለሌላኛው የቁሳዊ ባህል የሸክላ ስራ እንደ መሳሪያነት ያገለግላል ማለት ነው፡፡

ፎቶ ግራፍ 48 በድጋይ ወፍጮ እህል ሲከካ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

### 4.2.4.የድንጋይ ወፍጮ ቁስ ጠቀሜታ

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ የድንጋይ ወፍጮዎች የሚሰጡትን ጠቀሜታ እንመለከታለን፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ቁሶች የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህም መካከል ማህበራዊ ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ እነዚህን ጠቀሜታዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው እንመልከት፡-

- **ማህበራዊ ጠቀሜታ** ፡- የድንጋይ ወፍጮ በቤት ውስጥ እና በገዳማት ለእህል መከኪያነት ፣ መፍጫነት ፣ ለቤት ማስጌጫነት እንዲሁም ለሽክላ ስራ የሚሆኑ አፈሮችን ለመፍጨት የድንጋይ ወፍጮዎች ማህበራዊ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወፍጮ ባለሙያዎቹ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር እንደጠቀማቸው በመስክ ቆይታዬ ለመመልከት ችያለሁ፡፡
- **ባህላዊ ጠቀሜታ** ፡- የድንጋይ ወፍጮ ቁሶች ካላቸው ጠቀሜታ መካከል አንዱ የሆነው ባህላዊ ጠቀሜታ ነው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ የእለት ተእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የኅብረተሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ ፍልስፍና ፣ ማንነት ፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማስተዋወቅ በኩል አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ሙያውን ለተተኪው ትውልድ በማስተማር እንዲሁም ቁሶቹን ሰርቶ ባህልን ለማስተዋወቅ በሚደረግ ጥረት ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ የሺህ ዋስ ብርሃኑ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ " እኛ የድንጋይ ወፍጮ የምንሰራው ማህበረሰቡ የሚታወቅበት ባህል እንዳይጠፋ በማለት እንጂ ይህ ነው የሚባል ጥቅም አግኝተንበት አይደለም፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት18 ቀን 2011ዓ.ም)
- **ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ** ፡- የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው የኅብረተሰብ ክፍል ያቀርባሉ፡፡ ቁሶችን ለሚያበጇቸው ባለሙያዎች እንዲሁም ለተጠቃሚው የኅብረተሰብ ክፍል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ባለሙያዎቹ የሰሩትን ቁሶች በመሸጥ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመምራት የሚያግዝ ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ቁሶቹን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስመልከት አቶ መሐመድ አሊ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ " ከተማው ላይ ተጠቃሚ የለንም፡፡ ምክኒያቱም ዘመናዊ ወፍጮ በመስፋፋቱ ነው፡፡ የገጠር ነጋዴዎች እየመጡ

አንድ አስር ሃይ የሚሆን ወፍጮ ይወስዱልናል፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) በማለት ባለሙያዎቹ እና ተጠቃሚዎች የሚያገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ የድንጋይ ወፍጮ ተጠቃሚዎች በገጠሩ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡

## 4.2.5.የድንጋይ ወፍጮ ቁስ ወቅታዊ ሁኔታ

የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሶችን በተለያየ መልክ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቁሶቹ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ፍላጎት ሲያሽቆለቁል የቁሶቹ የመሰራት ዕድል እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ የቁሶቹን ወቅታዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ድሮ የሚሰሩና በአሁኑ ወቅት የመሰራት መጠናቸው የቀነሱ ቁሶች በሚል እንደሚከተለው እንዳስሳለን፡፡

የድንጋይ ወፍጮ በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ ወፍጮ ቤቶች እየተስፋፉ በመምጣታቸው የመሰራት መጠኑ እየቀነሰ ነው፡፡ ይህ አስመልክቶ የድንጋይ ወፍጮ ሙያተኛ የሆኑት አቶ የሺህ ዋስ ብርሃኑ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡ " በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚጠቀመው በኢሃኛው በዘመናዊው ነው፡፡ በተወሰነ መልኩ ገጠሩ አካባቢ ያሉ ሰዎች ብቻ ናቸው የሚፈልጉት፡፡ በዚህም የተነሳ በኛ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅህኖ አሳድሮብናል፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 49 ዘመናዊ ወፍጮ



16 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

ከዚህም በተጨማሪ የድንጋይ ወፍጮ ግልጋሎት ላይ ለማዋል ከፍተኛ ጉልበትና ጊዜን የሚፈጅ መሆኑ እና ተጠቃሚዎቹን ለወገብ እና ለእጅ በሽታ እየዳረጋቸው መሆኑ ሌላው የድንጋይ ወፍጮ የመሰራት መጠንን የቀነሱት ጉዳዮች ናቸው፡፡ በጥቅሉ የድንጋይ ወፍጮ በአሁኑ ወቅት በዘመናዊው ወፍጮ እየተተካ ስለሆነ በብዛት በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የመሰራት መጠኑ እየተመናመነ ነው፡፡

በአጠቃላይ የስፌትና ድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መንገድ ቅርፅ ሲሰሩ ኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ድንበር ተሻጋሪ ዘመንኛ ቁሶች በመኖራቸውና ድሮ ይሰጡት የነበረው አገልግሎት በመቀነሱ ምክንያት መጠናቸው የቀነሰ ቢሆንም አሁንም በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ባለሙያዎቹ የሚሰሯቸው ቁሶች ለኅብረተሰቡ የእለት ተእለት ተግባራት ለመከወኛነት ከማገልገላቸውም ባሻገር የኅብረተሰቡን ሰርካዊ ህይወት በማመላከት በኩል አበርክቶ አላቸው፡፡

## 4.2.6.በድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ የባለሙያዎች ፆታዊ ተሳትፎ

በተጠኚው ኅብረተሰብ በድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ የሚሰማሩት ወንዶች ናቸው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ስራ በወንዶች የሚከወንበት ምክንያት በተመለከተ አቶ የሺህ ዋስ ብርሃኑ እንዲህ ገልፀውታል፡፡

> የድንጋይ ወፍጮ የሚሰራው በወንዶች ነው፡፡ ምህኒያቱም ይህ የድሮ ባህላችን ነው፡፡ እናቶቻችን የስፌት ስራና የቤትስራን ሲሰሩ አባቶቻችን ደግሞ የድንጋይ ወፍጮና ታንኳ ይሰሩ ነበር፡፡ እኛም ከጥንት ጀምሮ ተአባቶቻችን ይህንን የድንጋይ ወፍጮ አሰራር ለመድን፡፡ በዛላይ ድንጋዩን ቆፍሮ ለማውጣትና ለመስራት ሴቶች አቅማቸው አይፈቅድም፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት17 ቀን 2011ዓ.ም)

ከዚህም በተጨማሪም ጣና ዳር ላይ በደንገል ታንኳ በመስራት ዓሳ በማጥመድ ፣ የእህል ወፍጮ ድንጋይ በማምጣት የማስቶሪ (የድንጋይ ካብ) እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በግምበኝነትና በአናጢነት በመሰማራት የሚሰሩት ወንዶች ናቸው፡፡

የድንጋይ ስራ በወንዶች የሚከወን ተግባር ነው፡፡ በነገዴ ኅብረተሰብ ውስጥ ሴቶችና ወንዶች የሚሰሩ ስራዎች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ ወንዶች ብቻ የሚሳተፉበት ምክኒያት በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ከቤት ውጪ ስለሚሰሩና ከፍተኛ ጉልበት ስለሚፈልጉ ነው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ሲሰራ ድንጋይ ቆፍሮ ማውጣት ፣ መጥረብ ፣ መውቀር ማለስለስ

የሚባሉ ሂደቶች አሉ፡፡ በተመሳሳይም ወንዶች የሚሰሯቸው የተለያዩ ስራዎች ከዚሁ ሂደት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በርግጥ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ የድንጋይ ወፍጮ ቁሶች ተሰርተው ከተጠናቀቁ በኋላ አብዛኛዎቹ በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ሴቶች ሲሆኑ የተለያዩ ጥራጥሬዎችን ይከኩበታል ፣ ይፈጩበታል፡፡ በዚህም የተነሳ ወፍጮውን ወንዶች ቢያበጁትም የሚገለገሉበት ግን ሴቶች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ድንጋዩን ቆፍሮ ከማውጣት ተግባር ጀምሮ ብዙ ጉልበት የሚጠይቅና ፀሃይን መቋቋም የሚያስፈልግ በመሆኑ ሴቶች ስለማይችሉት እንዲሁም በኅብረተሰቡ ባህል መሰረት ወንዶች ብቻ ይሰሩታል፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ስራ ከመፍለጥ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእጅ ጉልበት እና ሃይል የሚጠይቅ ስራ በመሆኑ ወንዶች ብቻ ይሰሩታል፡፡ በዚህም መነሻ ምክኒያት ወንዶች አባቶቻቸው የሚሰሩትን ቁሶች እየተመለከቱ እንደ እድሜያቸውና ግንዛቤያቸው መጠን ይሰራሉ፡፡ ሴቶች ግን የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን እንዲለምዱ በኅብረተሰቡ አይደረግም ይልቁንም እናቶቻቸው የሚሰሩትን ተግባር እንዲለምዱ ይደረጋል፡፡

## 4.3.ባህላዊ የስፌት እና የድንጋይ ወፍጮ ስራ ሙያ ለመዳ

የነገዴ ኅብረተሰብ የራሳቸው የሆነ የተለያየ የሙያ ክህሎት ያላቸው ሲሆን ክህሎቶቻቸው በፆታና በዕድሜ የተከፈሉ ናቸው፡፡ በባህር ዳር ከተማ በ03 ቀበሌና 16 ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የሙያ ለመዳ ተመሳሳይ ነው፡፡ በመረጃ አቀባይነት የተመረጡት በስፌት ስድስት በድንጋይ ወፍጮ አራት በአጠቃላይ አስር ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱት ከቤተሰቦቻቸው ስር በመሆን ነው፡፡ ቤተሰቦቻቸው ሲሰሩ ደጋግመው በመመልከት እና የስፌትና የድንጋይ ወፍጮ መሳሪያዎችን በማቀበል ቀስ በቀስ ወደ ሙያው ገብተው እንደቀሩ ይገልፃሉ፡፡

የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያ የሆነው የሺህ ዋስ ብርሃኑ ሙያውን የለመደበትን ሁኔታ ሲገልፅ " ልጅ (ኩታራ) እያለን አባቶቻችን ብዙውን ጊዜ ወፍጮ በሚሰሩበት ሰዓት አብረናቸው ቦታው ድረስ በመሄድ እንዴት እንደሚሰሩ እያየን ለመድን፡፡ ዘመናዊ ተማሪ ቤት ከማስገባት ይልቅ ሙያቸውን ነበር የሚያስለምዱን፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) ይላል፡፡ ሌላኛው የድንጋይ ወፍጮ ሙያተኛ የሆኑት አቶ መሐመድ አሊ ደግሞ " አባቶቻችን ሙያው እንዳይጠፋ ሲሉ ለኛ አስተምረውናል፡፡ እኔም ልጆቼን በትርፍ ጊዜያቸው ባህሉ ጨርሶ

እንዳይጠፋ በማየት እና ዕቃዎችን በማቀበል እንዲለምዱ እያደረኩ ነው፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት19 ቀን 2011ዓ.ም) በማለት ስለሙያ ለመዳ ገልፀዋል፡፡

የስፌት ስራ ውጤቶች ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ስመኝ መርሻ የሙያ ለመዳውን አስመልክቶ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> ይህን ሙያ የምትለምደው ሴት ልጅ ስትሆን የሰባት ዓመት ዕድሜ (ኩታራ ልጅ) ላይ ሳለች ከእናቷ አጠገብ በመሆን የሚሰራውን ስፌት በማየት ትከተላለች በመቀጠል እናትየው ወጥና (ጀምራ) የሰጠቻትን ዙር እያዞረች ግድግዳ በመስራት ለእናቷ መልሳ ትሰጣለች፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ልጅቷ ሙሉ ስራውን መስራት ትጀምራለች፡፡ (ቃለመጠይቅ መጋቢት14 ቀን 2011ዓ.ም)

ፎቶ ግራፍ 50 የተገኘች ተሾመ ሴት ልጅ መሪማ ሁሴን የስፌት ስራ ሙያ ስትለምድ



03 ቀበሌ በአጥኚው የተነሳ

በመሆኑም በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የስራ ክፍፍል ያለ ሲሆን ይህም ዕድሜና ፆታን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የስፌት ስራ ውጤቶችን ሴቶች ብቻ ሲሆኑ ወንዶቹ ደግሞ የእህል ወፍጮ ይሰራሉ፡፡ ሙያውንም እናትና አባቶቻቸው በማለማመድ እና በማሳየት ሙያው ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ የግላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ ሙያተኞቹም እንዚህን የእጅ ስራዎች ለመስራት ጥሩ ሙያዊ እውቀትና ልምድ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

## 4.4.በቁሶቹና በሰው ልጅ መካከል ያለ ቁርኝነት

የነገዴ ኅብረተሰብ የስፌት ቁሶች ከመጡበት አመጣጥ እና ከአኗኗር ዘይቤያቸው ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ነገዴዎች ባህር ለባህር ተጉዘው ውሃ ዳርቻ ያሉ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን እንዲሁም እንስሳትን እያደኑ የሚኖሩ ማህበረሰቦች መሆናቸው

በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ውሃ ዳር የሚገኘውን ደንገል ቆርጠው የስፌት ስራ እና ታንኳ የሚሰሩ መሆኑ በሰው ልጅ እና በቁሶቹ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳይ ነው፡፡

የሰው ልጅ ከአራቱ የስጋ ባህሪያት የተፈጠረ ነው፡፡ አራቱ የስጋ ባህሪያትም ንፋስ፣ እሳት፣ መሬትና ውሃ ናቸው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣አባ አረጋዊ፣መጋቢት 18 ቀን 2019.ም) የስፌት ቁስም ሲሰራ ልክ የሰው ልጅ እንደተፈጠረበት ስጋዊ ባህሪያት ውሃ ፣ ነፋስ ፣ ፀሐይ እና የደንገል ተክል እንዲሁም ቁሱ ውበት እንዲኖረው ለማስቻል ደግሞ አለላ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚያሳየው በሰው ልጅና በቁሶቹ መካከል ያለውን ተፈጥሯዊ ተዛምዶ ነው፡፡

የሰው ልጅ እናት እና ልጅ የሚባሉ የቤተሰብ ክፍሎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ በተመሳሳይ የስፌት ቁሶችም እነ መሶብ ፣ አገልግል ፣ ሙዳይ እና ሌማት በዚህ ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የድንጋይ ወፍጮም በተመሳሳይ እናትና ልጅ በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው በቁሶችና በሰዎች መካከል ቁርኝት መኖሩን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሰው ልጅ አፍ ፣ አንገት ፣ ሆድ እና እግር የሚባሉ የሰውነት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በተመሳሳይም የስፌት ውጤቶች በዚህ ስያሜ ይጠራሉ፡፡ ይህም የስፌት ባለሙያዎቹ የቁሶቹን ቅርፅ ከሰው ልጅ አካል ጋር በማመሳሰል እንደሚሰይማቸው ይጠቁመናል ማለት ነው፡፡

ሌላው በድንጋይ ወፍጮ እህል በሚፈጭበት ወይም በሚከካበት ጊዜ ጥሬውም ሆነ ዱቄቱ መሬት ላይ እንዳይፈስ ከወፍጮው ፊት ለፊት ሰፌድ በማስቀመጥ ጥራጥሬው እና ዱቄቱ ለማጠራቀም ያገለግላል፡፡ ይህም የሚያሳየው በድንጋይ ወፍጮና በስፌት ውጤቶች መካከል ያለውን ቁርኝት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በድንጋይ ወፍጮ የተፈጨው እህል ተጋግሮና ተዘጋጅቶ ለሰዎች የሚቀርበው በስፌት ውጤቶች መሆኑ ሌላው በቁሶቹ መካከል ያለ ተጠቃሽ ቁርኝነት ነው፡፡

## 4.5.የባለሙያዎቹ የዕርስ በዕርስ ግንኙነት

በባህር ዳር ከተማ በ03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ የሚገኙ የነገዴ ኅብረተሰብ አባላት የስፌት እና የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የዕርስ በዕርስ ግንኙነት በጣም ጠንካራ ነው፡፡ ከእርስ በእርስ ግንኙነታቸው መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ነገዴዎች በስፋት ከሚታወቁባቸው መገለጫዎች መካከል በአንድ አካባቢ ሰፍረው በቡድን መገኘታቸው መሆኑን በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል፡፡ የኅብረተሰቡ አባላት ወገንተኛና መጠቃትን የማይወዱ ከመሆናቸው በተጨማሪ በተለያዩ የሙያ ክህሎቶች ያገኙትን ጥሪት በጋራ ተከፋፍለው የሚበሉና ለእጅ ስራ የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በመዋዋስና በሃዘን በደስታ ጊዜ ከያሉበት በመሰብሰብ ያላቸውን በህብረት ይከፋፈላሉ፡፡ በገንዘብም ሆነ በጉልበት እንደ አቅማቸው ይረዳዳሉ፡፡ በመካከላቸው የተጋጩ ሰዎችን በራሳቸው የግጭት አፈታት መንገድ ለማስማማት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ነገዴዎች መልካም የሆነ የዕርስ በዕረስ ግንኙነት ቢኖራቸውም የስፌት ውጤቶችን እና የድንጋይ ወፍጮዎችን በሚሸጡበት ጊዜ አንዱ የአንዱን እጅ ስራ የማጣጣል ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ ያላቸውን መልካም ገፅታ ሊያበላሽ የሚችል ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ እኔም በመስክ ምከታዬ ገበያው ቦታ ድረስ በመገኘት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

## 4.6.ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሙያው ባለቤቶች ያላቸው አመለካከት

ሀገራችን ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ባለቤት ከሆኑት በርካታ የዓለማችን ሀገራት መካከል የጥበብና የእውቀት መፍለቂያ እንደነበረች የታሪክ ድርሳናት እና ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለዘመናት የእጅ ስራ ባለሙያዎች የጥበብ ስራዎች እየሰሩ ኖረዋል፡፡ ባለሙያዎቹም በራሳቸው ፈጥረው ሙያቸውን አዳብረው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡

ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ማንም ሳያስተምራቸው የራሳቸው የሆኑ በርካታ የእጅ ስራዎች እንደነበሯቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የስፌት ስራ ጥበብ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ታድያ ከጥንት ጀምሮ ሲሰሩ የነበሩ የእጅ ስራዎች ፣ ጥበቦች ብሎም ፍልስፍናዎች ለምን የቴክኖሎጂ ማማ ላይ አላደረሱንም? ጥንት የነበሩ ጥበቦች ለምንድን ነው ያልቀጠሉት? በፊት ይሰሩበት በነበረበት ደረጃ አሁን የማይሰሩት ለምንድን ነው? ድሮ የነበሩ የስፌት ጥበቦች በአሁኖቹ ላይ ለምንድን ነው ያልታዩት? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ባህሎችን መዝግቦ በሚገባው መንገድ ለሌላው ትውልድ የማስተላለፍ ስራ ክፍተት መኖሩ እና ለባለሙያዎቹ የሚሰጥ አሉታዊ አመለካከቶች ናቸው፡፡

በባህር ዳር ከተማ 03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ የሚገኙ የነገዴ ኅብረተሰብ አባላት ከተለያዩ ልማዶቻቸው ጋር በተያያዘ መልኩ ከሙያው ውጪ ያሉ አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለሙያተኞቹ የሚሰነዝሩትን አወንታዊና አሉታዊ አመለካከቶች ያሉ ሲሆን እነዚህንም ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

## 4.6.1.አወንታዊ አመለካከት

የነገዴ ኅብረተሰብ አባላት ከጥንት ጀምሮ ውሃ በሚገኝባቸው የተለያዩ ቦታዎች ሰፍረው የሚገኙና የተለያዩ የሙያ ክህሎቶቻቸውን በመጠቀም የተለያዩ መገልገያ ቁሶችን ጥበባዊ በሆነ መንገድ በመስራት ለኅብረተሰቡ መገልገያነት በማሟላታቸው እና ለስራ ያላቸው ክብር ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደመልካም ጎን ይገልፃሉ፡፡

## 4.6.2.አሉታዊ አመለካከት

የእጅ ስራ ባለሙያዎች  ለብዙ ዘመናት ኅብረተሰቡን ሲያገለግሉ የሙያቸውን አድናቆት ፣ የላባቸውን ዋጋ ሳያገኙና ሳይከበሩ እስካሁን ድረስ ኖረዋል፡፡ ለእጅ ስራ ባለሙያዎች ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አሉታዊ የሆኑ አመለካከቶችም አሏቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ነገዴዎች በሌላው ኅብረተሰብ የማይፈቀዱ ነገሮችን በመብላታቸው እንዲሁም ለዕለታዊ ኑሮ ብቻ የሚያስቡና ጊዜያዊ ነገሮች ብቻ የሚያስደስታቸው ከመሆኑም በላይ ደንገል ከቆረጡ በኃላ ባህሩ ዳርቻ ላይ ስለሚተኙ ጠረናቸው ሰው ስለማያስቀርብ ሌላው ኅብረተሰብ ለባለሙያዎቹ ያለው አመለካከት ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሙያተኞቹ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ ሲሆን ነገዴዎች የዕለት ተዕለት ኑሯቸው የተመሰረተው በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ስለሆነና በአመጋገብ ፣ በአለባበስ እና በእምነት ደረጃ የራሳቸውን ስርዓት የሚከተሉ ስለሆኑ ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለነገዴዎች ያላቸው አመለካከት አነስተኛ መሆኑን መረጃ አቀባዬ አቶ ግርማ ብርሃኑ (ቃለመጠይቅ መጋቢት15 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለነገዴዎች የሚወሩ የተሳሳቱ ወሬዎችን በመስማት እና ስለኅብረተሰቡ ምንም ዓይነት ዕውቀት ሳይኖራቸው እንዲሁ ያላቸው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ የሚሆንበት ጊዜም እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህም የተነሳ ከሙያው ውጪ ያሉ ኅብረተሰቦች ለቁሶቹ የሚሰጡትን ክብር ለባለሙያዎቹ መስጠትን አይፈልጉም፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ባለሙያዎችን ወደኋላ አስቀርቷል፡፡

ኅብረተሰቡ በራሱ አለም ፈጥሮ ለባለሙያዎቹ የሰጣቸው ስያሜ ከምንም ቁብ ሳይቆጥሩ ስራቸውን እንዲሰሩ ያደረጋቸው ነገር ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ለስራው ያላቸው ፍቅር ፣ ዘመናዊ ትምህርት ያለመማራቸው እና ባህሉ እንዳይጠፋ ካላቸው ፍላጎት መሆኑን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.7.በእጅ ስራዎቹና በባለሙያዎቹ ላይ የሚታዩ ችግሮች

ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ በመነሳት ከላይ ከተጠቀሰው አሉታዊ አመለካከት ባሻገር በአሁኑ ወቅት በባለሙያዎች እና በእጅ ስራዎቹ ላይ የሚታዩ የተለያዩ ተግዳሮቶችን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### 4.7.1.የመስሪያ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ

በአሁኑ ወቅት ጣና ሃይቅ በተለያዩ ባለሃብቶች በመከበቡ ምክንያት ለስፌት ስራ የሚሆነውን ደንገል ለማግኘት አዳጋች እየሆነ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጣና ሃይቅ እና የዓባይ ወንዝ ተረፈ ምርት እየቀነሰ መሄዱ ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በስፌት ውጤቶቹና በባለሙያዎቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት እያደረሰ ነው፡፡

መንግስት ዘመን አመጣሹን አረም " እምቦጭ " ሊቆጣጠር የሚችለው የደንገል ተክል መሆኑን በጥናት በማረጋገጡ ምክንያት ደንገል እንዳይቆርጡ እንዲሁም ድንጋይ ቆፍረው እንዳያወጡ ይህን በሚያደርጉት ላይ የእስርና የገንዘብ ቅጣት የሚጥልባቸው በመሆኑ በምሽት ተደብቀው መቁረጥን ልማዳቸው አድርገውታል፡፡ በዚህም የተነሳ እጅ ስራዎቹን ለመስራት ከፍተኛ የሆነ ችግር እንደተፈጠረባቸው መረጃ አቀባዬ አቶ ግርማ ብርሃኑ (ቃለመጠይቅ መጋቢት16 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡

ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ከጥሬ ዕቃዎች ግብዓት ጋር በተያያዘ እየደረሰ ያለው ተፅህኖ የጥሬ ዕቃዎች መወደድ የጥሬ ቁሶች ጥራት መቀነስ ባለሙያዎች ለመስራት ያላቸውን ተነሳሽነት ቀንሶታል፡፡ ይህም በባለሙያዎች ላይም ሆነ በጥሬ ዕቃዎች ላይ ተፅዕኖ አለው፡፡

## 4.7.2.የባለሙያዎች መቀነስ

በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የእጅ ስራ ባለሙያዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ከቤተሰቦቻቸው የስፌት እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርን እንደሚለምዱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የዚህ ዓይነት ልማድ እየቀነሰ በመምጣቱ ምክኒያት ልጆች ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት እየሄዱ እየተማሩ በመሆኑ የስፌቱም ሆነ የድንጋይ ወፍጮ ስራ ሙያተኞች እየቀነሱ ነው በማለት መረጃ አቀባዩ ፋሲል ሙጬ (ቃለመጠይቅ መጋቢት16 ቀን 2011ዓ.ም) ነግሮኛል፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የባለሙያዎች መቀነስ ዋነኛ ምክኒያት ልጆች ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገብተው በመማራቸው ሙያውን የሚለምዱበት ጊዜ ያለመኖሩና ሙሉ ጊዜያቸውን በትምህርት ማሳለፋቸው ለባለሙያዎች መቀነስ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠር እንደቻለ ነው፡፡

## 4.7.3.የፋብሪካ ምርቶች መስፋፋት

በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች ላይ ተፅዕኖ እየፈጠሩ ካሉ ነገሮች መካከል የፋብሪካ ምርቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከድጋይ ወፍጮ ጋር ሲነፃፀር በስፌት ውጤቶች ላይ ይህ ነው የሚባል ጉዳት የፋብሪካ ምርቶች መስፋፋት አላደረሱም፡፡ ምክንያቱም ከፋብሪካ ምርቶች ይልቅ የስፌት ውጤቶች ውበትና ጥንካሬ ስላላቸው መሆኑን መረጃ አቀባዩ ወ/ሮ እናና ቢያዝን (ቃለመጠይቅ መጋቢት17 ቀን 2011ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡ ነገር ግን የፋብሪካ ምርቶች ዋጋቸው ቅናሽ ከመሆኑም ባሻገር በቀላሉ ንፅህናቸውን ለመጠበቅ ምቹ መሆናቸው የስፌት ውጤቶች ላይ በተወሰነ መልኩ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

በባህር ዳር ከተማ ዘመናዊ ወፍጮ ቤቶች መስፋፋታቸው የድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ ክፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ ቢሆንም ግን በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል ዘመናዊ ወፍጮ ቤቶች ባልተስፋፉባቸው አካባቢዎች ላይ አሁንም ቁሱ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ውጤቶችን ከመጠቀም ይልቅ የፋብሪካ ውጤቶችን መጠቀም በብዛት እየተለመደ በመምጣቱ ባህላዊ በሆኑት ሀገረሰባዊ ቁሶች ላይ ተፅህኖ እየፈጠረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.7.4.የመንግስት ድጋፍ አለመኖር

ለአንድ ኅብረተሰብ መንግስት የሚያደርገው ድጋፍ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ አቶ የሺህ ዋስ ብርሃኑ " መንግስት ለዚህ ምንም አይነት እጋዘ አያደርግልንም፡፡ በሌላው ኅብረተሰብ ዘንድ እንዳንገለል ከማድረጉ ውጪ በሙያችን ላይ ምንም ዓይነት እገዛ አያደርግልንም፡፡ እኛም ባህሉ ከሚጠፋ ብለን ነው የምንሰራው፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት16 ቀን 2011ዓ.ም) በተመሳሳይ የስፌት ስራን በተመለከተ ወ/ሮ አንሻ ቸሩ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ " መንግስት ምንም ዓይነት ድጋፍ አያደርግልንም፡፡ እኛው እራሳችን ለፍተን ጥረን ነው የምንኖር፡፡ " (ቃለመጠይቅ መጋቢት16 ቀን 2011ዓ.ም)

ከዚህ በተጨማሪም መንግስት በአሁኑ ጊዜ ከመኖሪያ አካባቢያቸው በማፈናቀልና በማንሳት ሌላ መኖሪያ ቦታ ላይ በማስፈር ተፅዕኖ እንደፈጠረባቸው ምክንያቱም ደግሞ የድሮ መኖሪያቸውን ለባለሃብቶቸ ወይም ለኢንቨስተሮች በመስጠት ዘመናዊ ፎቆችና ቤቶች እንዲሰሩ በመደረጉ መሆኑን ሌሎች መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡

ሌላው ጉዳይ መንግስት ለኅብረተሰቡ የኑሮ መተዳደሪያ የሆኑትን የመስሪያ ጥሬ ቁሶችን ለስፌት የሚሆን ደንገል እና ለወፍጮ የሚሆን ድንጋይ እንዳይጠቀሙ ማድረጉ ከፍተኛ የሆነ ተፅህኖ አሳድሯል ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የእጅ ስራ ሙያ ዋና የገቢ ምንጭና መተዳደሪያ ሲሆን እነዚህ ባለሙያዎች ሙያዬ ብለው የሚተዳደሩበትና ኑሯቸውም በዚሁ የስራ መስክ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ባለሙያዎች በስራቸው እንዳይቀጥሉና እንዲጠፉ ከፍተኛ አስተዋፅዎ ይኖራቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ

በዚህ ክፍል በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች የተገኙ ፍሬ ሃሳቦች የቀረቡበት ነው፡፡ የጥናቱ ግኝት እና ጥናቱ በተከናወነበት አካባቢ ላይ በቀጣይ ቢሰሩ መልካም ነው ያልኳቸውን የይሁንታ ሃሳቦችም ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### 5.1.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በባህር ዳር ከተማ በ03 ቀበሌ እና 16 ቀበሌ በሚኖሩ የነገዴ ኅብረተሰብ እጅ ስራ ባለሙያዎች አማካኝነት የሚሰሩ ባህላዊ የስፌት ስራ ውጤቶች እና የድንጋይ ወፍጮ አሰራርና አገልግሎት ላይ የተከናወነ ነው፡፡ በመሆኑም የስፌት ውጤቶችን እና የድንጋይ ወፍጮ ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳርያዎች እና ጥሬ ቁሶች ፣ የባለሙያዎች ማንነትና የሙያ ለመዳ ፣ የባለሙያዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት ፣ ከሙያው ውጪ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለሙያው ባለቤቶች ያላቸውን አሉታዊና አዎንታዊ አመለካከት ፣ በስፌት ውጤቶቹና በሙያው ባለቤቶች ዘንድ የሚታዩ ተግዳሮቶች እንዲሁም ያታዊ ተሳትፎ የሚሉትን ርዕሰ ጉዳዮች ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

የስፌት ስራ በአብዛኛው የሚሰራው በሴቶች ሲሆኑ ቁሶቹ በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸውና የአሰራር ሂደታቸውም ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ሴቶችም ሙያውን የሚለምዱት ከእናቶቻቸው እንደሆነና በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ ጥሩ የስፌት ስራ ባለሙያ ለመሆን በሙያው ረዘም ያለ ጊዜ መስራትና ጥሩ ልምድ የሚያስፈልግ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

የስፌት ውጤቶች የተሳካ ሆነው ለአገልግሎት ይበቁ ዘንድ የተለያዩ ለስፌቱ አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ ቁሶችን መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑንና የስፌት ውጤቶቹም ተሰርተው ካለቁ በኋላ የተለያዩ የማስዋቢያ ጌጣጌጦችን ከኅብረተሰቡ ውጪ ያሉ ክፍሎች ጭምር ከገበያ በመግዛት በውጤቶቹ ላይ ጌጦችን በመጨመር እንደሚያስጌጧቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

የስፌት ባለሙያዎች ልምድ እያደገ በሄደ ቁጥርና የተጠቃሚው ኅብረተሰብ ፍላጎት ሲያሻቅብ ቁሶች በተለያየ መልክ እና ጥሬ ቁስ ሊሰሩ እንደሚችሉ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የደንገል ተክል በነገዴ ኅብረተሰብ ልዩ ትርጉም ያለውና ከህይወታቸው ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ ደንገል ውሃማ አካባቢ የሚበቅል በመሆኑ ምክኒያት የኅብረተሰቡን ጥንት አመጣጥ የሚጠቁም እና የኅብረተሰቡ ህይወት በውሃ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የደንገሉ አናት ላይ የሚገኘው ጨፌ ቤት ውስጥ የሚጎዘጎዝ ሲሆን ቀሪው አካሉ ደግሞ ለስፌት ስራና ለታንኳ ስራ አገልግሎት ይውላል፡፡ በዚህም የተነሳ ነገዴዎች ኑሯቸው የተመሰረተው በውሃ ላይ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በነገዴ ኅብረተሰብ ዘንድ የድንጋይ ወፍጮ ስራ የሚተገበረው በወንዶች ነው፡፡ የድንጋይ ወፍጮ ስራ በወንዶች የሚተገበረው ድንጋይ መቀጥቀጡና መጥረቡ ጉልበትን የሚጠይቅ በመሆኑ እና በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ከጥንት ጀምሮ የድንጋይ ወፍጮን ወንዶች ስለሚሰሩ መሆኑን እንዲሁም ሙያውን የሚለምዱት ከአባቶቻቸው እንደሆነ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የኅብረተሰቡ የእጅ ስራ ውጤቶች ተሰርተው ካለቁ በኋላ ማህበረሰቡ እምብዛም እንደማይጠቀምባቸው ይህም ሊሆን የቻለው የባህር ማዶ የፋብሪካ ውጤቶች መበራከታቸው እና ለአጠቃቀም ምቹ በመሆናቸው እንዲሁም ለሙያተኞች ካለው አሉታዊ አመለካከት የተነሳ በመሆኑ ነው፡፡

ሙያተኞቹ የእጅ ስራ ውጤቶችን በሚሰሩበት ወቅት በጋራ በመሆን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ግንኙነታቸውን ከማጠናከር በተጨማሪ ሰዎች ለተለያዩ ድርጊቶች እንደሚጠቀሙባቸው ማወቅ ተችሏል፡፡

## 5.2.የይሁንታ ሃሳቦች

በጥናቱ ከተዳሰሱ ጉዳዮች በመነሳት ቀጥሎ የሚከተሉትን የይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- የነገዴ ኅብረተሰብ የእጅ ስራ ሙያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ሄዷል፡፡ ምክንያቱም የእጅ ሙያ ከወላጆች ወደ ልጆች የመተላለፍ ዕድሉ እየጠበበ ነው፡፡ ዋነኛ የኑሮ መተዳደሪያ የነበረው የማህበረሰቡ የእጅ ስራ ሙያ ልጆች ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመግባታቸው ምክኒያት ቀጣይነቱ አሳሳቢ እየሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የእጅ ሙያው በማህበረሰቡ ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ቅብብሎሹ እንዲቀጥል በመንግስት በኩል የስፌት ባለሙያዎችን በማደራጀትና ስልጠና በመስጠት እንዲሁም ድጋፍ በማድረግ ቢያጠናክራቸው መልካም ነው፡፡
- በአሁኑ ጊዜ በተለይ የስፌት ስራ ለመስራት የሚያስፈልገው የደንገል ተክል መቁረጥ እንዲሁም ለወፍጮ የሚሆን ድንጋይ መቆፈር መንግስት በመከልከሉ ሳቢያ ሙያው አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶች መበራከታቸው ቁሶቹን ለመስራት የሚያስፈልጉ ጥሬ ቁሶችን ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ በመሆኑም መንግስትና የተለያዩ ባለሃብቶች ለእነዚህ የእጅ ስራ ባለሙያዎች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እና ጥሬ ቁሶቹን በተገቢው መንገድ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻል  እና ሌላ አማራጭ የጥሬ ቁስ አቅርቦቶችን ማመቻቸት ቢቻል ሙያው የመጥፋት ዕድሉ ይቀንሳል፡፡
- የእጅ ስራዎቹ በፋብሪካ ምርት ውጤቶች እየተተኩ በመሄዳቸው በሙያተኞች እና በቁሶች ላይ ተፅህኖ አሳድሯል፡፡ ተጠቃሚዎች የእጅ ስራ ውጤቶቹን በመገልገል ባለሙያዎችን ቢያበረታቱና የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በበኩሉ ጥናት በማድረግ እነዚህ ሙያተኞች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ ቢያመቻች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከጥንት ጀምሮ የተሰሩ የእጅ ስራ ውጤቶች ብሎም ፍስፍናዎች ከፍ ያለ ቦታ ላይ ለማድረስ ባህሎችን መዝግቦ በሚገባው መንገድ ለሌላው ትውልድ የማስተላለፍ ስራ ቢሰራ መልካም ነው፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብታሙ እንግዳው፡፡ " በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ በሻሞ ጎድጓዲት ገጠር ቀበሌ በሻሞ መድሃኒያለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና፡፡ " ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2001፡፡

ሐሰን ኡስማን፡፡ " በነገደ ወይጦ ለአዳኝና ለጣውንት የሚገጠሙ ስነቃላዊ ግጥሞች ማህበራዊ ረብነት፡፡ " ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 1981፡፡

ሰለሞን ተሾመ ባዬ፡፡ *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ*፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ አታሚዎች ፣ 2007 ፡፡

አስማማው እሰተዚያ፡፡ " በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ " ፡፡ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2003፡፡

አስቴር ሙሉ፡፡ " ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ፡፡ " ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2000፡፡

አብርሃም ዓለሙ፡፡ " የስነቃል ጥናት በኢትዮጵያ " አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነጽሁፍ ክፍል ፣ 1995፡፡

አየለ ፍቅሬ፡፡ " ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ " ፡፡ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ

ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 1998።

ከሁሉም በላይ። " የነገጼ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት። " ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2004።

ዘመኑ ታደለ። ባህር ዳር አጠቃላይ ምክር ቤት። *ውቢቱ ባህር ዳር* ። ባህር ዳር፣ ባህር ዳር አሳታሚ ድርጅት፣2010።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። *አማርኛ መዝገበ ቃላት*። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፣ 1993።

ያለው እንዳወቀ። *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር* ። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት ፣ 1998።

ደመቀ ከበደ። የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ማስታወቂያና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት። ባህርዳር ንግድ ማተሚያ ቤት ፣ 2003።

ደግሰው ጥላሁን። " ባህላዊ የሽክላና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ። " ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2003።

ገዛኸኝ ጎሹ ገብረስላሴ። " ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ። " ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 2005።

ጥላሁን ዳምጤ። *አማራ ስፖርት* ። የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስፖርት ኮሚሽን መጽሄት፣ የካቲት 2006።

*ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነቃል መምሪያ ፡፡* አዲስ አበባ ፣ ቦሌ አታሚዎች ፣ 1991፡፡

Ames, L.kenneth. " Meaning in Artifacts; Hall furnishing in victorya America. " in Jornal of Interdisiplinary History*;* Vol IX; No, 1, PP, 19-46; 1978.

Deetz , James, In Small Things Forgoten: *The Archeology of Early American Life*. New York: Anchor Books, 1996. ISBN: 0-385-48399-6

Dorson, Richard M. (ED. ) *Foklore and folk life; An Introduction*. Chicago; The University of Chicago Press, 1972.

Finnegan, Ruth. *Oral Traditions and the Verbal Arts*: A Guide to Research Practices.London And New York፡ Rutledge, 1992

Glassie, Henry. " folkloristic study of the American artifact ; Objects and objectives " In Hnad book of American folklore. Richard M dorson (ED).

Jones , owen, Micahel. Putting Foklore to use .USA: The university press of kentuky,1999.

Oring, Elliot. Folk grups and Folklore Geners; An Introduction; Logan, Utah; Utah university Press,1986.

Prown, Jules David. " mind in matter; An Introduction to material culture theory and methods. " On line. Available at; WWW. http:// jstor . Org /about/ terms. Html.1982.

Sims, Martha C. and martine stephens. *Living folklore: An Introduction to the study of people and their traditions*. Logan, Utah: Utah state university press,2005.

Teclehaimanote Gebere Sellasie. " The woyto of lake tana; An Ethino-History. " M.A Thesis,Department of History, Addis abeba University, 1984.

https://en.wikipedia.org/wiki/Weyto_(African_caste)

# አባሪዎች

## አባሪ 1 ለስፌት ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

አጠቃላይ መረጃ፡- ሙሉ ስም፣ዕድሜ፣የልጆች ብዛት፣መኖሪያ አካባቢ እና መተዳደሪያ?

1 የስፌት ስራ ላይ የሚሳተፉት እነማን ናቸው?ወንዶች ወይስ ሴቶች?ለምን?

2 ለስፌት ስራ የሚውሉ ቁሶች ምን ምንድን ናቸው?

3 ለስፌት ስራ የሚውሉ ጥሬ ቁሶችን ከየት ታገኛላችሁ?

4 የስፌት ንጥረ ቁሶችን ስትሰበስቡ በቡድን ነው ወይስ በግል ለምን?

5 የስፌት ስራ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

6 አንድን ቁስ ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ ምን ያህል ነው?

7 በስፌት ቁሶች ላይ የተለያዩ ቅርፆችን የምትሰሩት ለምንድን ነው?

8 ድሮ ይሰሩ የነበሩና በአሁኑ ወቅት የማይሰሩ ቁሶች ምን ምን ናቸው ለምን?

9 ድሮ የማይሰሩና በአሁኑ ወቅት ግን የሚሰሩ ቁሶች ምን ምን ናቸው ለምን?

10 የምትሰሯቸው የስፌት ቁሶች ምን ምን አገልግሎት አላቸው?

11 ቁሶቹን በመስራታችሁ ያገኛችሁት ጥቅም ምንድን ነው?

12 የቁሶቹ ተጠቃሚዎች አሉ? ካሉ ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

13 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በቁሶቹ እና በእናንተ ላይ ያሳደሩት ተፅህኖ አለ ወይ?

14 ከሙያው ጋር በተያያዘ በመንግስት እገዛ ይደረግላቹሃል ወይ?

## አባሪ 2 ለድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

አጠቃላይ መረጃ፡- ሙሉ ስም፣ዕድሜ፣የልጆች ብዛት፣መኖሪያ አካባቢ እና መተዳደሪያ?

1 የድንጋይ ወፍጮ ስራ ላይ የሚሳተፉት እነማን ናቸው?ወንዶች ወይስ ሴቶች?ለምን?

2 ለድንጋይ ወፍጮ ስራ የሚውሉ ቁሶች ምን ምንድን ናቸው?

3 ለድንጋይ ወፍጮ ስራ የሚውሉ ጥሬ ቁሶችን ከየት ታገኛላችሁ?

4 ለድንጋይ ወፍጮ ስራ የሚውሉ ንጥረ ቁሶችን ስትሰበስቡ በቡድን ነው ወይስ በግል ለምን?

5 የድንጋይ ወፍጮ ስራ ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?

6 አንድን ቁስ ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ ምን ያህል ነው?

7 ቁሶቹን ከድንጋይ ስትሰሩ ምን አገልግሎት እንዲሰጡ አስባችሁ ነው?

8 ቁሶቹን በመስራታቹ ያገኛችሁት ጥቅም ምንድን ነው?

9 የቁሶቹ ተጠቃሚዎች አሉ? ካሉ ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

10 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በቁሶቹ እና በእናንተ ላይ ያሳደሩት ተፅህኖ አለ ወይ?

11 ከሙያው ጋር በተያያዘ በመንግስት እገዛ ይደረግላቹሃል ወይ?

## አባሪ 3 ለሀገር ሽማግሌዎችና ታሪክ አዋቂዎች የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1 የነገዴ ወይጦ ኅብረተሰብ መነሻ ታሪክ ምን ይመስላል?

2 የነገዴ ወይጦ ኅብረተሰብ የምን ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው ?

3 የነገዴ ወይጦ ኅብረተሰብ መተዳደሪያ ምን ምን ናቸው?

4 የስፌት እና የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩት ቁሶች ለኅብረተሰቡ ምን ምን አገልግሎት ይሰጣሉ?

5 የቁሶቹን አጠቃቀም በሚመለከት የተለወጠ ነገር አለ?

6 በስፌት እና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩት ቁሶች ከእለት ግልጋሎት ውጪ ምን ጠቀሜታ አላቸው?

7 ለባለሙያዎቹ እና ለቁሶች ሌላው ኅብረተሰብ ያለው አመለካከት ምንድን ነው?

8 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በቁሶቹ እና በባለሙያዎቹ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ አለ ወይ?

## አባሪ 4 ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1በእጅ ስራ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የኅብረተሰቡን አኗኗር በምን መልኩ ያሳያሉ?

2 በእጅ ስራ ባለሙያዎቹ ለሚሰሩ ቁሶች ኅብረተሰቡ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

3 በሁለቱ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ሙሉ በሙሉ ለውጥ እንዳይከሰትባቸው እያከናወናቹት ያላችሁት ተግባር ካለ ብትገልፁልኝ ከሌለ ለምን?

4 የስፌት ስራ በሴቶች የድንጋይ ወፍጮ ደግሞ በወንዶች የሚሰራው ለምንድን ነው?

5 የስፌትና የድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድን ነው?

## አባሪ 5 ምልከታ የተደረግባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች

1.የቁሶቹ መስሪያ ንጥረቁስ ከብረት፣ከአፈር፣ከድንጋይ፣ከእንጨት ወይስ ከእፅዋት?

2.የቁሶቹ ቅርፅ እና መጠን ምን ይመስላል?

3.ባለሙያው ቁሱን የሚሰራበት ምክንያት ለራሱ ወይስ ለገበያ?

3.ቁሶቹን የመሸጫ ቦታ መንገድ ላይ ወይስ ሱቅ?

4.ቁሶቹ የሚጓጓዙበት ሁኔታ በሸክም፣በእንስሳት ወይስ በዘመናዊ ትራንስፖርት?

5.ባለሙያው አንድን ቁስ ለመስራት የሚፈጅበት ጊዜ በሰዓት ፣ በቀን ወይስ በሳምንት?

6.የቁሱን ዋና ጠቀሜታ ለመገልገያነት ወይስ ለጌጥ?

7.የባለሙያው የስራ ሁኔታ በትርፍ ጊዜ ወይስ በቋሚነት?

8.የባለሙያው የመስሪያ ቦታ ሁኔታ መንገድ ላይ ፣ ሱቅ ውስጥ ወይስ መኖሪያ ቤት?

9.የቁሱ አሰራር ደረጃዎች በመጀመሪያ፣በመቀጠል፣በመጨረሻ ደረጃ ምን ይሆናል?

## አባሪ 6 በስፌት እና በድንጋይ ወፍጮ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አገልግሎታቸው

| ተ.ቁ | የቁሶቹ ስም | የቁሶቹ አገልግሎት |
|---|---|---|
| 1 | መሶብ | ለእንጀራ ማስቀመጫ |
| 2 | ሰበጥራ | እንጀራ መሳቢያ |
| 3 | የጀበና ማስቀመጫ | ጀበና ማስቀመጫ |
| 4 | ሌማት (ቀለምሻሽ) | እንጀራ ማቅረቢያ |
| 5 | አገልግል | ምግብ ለመያዝ፣ለመዳርያ |
| 6 | ሙዳይ | ጢሳጢሶችን ፣ ጌጣጌጥ ለማስቀመጥ |
| 7 | ቁና(ወራንታ) | ለእህል መስፈሪያነት |
| 8 | ሰፌድ | እህል ለማበጠር እና ለማነፈስ |
| 9 | ወንፊት | እህል ለመንፋት |
| 10 | ወለወል | ለተሸከርካሪዎች መቀመጫ |
| 11 | ታንኳ | ለመጓጓዣ |
| 12 | የድንጋይ ወፍጮ | እህል ለመከካት እና ለመፍጫ |

## አባሪ 7 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ | የስራ ድርሻ | ቀን | ወር | ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እናና ቢያዝን | ሴ | 43 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 13 | 07 | 2011 |
| 2 | ናናዬ ገዳም | ሴ | 40 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 15 | 07 | 2011 |
| 3 | እናና አያሌው | ሴ | 38 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 17 | 07 | 2011 |
| 4 | ካሳዬ ማስረሻ | ሴ | 45 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 17 | 07 | 2011 |
| 5 | ስመኝ መርሻ | ሴ | 44 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 14 | 07 | 2011 |
| 6 | አንሻ ቸሩ | ሴ | 32 | 03ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 14 | 07 | 2011 |
| 7 | እማ ዘመድ | ሴ | 48 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 14 | 07 | 2011 |
| 8 | ተገኝች ተሾመ | ሴ | 49 | 03ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 13 | 07 | 2011 |
| 9 | ካሳዬ ጌታሁን | ሴ | 37 | 03ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 15 | 07 | 2011 |
| 10 | መድሃኒት አየለ | ሴ | 32 | 16ቀበሌ | የስፌት ባለሙያ | 16 | 07 | 2011 |
| 11 | የሺህዋስ ብርሃኑ | ወ | 33 | 16ቀበሌ | የድንጋይ ወፍጮ | 18 | 07 | 2011 |
| 12 | መሐመድ አሊ | ወ | 48 | 16ቀበሌ | የድንጋይ ወፍጮ | 19 | 07 | 2011 |
| 13 | መሐመድ ሁሴን | ወ | 47 | 16ቀበሌ | የድንጋይ ወፍጮ | 18 | 07 | 2011 |
| 14 | እንድሪስ ሙሃባ | ወ | 28 | 16ቀበሌ | የድንጋይ ወፍጮ | 18 | 07 | 2011 |
| 15 | ግርማ ብርሃኑ | ወ | 29 | 16ቀበሌ | ታሪክ አዋቂ | 13 | 07 | 2011 |
| 16 | አህመዴ ዳውድ | ወ | 64 | 16 ቀበሌ | ታሪክ አዋቂ | 16 | 07 | 2011 |
| 17 | ፋሲል ሙጩ | ወ | 28 | 16ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 13 | 07 | 2011 |
| 18 | በሃይሉ ግዛው | ወ | 32 | 16ቀበሌ | ታንኳ ሰራተኛ | 17 | 07 | 2011 |
| 19 | ያሬድ ደግፌው | ወ | 30 | 03ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 14 | 07 | 2011 |
| 20 | ኤፍሬም በላይ | ወ | 28 | 16ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 15 | 07 | 2011 |
| 21 | አንበሳው በለው | ወ | 35 | 16ቀበሌ | ታሪክ አዋቂ | 15 | 07 | 2011 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | አብደላ መሐመድ | ወ | 36 | 03ቀበሌ | የግል ሰራተኛ | 16 | 07 | 2011 |
| 23 | ጌታቸው ዘውዱ | ወ | 29 | 03ቀበሌ | የመንግስት ሰራተኛ | 16 | 07 | 2011 |
| 24 | ሱሌማን በሽር | ወ | 32 | 16ቀበሌ | መምህር | 17 | 07 | 2011 |
| 25 | ታደለ ጫካ | ወ | 30 | 03ቀበሌ | መምህር | 17 | 07 | 2011 |
| 26 | ወንድይፍራው ዘውዱ | ወ | 62 | 03ቀበሌ | የሀገርሽማግሌና ታሪክ አዋቂ | 18 | 07 | 2011 |
| 27 | ካሳሁን ቦጋለ | ወ | 61 | 16ቀበሌ | የሀገር ሽማግሌና ታሪክ አዋቂ | 18 | 07 | 2011 |
| 28 | እቴቱ ቦጋለ | ሴ | 49 | 16ቀበሌ | ታሪክ አዋቂ | 19 | 07 | 2011 |
| 29 | ወይንሸት አያሌው | ሴ | 52 | 03ቀበሌ | ታሪክ አዋቂ | 19 | 07 | 2011 |
| 30 | ወንድወሰን ጥበቡ | ወ | 35 | 03ቀበሌ | የባጃጅ ሹፌር | 15 | 07 | 2011 |
| 31 | አባ አረጋዊ | ወ | 58 | 16ቀበሌ | የሃይማኖት አባት | 18 | 07 | 2011 |

# አባሪ 8 የፎቶ ግራፍ ንባብ



አቶ መሐመድ አሊ ድንጋይ ሲጠርቡ



አቶ እንድሪስ ሙሀባ ወፍጮ ሲወቅሩ



አቶ የሺህዋስ ብርሃኑ ስለድንጋይ ወፍጮ አሰራር ሲናገሩ



አቶ መሐመድ አሊ ወፍጮ ሲወቅሩ



ወ/ሮ እናና ቢያዝን የመሶብን አሰራር ሲገልፁ



ወ/ሮ አንሻ ቸሩ የአገልግልን አጠቃቀም ሲያስረዱ



ወ/ሮ አንሻ ቸሩ የሰፌድን አጠቃቀም ሲያሳዩ



ወ/ሮ ካሳዬ ማስረሻና ስመኝ መርሻ ስለስፌት ሲናገሩ




ወ/ሮ አንሻ ቸሩ ስለነገዴዎች ጥንት አመጣጥ ሲናገሩ



የደረቀ ደንገል



ወ/ሮ ተገኘች ተሾመ እና ካሳዬ ጌታሁን ስለስፌት አሰራር ሲናገሩ



03 ቀበሌ ገበያ